# ዝሆን ላይ የሚጮህ እብድ ውሻ ብቻ ነው [ ህ.ወ.ሓ.ት.]

ገብረመድህን አርአያ

9/05/2016

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከህፃናት እስከ አዋቂዎች (የወያኔው) ፡ ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ማንነት ካወቁ ብዙ ዓመታት አስቆጥረዋል። ህወሓት ከየት መጣ፣ አላማውስ ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች የሕዝብ መነጋገሪያ ከሆነ አመታት ያስቆጠረ ነው ።የኢትዮጵያ ህዝብ ፤የኢትዮጵያን ሏላዊነት ደሙ አፍስሦ አጥንቱን ከስክሶ አንዲት ሏላዊት ኢትዮጵያ ያደረገ ህዝብ ፤በቋንቋ በሃይማኖት በዘር ያልተነጣጠለ ያልተከፋፈለ ህዝባዊ አንድነቱ ተፋቅሮ ተዋዶ በጋብቻ ተጋብቶ ፍቅርና ሰላም ገንብቶ ለስንት ሺህ ዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ የመጣ ኢትዮጵያዊነት ጠብቆ ፤የመጣ ኩሩ ህዝብ ኢትዮጵያዊ ነው ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ፤ አረንጓዴ፤ብጫ ፤ ቀይ ፤ ሰንደቅ ዓላማው ከስንት ሺህ ዘመናት ተረክቦ የማንነቱ መግለጫ አርማው ፤ተንከባክቦ ሲጠብቃት ጠብቆም ከትውልድ ወደ ትውልድ እያሸጋገር ሰንደቅ አላማችን የሃገርና የህዝብ ኩራት ደማቅ መለይታችን ኩራታችን በመሆን የተሰፋችን ሂወት ሆና ኑራለች ። የውጭ ባእዳን ጠላቶ ኢትዮጵያን በመውረር ግብጽ፤ሱዳን ፤ ጣልያን ሊብያ ወ.ዘ.ተ. በተደጋጋሚ ኢትዮጵያን ለማጥቃትና ለመውረር ያደረጉት ብዙ ሙኮራዎች በህዝብዋ አንድነትና አኩሪ ጀግንነት ኢትዮጵያዊ የመጡበት ጠላቶች ፊት ለፊት በጦር ሜዳ ተዋግቶ አሸንፎ ወራሪ ገድሎ ቀሪዉም ወደ መጣበት እንዲሸሽ በማድረግ የሚታወቅ የማይበገር ህዝብ ነው ።ኢትዮጵያ በባእዳን ጠላቶች አትደፈርም ብሎ ዘብ የቆመው የኢትዮጵያ ህዝብ በታሪክ ማህደር ውስጥ በጠላት የማትደፈር እትዮጵያ ፤በዓለም ውስጥ ቀዳሚው መእራፍ ይዛለች ።

ኢትዮጵያ ብዙ ጠላቶች አልዋት ፤በመሬቱ ተፈጥራዊ አቀማመጥም በጠላቶችዋ የተከበበች ናት ፤በሆንም ቅሉ ጠላቶችዋ የኢትዮጵያ ህዝብ ጀግንነት በጦር የማይቀለበስ ህዝብ ፤ወራሪ ጠላት ቢመጣበትም በአንድነቱ ተሰባስቦ ለጠላት እሾህ ተዋጊ ደፋር ህዝብ መሆኑም በሚገባ ስለሚያውቁ ፤እንደ ድሮው ሠራዊታቸው አስከትለው ኢትዮጵያን ወረው የኢትዮጵያን አንድነት ለማናጋት ፤ችሎታና አቅም እንደሌላቸው በመገንዘብ ፤ ከምዕራባውያን በተለይ እንግሊዝና አሜሪካ በመተባበር እነ ሱዳን፤ግብጽ፤ኢራቅ፤ሶሪያ፤ ጣልያን ፤ሊብያ ሶማሊያ ( መቃድሾ )ወ.ዘ.ተ. ተባብረው ፤ኢትዮጵያን የምናፈርሳት የምንበታትናት በራስዋ ዜጎች በቻ ነው ፤ይህም አስታጥቀን በተለያዩ ዘዴዎች እየደገፍን የብሄር ጥያቄ ፤ እስከ ነፃነት ጥያቄ የሚታገሉ መፍጠር ብቻ ነው ያለው ፖሊሳቸው አማራጭ ብለው ባወጡት እቅድ ፤ማ.ገ.ብ.ት =====ማሕበር ገስገስቲ ብሔረ ትግራይ === የዚሁ ፍሬ ነው ።ለዚሁም የመጀመሪያ ተማራኪው አረጋዊ በርሄ ሲሆን ጋሻ ጃግሬው ግደይ ዘራጽዮን አስከትሎ ነው ።

ህወሓት የትጥቅ ትግሉን ከመጀመሩ በፊት ተዘጋጅቶ ወደ ትጥቅ ትግሉ የገባበት ምክንያት አሉት ። 1ኛው የኢትዮጵያን አንድነትና ሏላዊነት ለማፍረስ ብሎም ለመበታተን ነው ። 2ኛው ሕዝብዋ በቋንቋው ሃይማናትና ዘርን መእከል በማድረግ የኢትዮጵያን አንድነት በሚያዘጋጀው ፖሊሲ ለመከፋፈል ለመበታተን ከዚሁ መነሻ ህዝቡ ለእርስበርስ ጦርነት ኢትዮጵያዊ ህብረተሰብ እርስበራሱ እንዲተላለቅ አመቺ ነው ብሎ ስላመነበት 3ኛው ተ.ሓ.ህ.ት. ህ.ወ.ሓ.ት. የተነሳለት ዓላማ የኢትዮጵያን ሏላዊነት አንድነት ከፈረሰ ህዝብዋም እርስበራሱ ወደ ማያባራው ጦርነትና መተላለቅ ከገባ ነፃ የሆነች ትግራይ የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት ለመመስረት አመቺና ጥሩ ሁኔታ ይፈጥራልብሎ ስለሚያም ፤ 4ኛው የህ.ወ.ሓ.ት መስራችና አመራር በትልቁ በአቋም ደረጃ የያዙት ኢትዮጵያን ለመበታተን ህዝቡን መከፋፈል ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የ አማራው ህልውና በማያዳግም ሁኔታ መመታትና ከመሬት መጥፋትና መደምሰስ አለበት፤ ከዚሁም ጎን ለጎን የእትዮጵያ ተዋህዶ ከርስትናም ሆነ የአማራው ቋንቋ የሆነው አማርኛ አብሮ እንዲከስም መቻል ማድረግም አለብን፤ የእስልምና ሃማኖትም አብሮ እንዲጠፋ ማድረግ ። ይህን በተግባር ስንጀምረው ኢትዮጵያዊነት የሚለው የአማራው ካባውም አብሮ ይከስማል ይጠፋል ።/ስለሆነም በፕሮግራሙ ቀዳሚ ምእራፍ በመስጠት በጽሁፍ አስቀምጦታል።

ህወሓት የትጥቅ ትግሉ እንደጀመረም በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኘው ሕዝብ በተለይ የትግራይ ሕብረተሰብ በግልጽ በማያሻማ ከመነሻው ጀምሮ ተቃውሞታል። ህ.ወ.ሓ.ት የተባለው ድርጅትና ፕሮግራሙ አልተቀበለውም ነበር ።ከዚሁም የተነሳ የ ህ.ወ.ሓ.ት አመራር ቂም በቀል በመያዝ በሰነዘሩት የጥቃት እርምጃ የትግራይ ሕብረተሰቡ በጣም ብዙ የሒወት መስዋእትነትና ሃብት ንብረቱ በህ.ወ.ሓ፣ት. እየተዘረፈ ውርስ ሆነዋል ተብሎ የፈረሰው ቤት ከህ.ወ.ሓ.ት ግድያ ያመለጠ ትንሽ ቢሆንም ወደ ጎንደር ሸዋ ጎጃም ተበተነ ።

በየካቲት ወር 1968 የተዘረጋው ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ-ሕዝብ ፕሮግራሙ በመጀመሪያ ተቃውሞ የገጠመው በትግራይ ሕዝብ ነበር። በዚሁም የተነሳ የትግራይ ሕዝብ ከፍተኛ የመስዋ'እትነት እዳ ከፍሎበታል። በህወሓት አመራር ሕዝቡ ከየቤቱ ከተገኘበት በህወሓት የሃለዋ ወያኔ አባላት እየተያዘ ተረሸነ፣ ንብረቱ ተወረሰ፣ ቤቱ ፈረሰ፣ ሕፃናት አሳዳጊና ወላጅ በማጣት ተበታትነዋል። ፕሮግራሙ እውቅና አንሰጥም፣ እናንተ አሁን በትጥቅ ትግል ተሰማርተናል የምትሉትን ማንነታችሁን አናውቅም፤ በግልጽ የሚታየው በፕሮግራም አቋማችሁ ጸረኢትዮጵያ ሉአላዊነት መነሳታችሁ ይናገራል።

እኛ የትግራይ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያ ሃገራችን በተደጋጋሚ በግብጾች፣ ቱርኮች፣ የሱዳን ማህዲስቶች፣ በጣልያን ስትወረር ሃገራችንን ከጠላት ለመከላከል ሁላችን ኢትዮጵያውያ አማራ ኦሮሞው አፋሩ አሩሲው ወሊጋው ትግሬው ወላይታው ሲዳማው ኦጋዴው ከምባታው ወ.ዘ.ተ.ሁሉም ኢትዮጵያዊ አንድም ሳይቀር በዘር በቋንቋ በሃይማኖት ሳንከፋፈ በአንድነት በኢትዮጵያዊነታችን ተባብረን ተደጋግፈን ሃገራችን ኢትዮጵያ በጠላት እንዳትወረር ደማችንን አፍሰን አጥንታችንን ከስክሰን ነፃነቷን የጠበቀች ኢትዮጵያን ለልጆቻችን አስረክበናል።ተ.ሓ.ህ.ት. የምትሉት የምትናገሩት ነጻነትዋ ታሪክዋ ገናናዋ እትዮጵያ የቀይ ባህር ባለቤት የቀይ ባህር ንግሥት ኢትዮጵያ ታሪዋን በመካድ ኢትዮጵያ የተፈጠረችው በዳግማዊ ምኒሊክ ፡ታሪክዋ ከ 100 ዓመት ያነሰ ኢትዮጵያ የምትባል ሃገር እንዳልነበረች በየቦታው እየተዘዋወራችሁ ለትግራይ ህብረተሰብ ትሰብካላችሁ አማራ የትግራይ ህዝብ ጠላት ደመኛ ጠላት የምትሉት ለኛ ጠላት ሳይሆን ወንድማችን ሥጋችን ኢትዮጵያዊ ወንድማችን ነው ።

ዛሬ ለትግራይ ሕዝብ ታግለን ትግራይን ነፃ አውጥተን የራስዋ መንግሥት ትመሰርታለች የምትሉት የተሓህትህወሓት መሪዎች ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረበት ይህን በናንተ ፕሮግራም የተካተተውን ለአስተዳደሩ ለቅኝ ገዥነት እንዲመቸው ያስቀመጥው ሃገርና ሕዝብን ከፋፍሎት የነበረውን በጣልያን እቅድ የኢትዮጵያን አንድነት ለማጥፋትና ለመደምሰስ ነው። ታዲያስ እናንተ ከጣልያን የከፋችሁ እንጂ የተሻላችሁ አይደላችሁም፤ በማለቱና በግልጽ በመናገሩ ከሐምሌ 1968 ጀምሮ የህወሓት መሪዎች ሰፊ የመግደልና የማጥፋት እርምጃ በትግራይ ሕብረተሰብ ላይ በማጠናከር ሕዝቡን አጠፉት።ሃብት ንብረቱ ወረሱት ፤ ቤቱ ፈረሰ ።

በዚህ ወቅት የነበሩት ዋና አመራር፤ አረጋዊ በርሄ፣ የድርጅቱ ሊቀመንበርና ወታደራዊ አዛዥ፤ ግደይ ዘርአጽዮን፣ ም/ሊቀመንበር፤ አባይ ፀሃየ፣ የፖለቲካ መሪ፤ ስብሃት ነጋ፣ የአረጋዊ በርሄ አማካሪና የሃለዋ ወያነ ሃላፊ፤ ስዩም መስፍን እና ተጨማሪ ዋና ተባባሪ መለስ ዜናዊ። እነዚህ ስድስቱ ታጋዮች በሕዝብ ላይ የሚወስዱትን እርምጃ ትመካክረው በአንድነት ተሰባስበው ይወስናሉ፣ በተግባርም ይፈጽማሉ። በ 1969 ከፈጸሙት የግፍ ግፍ ጣልያን 1928 ኢትዮጵያን ዳግም በወረረበት ጊዜ ኢትዮጵያውያን ከተለያዩ የሃገሪቱ ክፍል ከተት በማለት ሃገራቸውን ከወራሪ ጠላት ለመከላከል በሞላው ሃገራችን በተለያዩ የጦርነት አውድማ ተሰልፈው ወራሪውን ጠላት በአምስት ዓመት የአርበኞች ታጋድሎ ተሸንፎ ጓዙን ሳይጠቀልል በውርደትና በሃፍረት ተሸንፎ ወደመጣበት ሃገሩ ጣልያን እንደሸሸ ከገድላዊ ታሪካችን ተምረናል።

የትግራይ ሕዝብ ከወንድሞቹ ኢትዮጵያውያን ጎን ተሰልፎ ለሃገር ሉዓላዊነትና ክብር ሲል መስዋእትነት ከከፈሉት ኢትዮጵያውያን አንዱ ነው። የተሓህት-ህወሓት መሪዎች ይህ የሃገር ክብር የተቀደሰ ጀግንነት አልተቀበሉትም። ለምን የትግራይ ሕዝብ ጸረ-ጣልያን ሆኖ ተሰለፈ በማለት የተናደዱት በአረጋዊ በርሄ የሚመሩ የተሓህት-ህወሓት መሪዎች አርበኞች አዛውንቶችን ከየቤታቸው በመልቀም ከየአሉበት በማሰር በቀን ከእርሻ ቦታው ለሊት ክቤቱ በማፈን ሃለዋ ወያነ አስገብተው ደብዛቸው እንድ ውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ። ከነዚህ ከተገደሉት ብዛታቸው ባይታወቅም ለአብነት ከሚጠቀሱት መካከል ፊታውራሪ በጹእ ው/ጊዮርጊስ፤ የ 82 ዓመት፣ ዳጃዝማች ዘገየ አዛውንት ከነልጆቻቸው፣ ባቡ ዘገየ፣ ፊታውራሪ እምብዛ፣ ፊታውራሪ አጽብሃ፣ አስር አለቃ ገብረሥላሴ፣ የ 10 አለቃ ገብረዝጊ አለማዮህ እነዚህ ለአብነት ይበቃሉ። እነዚህ የኢትዮጵያ አርበኞች ከያሉበት እየተያዙ የተገደሉት ከጣልያን ጋር ለምን ጦርነት ገጠማችሁ ተብለው እንጂ አዛውንቶቹ ያጠፉት ጥፋት የለም። ይህ ሲሆን እውነት ተሓህት-ህወሓት ለትግራይ ሕዝብ የቆሞ ነው? መልሱ፣ አይደለም ነው።

ተሓህት-ህወሓት በፀረ-ኢትዮጵያ ባእዳን የተመሰረተ ድርጅት ነው። ለስልጣን ያበቁትም እነሱ ናቸው። ተሓህት-ህወሓት በትግራይ ሕዝብ ላይ የፈጸመው ግፍ እጅግ ዘግናኝ ስለሆነ ሌላው ቀርቶ ፈዳያን ወይም አትፍቶ ጠፊ terriorist ቡድን በማቋቋም በየአውራጃ ያፈሰሰው ደም የትናንት ትዝታ ነው። የትግራይ ሕዝብ በተሓህት-ህወሓት ንብረቱ ተዘረፈ፣ መሬቱ ተነጠቀ፣ ቤቱ ፈረሰ፣ ለችግርና መከራ ተዳረገ፣ ተገደለ፣ ተሰደደ። ለዚህ ዋና ተጠያቂዎቹ የህወሓት አመራር፣ አረጋዊ በርሄ፣ ግደይ ዘርአጽዮን፣ አባይ ፀሃየ፣ ስብሃት ነጋ፣ ስዩም መስፍን እና መለስ ዜናዊ ናቸው። እነዚህም ቢሆኑ ተከታትለው የመጡ፤ ስየ አብርሃ፣ አውአሎም ወልዱ፣ ገብሩ አስራት፣ ዘርአይ አስገዶም፣ ጻድቃን ገብረተንሳይ፣ አስፍሃ ሃጎስ፣ አርከበ እቁባይ፣ ተወልድ ወ/ማርያም፣ እነዚህ ደግሞ በሕብረተሰዉ ግድያውን በመፈጸም እና ጥረው ግረው ያፈሩትን ሃብት ንበረት ለህ.ወ.ሓ.ት ውርስ ተደርገዋል በማለት በመዝረፍ ተባባሪና አስተባባሪ በመሆን በትግራይ ሕዝብ ወንጀል ፈጽመዋል ። በታጋዩ ላይ በፈጸሙት ወንጀል ተጠያቂ ናቸው ፤። በፈፀሙት አሰቃቂ ተግባራቸው በወንጀሉ ይጠየቃሉ። በተለየ ደግሞ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት በተመለከተ ከላይ የተጠቀሱት ዋና መሪዎች የኢትዮጵያን አንድነት፣ ሉአላዊነት፣ መሬት አሳልፎ ለሱዳን በመሸጥ የወያኔ አመራር ቀዳሚ ተግባራቸው አደርገው ሲንቀሳቀሱ፣ እነዚህ የተጠቀሱት የማ/ኮሚቴ አባላት ተባባሪ በመሆን በኢትዮጵያና ሕዝቧ ላይ በርካታ የካሃዲነት ተግባራት ሲፈጽሙ የቆዩ ናቸው።

የኤርትራን መገንጠልም ተባብረው ከነአረጋዊ በርሄ ጋር በመወገን ኤርትራን አስገነጠሉ በሃገር ላይ ጉዳት አድርሰዋል።ለጊዛዊ ጥቅም ብለው ከሱዳን መንግሥት በጀነራል ጃአፈር ኒሜሪ ፕረዚዳንት ነበር ጊዜ በወቅቱ የነበረው የገዳሪፍ ገዥ በ 1975 ዓ.ም መስከረም ወር ከላይ የተጠቀሱ የህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች እና የሱዳን ባለሥልጣናት በቋጨት ውል መሰረት የኢትዮጵያ ለምና ታሪካዊ መሬት በጸረ ኢትዮጵያዊነት የተነሱት የወያኔ መሪዎች አሳልፈው ለባእድ ሃገር ለጊዜዊ ጥቅም ሸጠዋል ።

ይህም ምንም ህዝባዊ ውክልና ሳይኖራቸው ትግራይን ለማ ስገንጠል የተነሱ ከሃዲ ባንዳዎች ። ዛሬ ኢትዮጵያን እየገዛ ያለው ቅኝ ገዢ ወያኔ ህወሓት ለሱዳን ለመስጠት ደፋ ቀና እያሉ ይገኛሉ ። በዚሁስ የኢትዮጵያ ህዝብስ የሚወዳት የታሪክ ባለቤት ሃገሩ እየተሸራረፈች ለባዕድ ሃገር ለሱዳን እየተሸጠች ባለችበት ጊዜ ምን እያለ ነው ? የህ.ወ.ሓ.ት. አመራር ድሮ የነበሩ አሁንም ያሉ የኢትዮጵያን ሏአልዊንት የኢትዮጵያን ዳር ድንበር በአለም አቀፍ የተከበር ወሰን በወያኔ ባንዳ መሪዎች ለባእድ አሳልፎ መስጠት ከባድ ክህደት ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ህዝብ ሃገርና ህዝብ አሳልፎ መሸጥ ተፈጽሞበታል ።ወያኔው ህ.ወ.ሓ.ት ኢትዮጵያና ህዝብዋን አጠፋለሁ በማለት ከደደቢት በረሃ ይዞት በመጣ ጸረ ኢትዮጵያ አቋሙ ሥልጣን ከያዘበት ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛቱ ወስጥ ከተቆጣጠረ የኢትዮጵያን ሏላዊነት ያወደመ ያፈረሰ ስርዓት ነው ።በህ.ወ.ሓ.ት. የፖለቲካ ወይም የፖሊሲ ልዩነት ተፈጥሮ ወይም ታይቶ አያውቅም ፤የሚከተሉት ፖሊሲ ያው ነች ፤ፀረ ኢትዮጵያ ሏላዊነት ፀረ ህዝብ ከፋፋይ ፤ፀረ ዲሞክራሲ አሁንም በሥልጣን ያሉትን ጨምረን አንድም የራእይ ልዩነት ያለው ግለሰብ አመራር የነበረው የለም። ችግራቸው የሥልጣን ሽኩቻ ነው ፤ይህም ገና ከትግሉ መነሻ ጀምሮ በማያቋርጥ እስከ አሁኑ ጊዜ በግልጽ የሚታየው ነው ።በአሁኑ ጊዜ አረጋዊ በርሄም ሆነ ሌሎቹ የተባረሩ የሚናገሩት ለኢትዮጵያ ህዝብን ለማታለል ፤ በትግሉ ጊዜ ብዙ ልዩነት ነበረን ሲሉ ይደመጣሉ ፤ልዩነታችሁ ምን ነበር ተብለው ቢጠየቁ ግን መልስ የላቸውም ፤በተለይ አረጋዊ በርሄ ፤ድርጅቱ እስከ ተባረረ ሓምሌ ወር 1977 ዓ.ም. በዋናነት በበላይነት ሲመራው የነበረ እርሱ ነው ፤ፕሮግራሙን ተንከባክቡ ያቆየው እሱ ነው ፤የሚወጡ አዳዲስ ፖሊሲ በሱ ነው ፤በድርጅቱ ውስጥ አንድም አመራር የአረጋዊ በርሄ ሃሳብ የሚቃወም የለም ፤ሁሉ በእጁ ፤ስለሆነም ዛሬ የሚናገረው ውሸት መሆኑ መታወቅ አለበት ፤ይህ ሁሉ የሚዘባርቀው ፤ህ.ወ.ሓ.ት. ወንጀለኛ ድርጅት ነው በዘር ማጥፋት ወንጀል ይጠየቃል ፤ለወልቃይት ጠገዴ በጉልበቱ በመሪነት ፤ እንዲሁም የሰሜን ወሎ ወደ ትግራይ በማካለል የመሬት መስፋፋትና ወረራ የፈጸመው እሱ ስለሆነ ያቂነት ለማምለጥ ባፈሰሰው የንፁሃን ዜጎች ደም ተጠያቂነት ለመሸሽ ፤የፈጠረው ዘዴ ህዝብ መታለል የለበትም ።

አረጋዊ በርሄ በህወሓት ወስጥ ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ የመጣበት ማህበረ ገስገስቲ ብሄረ ትግራይ (ማገበት) ከተመሰረተበት እለት መስከረም 1967 ጀምሮ ተሓህት - ህወሓት የትጥቅ ትግሉን ከጀመረበት የካቲት 11፣ 1967 አንስቶ እስከ 1977 መጨረሻ ህወሓትን የሚዘውረው የነበረ በዚሁ ፀረ-ኢትዮጵያ አንድነትና ፀረ-ሕዝብ ግለሰብ ነበር። በድርጅቱ የሚፈጸሙ ጉዳዮች የሱን ይሁንታ ማግኘት አለባቸው እሱ ካልፈቀደ ደግሞ ይሰረዛል።

አረጋዊ በርሄ ገና ትገሉ ሳይጀመር የድርጅቱን ፕሮግራም በዋና ሃላፊነት ያዘጋጀ ነው። ይህ ፕሮግራም ነው ዛሬ ኢትዮጵያ

እያፈረስ እየበወዘ ሃገራችን ኢትዮጵያ በማትወጣው ችግር ዳርጓት ያለው ። የሰሜን ጎንደር ግዛቶችን አማራው የሚኖርበት ለብዙ ሺህ ዓመታት የአማራ መሬት ከዘር እስከ ዘር ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገር የመጣው የአማራው ባህልና ማንነት እየጠበቀ የመጣው የትግራይ መሬት በሚል አጉል የመስፋፋት ዘይቤ አማራውን ዘሩ በማጥፋት ያለቀው በህ.ወ.ሓ.ት. አመራር ታሪክ ዘግቦታል ለዚሁየሰው እልቂት ዘር ማጥፋት ተጠያቂው የህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች ከ 1967 ዓ.ም. እስከ ዛሬዋ እለት ያሉትን አመራር ተጠያቂ ናቸው ። ነብሱን አይማረውና ባለቀንዱ የባንዳ ዘር መለስ ዜናዊ እና ሌሎች የሞቱም በወንጀሉ ይጠየቃሉ ። ማለት ነው፣ ጠገዴ፣ ጠለምት፣ ወላቃይት፣ ቃፍታ፣ ሁመራ፣ ህ.ወ.ሓ.ት በፕሮግራሙ ውስጥ የእጅ ጽሁፉ( የአቶ አረጋዊ በርሄ) ከሰሜን ወሎም ራያና ቆቦ፣ ወልዲያ፣ አፍላ ደራ ወዘተ አጠቃላይ አለውሃ ምላሽ ተብለው የሚታወቁት የወሎ ግዛት ወደ ትግራይ አጠቃሎ ካርታውን ያዘጋጀው፣ መልክአ ምድሩን የለወጠው አሁን በትግራይ ክልል የተጠቃለሉት በአረጋዊ በርሄ የተዘጋጀው ነው። ይህን ለማረጋገጥ መቅድም በሚለው ( v )ቁጥር ነው (ገጽ 5 )እንመልከት ፤።

ህወሓት ትግሉን እንደጀመረ የቅድሚያ ትኩረት የሰጠው ሰሜን ጎንደርን ነበር። ይህንን የሰሜን ጎንደር ለም መሬት ለመያዝና ወሮ ወደ ትግራይ ለማጠቃለለ በወቅቱ መጠሪያው ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ (ተሓህት) አስቀድሞ በመዘጋጀት ከነዚህም የሚታዩት ከነበሩት ተጨባጭ ሁኔታዎች። ጊዜው በ መጀመሪያ 1969 ዓ.ም መጀመሪያ ጀምሮ።

1. የዚህ ድርጀት የሕዝብ ግንኙነት አባላት ሰርገው በመግባት በየቦታው የሚኖሩትን አማራ ታላላቅ ሰዎች የቦታው ታሪካዊ ጥናት የሚያውቁ ፤ በህዝቡ ተቀባይነት ያላቸው ፤ተናግረው ህብረተሰቡ የሚቀበላቸው ፤ጥናት በማካሄድ፣ 2. የታጠቁ ሰዎች ብዛታቸውም ሆነ ስሜታቸውን ማጥናት፣ ያላቸውን ሃብትና ንብረት የአካባቢውን ኗሪ ብዛትም ጭምር ማጥናት፣ይህ የትግራይ መሬት ነው ቢባሉ የሚያስከትሉት ችግር ማወቅ ማጥናት በተናጠል ማነጋገር ወ.ዘ.ተ. የሚሉትን ተሸክመው መንቀሳቀስ ተጀመረ ። 3. ይህንን የሰሜን ጎንደር ለም መሬት በጉልበትና በሃይል ለመውረር በአማራው ላይ ከባድ ጥቃት መፈጸም ግዴታ መሆኑ አስቀድሞ ተይዞ የትግራይን ሕዝብ ድጋፍ የሚፈልጉ የተሓህት አመራር በወቅቱ የነበሩ አመራር፣ አረጋዊ በርሄ፣ ስብሃት ነጋ፣ አባይ ፀሃየ፣ ስዩም መስፍን፣ ግደይ ዘርአጽዮን፣ በአራቱ መአዘን ተበታትነው አማራ የትግራይ ሕዝብ ጠላት መሆኑን፣ የትግራይን መሬት ነጥቀው የትግራይን ሕዝብ ለችግርና መከራ የደረጉት ደመኛ ጠላቶችህ ሲሆኑ የነጠቁህን መሬትህ ወልቃይት ፣ ጠገዴ፣ ጠለምት፣ ቃፍታ ሁመራ፣ እንዲሁም በሰሜን ወሎ ከአለ ውሃ ምላሽ የተነጠቅነውን መሬታችንን ለማስመለስ የትግራይ ሕዝብ የፈጠርከው መሪ ድርጅትህ ተሓህት ድጋፍህን እና እርዳታህን እንፈልጋለን፣ እያሉ ሕዝብ እየሰበሰቡ ተቆርቋሪ በመምሰል እያለቀሱ የትግራይን ሕዝብ አስተሳሰብ ለመቀየር ከፍጠኛ እንቅስቃሴ አደረጉ። ቢሆንም ከትግራይ ሕዝብ ያገኙት መልስ የሚከተሉት ነበሩ። 1. አማራ ጠላታችሁ ነው የምትሉን ከእውነት የራቀ ነው። አማራ የትግራይ ሕዝብ ጠላት አይደለም፣ ሆኖም አያውቅም። በአንድነት ሁነን ኢትዮጵያን ከብዙ የውጭ ወራሪ ሃይል አድነናል ተከላክለናልም።

   በዚህም አማራና ትግሬው ኢትዮጵያዊ ማተባችን በጋብቻና በባህል የተሳሰረ ሕዝብ ነው። ስለዚህ አማራ የኛ ወገን ትግሬውም የአማራ ወገን ነው።ልዩነት ጥላቻ ቅራኔ የለንም አንድ ኢትዮጵያዊ ህዝብ ነን ። ለወደፊቱ አይኖርም :አብረን እንኖራለን ።

2. ስለመሬቱ የምትናገሩት የትግራይ አልነበረም ሆም አያውቅም። ስለሆነም የሰሜን ጎንደርና የሰሜን ወሎ የትግራይ መሬት አልነበርም አሁንም አይደለም ከትግራይ የተነጠቀ መሬት የለም። የራሳቸው መሬት ነው። የኛ የትግራይ አይደለም፣ አልነበረም። የትግራይ ሕዝብ በተናገረው እውነተኛ ሃሳቡ ቀጠለ። ከሃቀኛ ሃሳቡ ፍንከች ባለማለቱ የወያኔው አመራር ግራ ተጋባ ጸረ ትግራይ ህዝብም መንቀሳቀስ ተጀመረ 3. ስለ ተሓህት የትግራይ ሕዝብ ድርጅት ነው የምትሉት፣ የታጠቀ ሃይል የትግራይ ሕዝብ ድረጅት አይደለም፣ አናውቀውም። የራሳችሁ የናንተው ነው። የትግራይ ሕዝብ ይህንን ድረጅት ከየት እንደመጣ፣ ማን እንደፈጠረው የምናውቀው ነገር የለም፣ እውቅናም አንሰጥም፣ በማለት የማያወላውል መልስ አግኝተው ራሳቸውን ደፉ፣ በዚሁ ጊዜ ግንቦት ወር 1968 ዓ.ም አካባቢ የትግራይ ህዝብን በተናጠል ለማጥቃት የተነሱት ። እነ አረጋዊ በርሄ። እነዚህ የተህሓት መሪዎች በትግራይ ሕዝብ ላይ አጸፋዊ ጥቃት በተቀናጀ መልኩ እንዲፈጸም ፖሊት ቢሮ፣ ማለትም በአረጋዊ በርሄ በሚመራው ግደይ ዘርአጽዮን፣ አባይ ፀሃየ፣ ስብሃት ነጋ፣ ስዩም መስፍን ተሰብስበው በሶስት እቅዶች ላይ

ተሰማሙ፡ - 1 የከተማውንና የገጠር ሕዝብ ግንኙነት በሕዝቡ ሙሉ የጥናት ክትትል እያደረጉ ለግደይ ዘርአጽዮን እንዲያቀርቡ፤፤.. - 2 የከተማውን ኗሪ የሚያጠቃ ፈዳያን 'አጥፍቶ ጠፊ" terrorist እንዲቋቋም፣ ስልጠናም እንዲያገኝ፣ - 3 ክብሪት የሚባል ጉጅሌ ገዳይና አፋኝ ቡድን እንዲቋቋም ተስማሙ። ይህ ጉጅሌ 12 ሰዎች የያዘ ሲሆን 7 ታጋዮች 5 ሚሊሽያ ሆኖ ተመሰረተ። የሚሊሽያው ዋና ተግባሩ መንገድ መሪ የሚፈለጉ ሰዎች ጦቋሚ።ከተራ ቁጥር 1---እስከ 3 ተግባራዊ ም ተደረገ ። -

በዚሁም ጊዜ የነበሩት (06) ሓለዋ ወያነ፣ ቀደም ሲል የነበሩት ሰፋፊ ቤቶች እየተፈለጉ ነዋሪውን በማባረር ሲጠቀሙበት የነበሩትን በሙተው ሰው በማይንቀሳቀበት ቦታ በመምረጥ፤ ሽራሮ ወረዳ ሽሽቢት ቡምበት፣ ሱር፣ ወርዲ፣ ፃኢና አዲበቅሎ፣ ዓዴት፣ ዓዲ ጨጓር፣ ፣ በለሳ፣ ማይሃምቶና ባኽላ ሳምረ። እነዚህን ሰፋፊ መግደያ ቦታዎች በአዲስ ዘዴ በመስራት ገነቡ ።፣ ይህም በግደይ ዘርአጽዮን መሪነት ከመሬት በታች 2 ሜትር ተቆፍረው እንዲሰሩ ከ200 ያላነስ እስረኛ የሚታሰርበት አንዲት ጠባብ መስኮት ያላት ሆኖ እንዲሰራ በህ.ወ.ሓ.ቱ ም/ሊቀመንበር በግደይ ዘራጽዮን ትእዛዝ መሰረት ከላይ በተጠቀሱ ቦታዎች ለመጀምሪያ ጊዜ ተሰሩ ። በተእዛዙ መሰረትም ሥራው ተጠናቀቀ። ይህ ጊዜ 1969 ዓ.ም መጨረሻ ነበር ።የትግራይ ህዝብም ያለቀው የተገደለው በእነዚህ ቦታ ነው ። በጠባብዋ መስኮት ዓየ ዛፍ በእርጥቡ እየተቆረጠ ተፈልጦ በእሳት በማቀጣጠል በጠባብዋ መስኮት በመልቀቅ የሰው ልጅ ፍጡር በጢሱ ታፍኖ ያለቀው አምላክ ይቁጠረው ። የዚች አሰቃቂ ግድያም የግደይ ዘራጽዮን ብልሃት ናት ።ለዚህ ክፉ የውንጀል ግድያም ይጠየቅበታ ።ይህ ክፉ አገዳደል በተለይ በአማራው ህዝብ በስፋት የወያኔ መሪዎች በመጠቀማቸው የአማራውን ዘር አጥፍተዋል ።

ክብሪት ተንቀሳቃሹ ጉጅሌ፡ ሆኖ ሲመሰረቱ፣ 16 ጉጅሌ ነበር የተመሰረተው የእነዚህ መሪዎችም በአርከበ እቁባይ፣ አሰፋ ማሞ፣ ሰአረ መኮንን፣ ሽሻይ በላይ (አመደ)፣ ታደስ ጋውናይ፣ ወዘተ በመደራጀት በየገጠሩና በየከተማው አካባቢ እንዲሁም በየወረዳው በሌሊት ተሸለኩልከው በመግባት የሚፈልጉትን ሰው ወንድ ፤ ሴት አፍነው በማውጣት ሃለዋ ወያነ ታስሮ ፤ታስራ በማስገባት እዛው እርምጃ ይወሰድበታል ( 06 ) ሓለዋ ወያኔ የገባ ሰው ሁሉ በሂወት ወደ ቤቱ አይመለስም ። ሕዝብ የሚገደልበት መግደያ የሲኦል ገሃነብ ነው ። በገጠሩ ነዋሪ በፈለጉት ስአት በሙሄድ ኗሪውን ሰላማዊ ዜጋ ኢትዮጵያዊ በማሰር ንበረቱን በመውረስ እየታሰረ ሃለዋ ወያኔ ገብቶ ይገደላል ፣ ቤት ፈረሰ ልጆች ካለ አባትና እናት ተበታትነው ቀሩ፤ በጅምላ ፉድጓድ በጥይት ይረሸናሉ። መግደያ ጉድጓዳቸውም የሚቆፉራት ራሳቸው ተገዳዮቹ ናቸው ።

ፈዳያን የተባለው በብስራት አማረ የሚመራው አጥፍቶ ጠፊ ሽብርተኛው ክፍል በተመሰረተው ከሓምሌ ወር 1969 ዓ.ም ጀምሮ በየከተማው አውራጃዎች አድዋ፤ መቀሌ ፤ሽሬ፤ አክሱም ፤አዲግራት፤ ውቅሮ ሁለት አውላእሎ ፤ ወዘተ እንዲሁም በወረዳዎች እየገባ በሙቶዎች የሚቆጠሩ በየከተማውና በወረዳው በቀን ተመሳስሎ በመግባት በየመጠጥ ቤቱ ሻይ ቤት በማኽል ከተማ ቤተ ክርስትያን ውስጥ አጋጣሚው ሲመችለት አፍኖ በማስወጣት የስንቱን ንጹሃን ዜጎች በጠራራ ቀን ደማቸው ፈሰሰ ተገደሉ።

በዚሁ ፈዳያን የተሰማሩ አመራር፣ አረጋዊ በርሄ፣ አድዋ፣ አባይ ፀሃየ፣ አክሱም፣ አርከበ እቁባይ፣ አዲግራት፣ ስዩም መስፍን፣ ውቅሮ፣ ስብሃት ነጋ፣ ተምቤን፣ በሽብርተኝነት ተሰማርተው ሰዎች ገድለዋል። ግደይ ዘርአጽዮን እንትጮ፣ ሰለከላካ፣ ራማ፤ ኩሓ የስንት ሰው ሕይወት ከግብረአበሮቹ ፈዳያን ጋር አጠፋ። ይህ የወያኔ ጥቃት ከተሓህት-ህወሓት በትግራይ ሕዝብ የማጥቃት ዘመቻው በተለያየ መልኩ ቀጠለ።ግደይ ዘራጽዮን አክሱም ከተማ የጉጅሌ መሪ በመሆን ሁለት የአብርሃ ወአፅብሃ ሁለተኛ መለስተኛ ደረጃ አስተማሪዎች መም/አበበ ፤ መም/ መላኩ መንገሻ የተባሉ አስተማሪዎች በመግደሉ ተወገዘ ።ተመልሶ አክሱም የሚገባበት እድልም የለውም ።

ይህ ሰው በተፈጠረው ውግዘት ለወላጆቹም ግደይ በፈጸመው ወንጀል ቁርሸው ትቶ አልፈዋል ። የግደይ ጣጣ በዙ ነው ፤ግደይ ዘራጽዮን ሱር ሓለዋ ወያኔ ታስረው የነብሩት በዙዎቹ አማራ ቀሪዎቹ የትግራይ ሰዎች በየታሰሩበት ከመሬት በታች የጉድጓድ እስር ቤቶች የዓየ እንጨት በማቀጣጠል እንጨቱ እይተቀጣጣለ በትንሸዋ ቀዳዳ መስኮት የገባው ጢስ እዛው ጉድጓዱ የታሰረው ንፁሃን ዜጎች በጢሱ ታፍነው ሲያልቁ የተመለከተው በህዝብ ግኙኝነት ክፍል የሚሰራ ታጋይ ዓለም ወልደገሪማ የሚባለው የቀ.ኃ.ሥ.ዩኒቨርሲትይ የ4ኛ ዓመት በኢኮነሚክስ ተማሪ የነበረው ፤ግደይ ዘራጽዮን ኢ-ሰአዊ አረሜናዊ ግድያ ህዝቡን በመፍጀቱ በዓይኑ በማየቱ በድርጊቱ አወገዘው ፤ግደይ ቂሙን ቋጥሮ ቆይቶ ፤በስራ ምክንያት ዓለም ው/ገሪማ ወደ ርጅን 2 የሚሄድ መሆኑ ስላወቀ ዓዴት የሚገኘ ሓለዋ ወያኔ 06 ለብስራት አማረ ደብዳቤ

ፅፎ ፤የውስጥ ይዘትዋ ዓለም ው/ገሪማ ይህች ደብዳቤ እንደሰጠ ተቀብለህ ወዲውኑ እሰረው ከዛ ረሽነህ ግደለው የምትል ፤ዓለም ው/ገሪም የመግደያው የፍርድ ወረቀቱ ተሸከሞ ሂዶ አዲበቅሎ ዓዴት ወዲያውኑ በጥይት ተደብድቦ ተገደለ ፡ ይህች የግፍ ግድያ ብዙም ሳትቆይ እጃቸው ለደርግ የሰጡ የአክሱም ልጆች ታጋይ ነበር ፤ዓለም በግደይ ዘራጽዮን እንደተገደለ ለውላጅ አባቱ ነገርዋቸው ፤ምህረይ (ቄስ ) ወልደገሪማም የአክሱም ህዝበ አዳም በልጃቸው በህ.ወ.ሓ.ት. መሪው የተፈጸመው ገፍ በየቤተ ክርስትያኑ ከማጋለጥ ቀጠሉበት ።የዓለም ወንድሞች ደማቸው ለመበቀል ፤ጊዜያቸው እየጠበቁ ናቸው ። ወደ ዋናው አረእስታችን ስንመለስ ።

ወያኔዎች በትግራይ ህዝብ የጥቃት ዘመቻ የከፈቱበት ምክንያት የትግራይ ህዝብ በኢትዮጵያዊነቱ እምነቱ ከፋፋይና ዘረኛው ወያኔ ፤በእውቅና አለመቀበሉ ቀጥሎ ያለውን ዋና ምክንያቶች እንመልከት ። 1. አማራ ደመኛ ጠላትህ ሲሉት አይደለም ወንድሜ ወገኔ ኢትዮጵያዊ ነው በማለቱ፣ 2 ተሓህት የትግራይን ሕዝብ አይወክልም አንውቃችሁን በማለቱ፣ 3 ተሓህት የነጠቀውን የሰሜን ጎንደርና የሰሜን ወሎ ለም መሬቶች አንቀበልም፣ የሰሜን ጎንደሩ የጎንደር ጠ/ግዛት ነው፣ የሰሜን ወሎ የወሎ ጠ/ግዛት ነው፣ ከትግራይ ግንኙነት የላቸውም በጎንደር በኩል የሚያዋስነን ተከዜ ወንዝ ነው ።በወሎ በኩል ማይ ጨው ችንኮማጂ ነው ፤ሲሆን በምን መልኩ ነው የትግራይ የሚሆነው በማለቱ፣ ከወንድሞቻችን ጥላቻና ቅራኔ አትፍጠሩብን ብሎ ጭሆ በመናገሩ ፤ ሸዋዊ የትግራይ አማራ ተብሎ የግድያ ኖህ የወረደበት ። 4 የተሓህትን ፕሮግራም አንቀበልም 1ኛ ትግራይ የኢትዮጵያ የታሪክ አስኳል የትግራይ ህዝብ በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ የሚመካ ነው ፤ትግራይ የኢትዮጵያ አካል ግዛት እንጂ ቅኝ ተገዢ አይደለችም ፤ አማራው ኢትዮጵያዊ ፤ ትግራይም ኢትዮጵያዊ ፤ ምንም ልዩነት የለንም ። በማለቱ ጭሆ በመናገሩ ።በህ.ወ.ሓ.ት. መሪዎች በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የታሪክ አዋቂዎች አዛውንት ሊቃውንት የአምስት ዓመት ከወራሪው ጣልያን የተዋጉ አርበኞች በሙብራት እየፈለገ የወያኔው መሪዎች የገደልዋቸው ያጠፍዋቸው ፤ ተገድለም ሃብት ንብረታቸው ህ.ወ.ሓ.ት ወረሰው ። እነዚህ የሃገርና የህዝብ አለኝታዋች ሙሉ በሙሉ በትግሉ ጊዜ አጠፉዋቸው ፤ ገደልዋቸው ። ፤ዛሬ ስለ ትግራይም ሆነ አጠቃላይ ስለ ነበረው ጥንታዊ ታሪክ በትግራይ ውስጥ የሚያውቅ ተፈልጎ አንድም አይገኝም ።ትግራይ በ 17 ቱ የህ.ወ.ሓ.ት. የትግሉ ዘመን ወድማለች ።

የታሪክ አዋቂ በኢትዮጵያዊነቱ የሚቆረቆር በትግሉ ዘመን ተመልሶ እንድያንሰራራ ተመልሶ እንዳይፈጠር አድርገው በመምታት አጥፍተዉታል ። በጣም የሚያስገርም ሁኔታም የተፈፀመው በወልቃይት ፤ጠለምት ፤ ጠገዴ ብቻ በሰሜን ጎንደር አማራው በተመሳሳይ ሁኔታ አዛውንቶች እየተፈለጉ በስውር እይታፈኑ የት እንደገቡ የማይታወቁ ማን ተያዘ ማን ተገደለ የሚለው በግልጽ ለማወቅ አስቸጋሪ ቢሆንም ብዙ የሰሜን ጎንደር አዋቂ ሽማግሌዎች የውሃ ሽታ ሆነው የቀሩ አሉ ፤ይህን ለማወቅ የሚችሉት የየአካባቢው ነዋሪዎች ናቸው ።እነዚህ ግን የታሪክ አዋቂዎች ናቸው ።ታሪክ አዋቂ ሲጠፋም ተተኪው ትውልድ ይቸገራል ።የህ.ወ.ሓ.ት. መሪዎች ይህ እንደፖሊሳቸው የሚጠቀሙበትም የቆየው ታሪክ ለማጥፋትና ለማክሰም ነው ።

በእነዚህ ንጹሃን የትግራይ እና የሰሜን ጎንደር ኢትዮጵያውያን የፈሰሰሰው ደም ትጠያቂው ማነው? ማነወስ ሃላፊነቱ የሚቀበለው ? ምንስ አጥፍተው ነው ? ወደ ትግራይ ስንመለስ ፤ የተናገሩት እውነት ነው ፡ትግራይ የአማራው ቅኝ ተገዢ አይደለችም ሰሜን ጎንደር ወልቃይት ፤ ጠገዴ ጠለምት ፤ቃፍታ ( ሰቲት ) ሁመራ የሰሜን ወሎን መሬቶች የትግራይ አይደሉም አልነበሩም ይህም ታሪክ የሚያውቀው ሃቅ ነው ።የትግራይ ህዝብ ምን አጠፋ ህ.ወ.ሓ.ት የገደለው የረሸነው ያጠፋው ። ማንኛው ህዝብ አስተዋይና አርቆም ሃሳቢ ነው የትግራይ ህዝብም ከዚሁ ተነስቶ ነብር እውነቱን የተናገርው ። ይህ ህ.ወ.ሓ.ት የጀመረው በትግራይ ህብረተሰብ ማጥቃትና መግደል የንጹሃን ዜጎችደም በከንቱ የፈሰሰው ይህ ደም አሁንም በእግዚአቢሄር ፊት እየጮኸ ይኖራል መሬትና ሰማይ የፈጠረ ጌታም ፍርዱ ይሰጣል የማይቀር ነው ።

የህ.ወ.ሓ.ት. መሪዎች የአማራው ጎንደሬው ለምና ሰፊ መሬት በሕገ ወጥ በጉልበት ለመንጠቅ የአማራው ደም የንጹን ኢትዮጵያወያን ዜጎች ደማቸው በትውልድ መንደራቸው እንደጎርፍ ፈሰሰ ካለምንም ጥፋትና ሃጥያት ፈሰዋል ዘራቸው አጥፍተዋል ህፃን አራስ እርጉዝ ሽማግሌ ወጣት ተገድለዋል በስዉር ጠፍተዋል የእንዚህ ንጹሃን ኢትዮጵያዊ ዜጎችም ፈጣሪ አምላክ ፊት ደማቸው እየጮኸ ነው ።ቀሪዎቹ በሂወት ያመለጡም በስደት እየተንከራተቱ ይኖራሉ ።ይህን አሳዛኝ ታሪክ ያነሳሁት የትግራይ ነፃ ህዝባዊ ወያኔ ፤ ህ.ወ.ሓ.ት. ማ.ገ.ብ.ት ተብሎ ሲፈጠር ቀጥሎም ደደቢት በርሃ ወርዶ ተ.ሓ.ህ.ት. ( ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ ) ከዛም ስሙን ለውጦ ህ.ወ.ሓ.ት. ( ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ) ቢልም እውቅና ያልሰጠው በአንጻሩ ግን የትግራይ ሕብረተሰብ ፀረ ወያኔ አምርሮ የታገለው ህዝብ ነበር ፤ ፀረ ወያኔ ሆኖ መታገሉ ከባድ መስዋእትነት በሂወቱ በንብረቱ በሃብቱ ከፍሎ ያለፈው ። ሁሉ ኢትዮጵያዊም ይህን በእምነት ሁሉ

ኢትዮጵያዊ ያምንበታል።

ለዚሁም ተጠያዊቆቹ አረጋዊ በርሄ፣ ስብሃት ነጋ፣ አባይ ፀሃየ፣ ግደይ ዘርአጽዮን፣ ስዩም መስፍን ፤መለስ ዜናዊ ሲሆኑ፣ እነዚህ በዋና የንፁሃን ደም በሰሜን ጎንደር በትግራይ በኢትዮጵያውያን ንፁህ ደም በፈጸሙት ወንጀል ግንባር ቀደም ተጠያቂ ናቸው ። ቀጥሎ ደግሞ፣፣ ስየ አብርሃ፣ አውአሎም ወልዱ አርከበ ዕቁባይ ገብሩ አስራት በዋናነት ግንባር ቀደም ይጠቀሳሉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ክስ ሲመሰርትም መነሻው ከዚሁ ነው ።የህ.ወ.ሓ.ት. ፋሽሽት ድርጅት ለብዙ ዓመታት የምሩም እነዚህ ፤ተከታትለው ወደ ሥልጣን የመጡ እንመለከታለን ።

ይህ የትግራይ ሕዝብ በማጥፋት የተሰማራው የህወሓት አመራር ሕዝብ በመግደሉ በተሰማራበት ወቅት በተሓህት ውስጥ የነበርው ታጋይ በዝምታ አልተመለከተውም ነበር ከዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎች እና በህዝቡ እየተፈጽሙት ያሉትን ግፍን ሰቆቃ ድርጅቱ ከምን ተነስቶ በምን ምክንያት ሰላማዊ ህዝብ እያሰረና እያሰቃየ ሽማግሌዎች ወጣቱን ወንድ ሴት ይፈጃል የሚሉና ተዛማች ብዙ ጥያቄዎች ተነሱ ። አመራሩ በታጋዩ የተነሱ የዲሞክራሲ ጥያቄዎች ተቀብሎ በሰላም ከመፍታት ይልቅ ታጋዩን በመወንጀል ። ይህ ፀረ ተ.ሓ.ህ.ት እንቅስቃሴ ነው በማለት ራሱ አመራሩ ለተነሱ የዲሞክራሲ ጥያቄ በመወንጀል ሕንፍሽፍሽ የሚል ስም በምስጠት ፣ በበዙ ታጋዮችና ሰላማዊ ዜጋወም በሕንፍሽፍሽ ተመርዘዋል ተብሎ ሰላማዊ ዜጋው ከየቤቱ እየተለቀመ ታጋዩ ከትግል ሜዳው እየተለቀመ እየታፈነ በቶርቸርና በእሳት እየተቃጠለ በእሳት የጋለ ፍም ሳንጃ ሆድ እቃው እየገባ ተገደል፣ ጠፋ፣ የተገደሉት ሰላማዊ ዜነችም ሙሉ ንበረቱ ሃብቱም በህወሓት ተወረሰ።የስንቱን ቤት ፈረሰ ።

የትግራይ ሕብረተሰብ ለዚሁ ሁሉ መጥፎ ጥቃት የተዳረገበት ዋና ምክንያት ከላይ የተጠቀሱ ሲሆኑ ሌላው ደግሞ ጣልያን ኢትዮጵያ በ 1928 በወረረበት ጊዜ በአርበኝነት ጸረ ጣልያንን የተዋጉ የተሓህት-ህወሓት አመራር ኮንነዉታ ፣ አረጋዊ በርሄ፣ ግደይ ዘርአጽዮን፣ አባይ ፀሃየ፣ ስብሃት ነጋ፣ ስዩም መስፍን፣ መለስ ዜናዊ ያሳለፉት መመሪያ እንዚህ የትግራይ ሸዋ አማራ በአጭሩ አነጋገር ሸዋዊ ትግራዋይ በሙሉ በየትም ትግራይ መሬት የሚኖሩ በሕዝብ ግንኙነት እየተለቀሙ ታሰረው ሃለዋ ወያኔ (06 ) በሚስጢር እንዲጋቡ በማለት በሰጡት የትእዛዝ መመሪያ ሁሉ ከያሉበት ተለቅመው ሃለዋ ወያኔ እየገቡ ተገድለዋል፣ ንብረታቸውን ተወርሰዋል።

ዛሬ በትግራይ እንኳንስ ከጣልያን የተዋጋ በወቅቱ ሕጻናት የነበሩትም አንድም ሰው አይገኝም፣ ተገድለዋል። ዋና ምክንያቱ የተገደሉት 1 የህ.ወ.ሓ.ት የፖለቲካ አቋም ወይም ፕሮግራም አንቀበልም ብለው በማውገዛቸው 2 አማራ የትግራይ ህዝብ ደመኛ ጠላት ስለሆነ አብረን እንምታው እናጥቃው ሲሉትም የሰጠው መልስ አማራ የትግራይ ህዝብ ጠላት አይደለም ሁላችን አንድ ኢትዮጵያ ወንድማሞች ነን አማራ የፈጸሙብን በደል ጥቃት የለም አማራው የኛ፤ እኛም የሱ ነን ፤ 3 የሰሜን ጎንደር የሰሜን ወሎ መሬት የትግራይ ነው የምትሉን የትግራይ አይደለም በታሪክም አልነብረም የወንድሞቻችን በጉልበት የምትወሩት ያላችሁ ርስተ መሬት አንቀበልም በማለቱ 4 ጣልያን ጣልያን የምትሉት በየቦታ ከጣልያን የተዋጋነው ሃገራችን ኢትዮጵያ ለመውረር በቅኝ አገዛዝ ስርአቱ ሊገዛን የመጣው ወራሪ ቅኝ ገዢ ጠላት የሃገራችን ኢትዮጵያ አንድነትና ሏላዊነት አሳልፈን አንሰጥም በማለት ጣልያን መታነው አሸነፍነው ፤ ኢትዮጵያን ነፃ አወጣን ፤ በማለት ፀረ ወያኔ ህ.ወ.ሓ.ት ባሳየው ጠንካራ አቋሙ ከላይ በተጠቀሱ የወያኔ መሪዎች ከባድ ጥቃት በመሰንዘር ህዝብ አለቀ ።

ዛሬ ታሪክ ነጋሪ በትግራይ ፈጽሞ አይገኝም። የታሪክ ፈላስፋዎች የታሪክ አዋቂዎች የሆኑት የወያኔው መስራቶችና አሁንም በሥልጣን ያሉት ደንቆሮች የወያኔ መሪዎች በሥልጣን ኮረቻ የተንጠለጠሉ ቅኝ ገዢዎች የህ.ወ.ሓ.ት. ባንዳዎች ናቸው።

ይህ በዚሁ እንዳለ፣ የትሓህት-ህወሓት መሪዎች በትግራይ ሕብረተሰብ የጀመሩትን ጥቃት እንደቀጠለ ሁኖ የወልቃይት፤ ጠገዴ ፤ጠለምት ፤ሰቲት ሁመራን ፤ በጉልበትና በማን አለብኝነት በካርታቸው የተካተተው በፕሮግራማቸው ውስጥ የትግራይ መሬት ነው በማለት ሰፊዉን የጎንደር ክፍለ ሃገር መሬት የሰሜን ወሎ መሬት በማካተት ( ፀሃፊና አዘጋጅ አረጋዊ በርሄ ) ሕገ ወጥ የለም ሰፊ መሬት ወረራ ፈጽመዋል ።ይህን ወረራ ለማስፈጸም የተካሄድ ቅድመ ዝግጅት በሰሜን ቤገምድር ( ሰሜን ጎንደር) ማለት ነው ) 1 ኛ መኩንን ዘለለው የተባለው ነገር ግን አካባቢውን የማያውቀው በስመ ተወላጅ በአባቱ በኩል ተወላጅ የሆነወን ታጋይና በህዝብ ግኑኝነት ክፍል የተመደበ በሱ የሚመራ ቡድን በወልቃይት ፤በጠገዴ ፤በጠለምት ጥናት እንዲያካሂድ በ 1969 ዓ.ም ውስጥ ተላከ ይህ ከሃዲ ግለሰብ ከግለ ሰው እስከ

ቡድን ከቡድን በየ በአላቱ እሁድ ወ.ዘ.ተ. በየቤት ክርስትያኑ እየተንቀሳቀሰ ወልቃይት ፤ጠገዴ ፤ጠለምት ፤ ቃፍታ ሁመራ የትግራይ መሬት መሆኑ የሰሜን ጎንደር ህዝብም ሁሉ ትግራዋይ መሆኑ የታርክ ሃቅነት በጎደለው ለማሳመን ባካሄደው መፍጨርጨር ሳይሳካለት በሙሉ የሰሜን ጎንደር ህዝብ በልበ ሙሉነት ወድቅ አደረገው ።

በግልጽም እናንተ ወራሪ የጣልያን አሽከሮች ውላጅ ናችሁ በማለት አሽማቀቃችው ።ይህ የጎንደር ግዛት በማንም ያልተደፈረ በእናንተ ከሃዲዎች እይፈፈርም ብሎ ህዝቡ በግልጽ የተናገረበት ጊዜም ነው ። ተዋርዱ ተደብዶቦ፤ ህዝቡም ወደ ማንም ቤት ዝር እንዳይሉ በማስጠንቀቅ በርሃብ ጠውልገው ወደ መጡብት እንዲመለሱ አደረጋቸው ።

ነገር ግን መኮንን ዘለለውና ቡዱኑ ሲያደርጉት የነበረው ሤራ ህዝቡ ሁሉ ቢቃወምም ትልልቅ ሰዎች የታሪክ አዋቂዎች የበሰሉ ጠንካራ ሰዎች በብዛት በሚስጢር እየመዘገቡ ፤ እነዚህ ሰዎች በሂወት ካሉ ነገሩ አይሳካም በማለት በድብቅ ስማቸው ወደ ወያኔ መሪዎች በየእለቱ በማስተላለፍ ለክፉ ሞት ዳረጉዋቸው ። የህ.ወ.ሓ.ት . መሪዎች አሁን የገጠማቸው ክሽፈትና ወርዴት አጠፋውን ለመመለስ ዝግጅታቸው አሰቀመጡ ፤ ቀደም በማለት _በትግራይ ሕብረተሰብ የአፈና ዘዴ በመጠቀም አነስተኛ ሀይል አፋኝ ጉጅሌ በማደራጀት ክፉና አረመኔው ጨካኞች አፋኝ ቡድን ብሶስት አቅጣጫ ተሰማራ። ይህ ጊዜም በ 1969 ዓ.ም. ወደ መጨረሻው አከባቢ በሶስት አቅጣጫ በማሰማራት 1. ወልቃይት ውስጥ፣ 2. ጠለምት፣ 3. ጠገዴ ውስጥ፤ ሲገቡ ፣ ጉጅሌቸው ይዘው በሶስቱ ቦታዎች ተሰማርተው ቀደም ሲል ከመኮነን ዘለለው የነበሩ የህዝብ ግኑኝነት መሪነት በድብቅ በዘዴ የተቃወሙት የሰሜን ጎንደር አማሮች አንድ በአንድ በተናጠል እያፈኑ ሰውን መልቀም ጀመራ የታፈነው ሓለዋ ወያኔ ገብቶ ይገደላል ፣ ወንድ፣ ሴት ተገደሉ። ሃብት ንብረታቸውም እየተወረሰ ዝርፍያው ቀጠለ ቀስ በቀስም የጀመሩት ጥቃት ቀጠለ ። ተ.ሓ.ህ.ት.ለ 1 ኛው ጉባኤ ይዘጋጅም ስለነበረ 1 ኛ ጉባኤው የካቲት 5 ቀን 1971 ዓ.ም. ዓዲ ዳዕሮ አካባቢ ማይ አባይ በተባለው ቦታ ተካሂዶ የአመራር ቦታ ለውጥም ተደረገ በዚሁ መሰረት እንደሚከተለው ተደላደሉ ።

በዚሁ ጉባኤ የተመረጡ አመራር ። አምስቱ የቆዩ ፖሊት ቢሮ ( ሥራ አስፈጻሚ ) እንዳሉ ተመልሰው ሥልጣናቸው ሲይዙ ቀሪዎቹም ዝርዝሩ እንመልከት ። 1 ኛ አረጋዊ በርሂ ወታደራዊ አዛዥ ፖሊት ቢሮ 2 ኛ ስብሃት ነጋ የህ.ወ.ሓት ሊቀ መንበር ፖሊት ቢሮ 3 ኛ ግደይ ዘራፅዮን የህ.ወ.ሓ.ት ም/ሊቀመንበር ፖሊት ቢሮ 4 ኛ አባይ ፀሃየ የፕሮፓጋንዳ ክፍል ዋና ሃላፊ ፖሊት ቢሮ 5 ኛ ስዩም መስፍን የውጭ ጉዳይ ዋና ሃላፊ ፖሊት ቢሮ 6 ገብሩ አስራት ማእከልይ ኮሚቴ 7 መለስ ዜናዊ የፕሮፓጋንዳ ጽ/ቤት ም/ሃላፊ ማእከላይ ኮሚቴ 8 አስፍሃ ሓጎስ ማእከላይ ኮሚቴ 9 አርከበ (ዮሓንስ ) እቁባይ ማእከላይ ኮሚቴ 10 ፃድቃን ገብረተንሳይ ማእከላይ ኮሚቴ 11 ስየ አብርሃ ማእከላይ ኮሚቴ 12 አታክልት ቀፀላ ማእከላይ ኮሚተ ግንቦት ወር 1971 ዓ.ም በስብሃት ነጋ በአባይ ፀሃየ እንዲሁም በመለስ ዜናዊ የተገደለ ። ገዳይ ሳሞራ (መሓመድ ) የኑስ በሲሞኖቭ ባልር መነጽር ጠመንጃ ።

13 ዘርአይ አስገዶም ማእከላይ ኮሚቴ 14 አውዓሎም ወልዱ ማእከላይ ኮሚቴ 15 ተወልደ ወ/ማርያም ማእከላይ ኮሚቴ ብዙም ሳይቆይ በህመም ምክንያት ሱዳን ሂዶ 1975 ዓ.ም የተመለሰው ።የነዚህን ስም ዝርዝር ያስቀመጥኩበት ካለ ምክንያት አይደለም ፤በአማራው በትግሬው ፤ በአማራው የዘር ማፅዳት ከባድ ወንጀል ፈፅመዋል ፤አማራው ያፈራው ሃብት ንብረት ወ.ዘ.ተ. መርፌም ሳትቀር ለህ.ወ.ሓ.ት ውርስ ብለው የህዝብ ሃብት ንብረት የዘረፉ የአማራው ህዝብ የገደሉ ፤ የግድያውም ቀንደኛ ተባባሪዎችን ፈፃሚዎች የነበሩ ናቸው ።

እነዚህ ተሰባስበው ነው በንጹሃን ዜጎች ላይ እልቂትና ሶቆቃ እያደረሱ የመጡ ፤ ስለዚህ ከአምስቱ ፖሊት ቢሮ ስድስተኛው መለስ ዜናዊ አብረው የሚጠየቁ የሚከሰሱ ናቸው ። የሰሜን ጎንደር ህዝብ በአረጋዊ በርሄ የሚመራው የህ.ወ.ሓ.ት ሰራዊት ቀሪው አራቱ ፖሊት ቢሮ በየቦታው ተሰማርተው ተዛዝና አመራር በምስጠት ማእከላ ኮሚቴውም የበልጥ በዘር ማጥፋቱ የተሰማሩ ፤ 1 አዋአሎም ወልዱ 2 ስየ አብርሃ 3 መለስ ዜናዊ ከስየ አብርሃ ተደራቢ በመሆን 4 ዘራይ አስገዶም 5 ፃድቃን ገብረ ተንሳይ 6 ገብሩ አስራት 7 አርከብ እቁባይ 8 አስፍሃ ሓጎስ እነዚ ደግሞ በየተዋጊው ሰራዊት ተመድበው ተእዛዝ በመጠት በአማራው ላይ ጥቃት በመክፈት የአማራ የዘር ማጥፋት ከባድ እርምጃ ነዋሪው አማራ ሊቋቋመው በማችል ሁኔታ ሰላማዊው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ዘሩን ለማጥፋት ያለው የሌው ሃይላቸው አጠናክረው የህ.ወ.ሓ.ት. መሪዎች ማለት 1 አረጋዊ በርሄ 2 ግደይ ዘራጽዮን 3 ስብሃት ነጋ 4 አባይ ጸሃየ 5 ሥዩም መስፍን 6 መለስ ዜናዊ በሰሜን ጎንደር አማራ በትንሹ ከ 1969 ዓ.ም. የጀመረው ጥቃት በክፉ መልኩ ተጠናክሮ ከታህሣስ ወ 1972 ዓ. ም.የተጀመረው የአማራ የዘር ማጥፋት ዘመቻ እስከ 1977 ዓ .ም .በዋናነት ወንጀሉ የዘር ማጥፋት በአማራው የፈጸሙ ዋናዎቹ እነዚህ ናቸው ።

በዚሁ የወያኔ ጥቃት ከ2 ሚልዮን በላይ ነብሰ ጡር አራስ ህፃናት ሽማግሌዎች ወጣቶች ወንድ ሴት ልዩነት በሌለው በወያኔ እጅ ተገድለዋል ፤ አገዳደሉም ንበተለያየ ዘዴ ተፈጽሞባቸውል ፤ቀሪው ለስደት ተዳረግ ፤የመጣ ይምጣ ከቤትየ ወጥቸ አልንገላታም ያለም አለ ። ከማ.ገ.ብ.ት ምስረታ እስከ የካቲት ወር 1967 ዓ.ም. የማገብት ሊቀ መንበር ፤ ቀጥሎም በትግሉ ሜዳ ከየካቲት ወ ር 11 ቀን 1967 ዓ.ም እስከ የካቲት ወር 1971 ዓ፣ም ሊቀ መንበርና ወታደራዊ አዛዥ የነበረው አረጋዊ ነው። በምን ምክንያት ሊቀ መንበርነቱን ለቀቀ ለሚል ጥያቄ አጭር መልስ ። አረጋዊ በርሄ ስብሃት ነጋ መለስ ዜናዊ ገና ጉባኤው ሳይገባ ሶስቱ እየተደበቁ ያደረጉት ስምምነት ነበራቸው ።

ድርጅቱን በሞኖፖል ለመቆጣጠር የሚያስችላቸው ሶስቱን የተስማሙበት አረጋዊ ሊቀመንበርነቱን ለስብሃት ነጋ ሊሰጠው አረጋዊ በወታደራዊ አዛዥነቱ እንዲወሰን መለስ ዜናዊ የማርክሲስት ሌኒንስት ፤ በሌኒናዊ መርህ ግብር የካድሬዎች አሰልጣኝና አደራጅ ኮሚሽን እንዲሆን በተስማሙት መሰረት 1ኛው ጉባኤው ተካሂዶ 15 አመርር ተመርጠው የሥራአስፈፃሚው ምርጫ በሚመረጥበት ጊዜ በሁሉም በሙሉ ድምጽ የተመረጠው አረጋዊ በርሄ የህ.ወ.ሓኣዓ.ት ሊቀመንበር ሲመረጥ ብሞትም አልቀበልም ስብሃት ነጋ ነው ብቁ ለሱ ይስጠው ብሎ አንገቱን ለካር አለ፤ የተመረጡ አመራር ስብሃት ለዚሁ ብቃት የለውም እባክህ ተቀበለን ቢሉቱም በፍፁም አልቀበልም በማለቱ ለስብሃት ነጋ ሰጡት መለስ የተሰጠው ቦታ አደላድሎ ያዘ አረጋዊም ድሮም የራሱ የነበረው ወታደራዊ አዛዥነቱን ያዘ ፤ቀሪው በየቦታው ተደላደለ ።በአጭሩ ነው የገለፅኩት እንጂ ብዙ ታሪክ አለው ፤ለወደፊቱ ራሱን በቻለ አረእስት ለህዝብ አሳውቃለሁ ፤ለአሁኑ ይህ ይበቃል ። አረጋዊ በርሄ ደግሞ በታጋዩ እንዲጠላ እንዲናቅ ያደረገው ዋናው ይህ ነው ። ስብሃት ነጋ ማለት ኸምሮው የዞሮበት ደፍድፍ ደንቆሮ ገዳይ ጨካኝ አውሬ ነው ።

ህወሓት ከኢህአፓ ጦርነት ስለአጋጠመው ደፍሮ ሰሜን ጎንደር ሕዝብ ለማጥቃት ሁኔታውና ጊዜው አልፈቀደለትም ነበር። ከኢህአፓ ጋር በተካሄደው ጦርነት ኢህአፓ ጥቃት ደርሶበት ሴሜን ጎንደርን ለቆ በመውጣቱ ምክያት ህወሓት በአረጋዊ በርሄ ወታደራዊ አዛዥ የሚመራው የወያኔ ሰራዊት ጠቅላላ ወልቃይት ጠገዴ፣ ጠለምት( 'ሰሜን ጎንደር') በመውረር ከፍተኛ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈጸመ። ስብሃት ነጋ፣ ግደይ ዘርአጽዮን፣ አባይ ፀሀየ፣ ስየ አብርሃ፣ ስዩም መስፍን መለስ ዜናዊ እነዚህ አመራር ሰዎች የወያኔው ሰራዊት ተከፋፍለው በመያዝ ሰሜን ጎንደር የንጹሃን ዜጎች አማራ የሬሳ ክምር መሬት አደረጉት። እነዚህ ሁሉ አመራር በቀጥታ ትእዛዝ የሚቀበሉት፣ የሚንቀሳቀሱት፣ ጥቃት የሚፈጽሙበት ቦታዎች ከአረጋዊ በርሄ በሚሰጣቸው መመሪያ ነበር።

በዚሁ ጊዜም ተጨማሪ (06) ሃለዋ ወያነ በስፋት እንዲዘጋጁ አመራሩ ስላመነበት በምክትል ሊቀመንበሩ ቁጥጥር እንዲዘጋጅ ፣ ምክትል ሊቀመንበሩ ግደይ ዘርአጽዮን ተጨማሪ ሃለዋ ወያን ከመሬት በታች 1 2 ሜትር ጥልቀት ትንሽ ጠባብ መስኮት 150 እስከ 200 እስረኞች የሚይዙ ሆነው እንዲሰሩ ወስኖ የነበሩትም እንዲሰፉ አድርጎ አሰራው ።

የሚሰሩበትም ቦታዎቹም ፣ ግህነብ ( ቃሌማ )፣ ፍየል ውሃ፣ ባኸላ ሳምረ፣ ሱር እስር ቤት ሲሆን፣ እንዲሰፋ አዲ በቅሎ፣ ወርዒን ፃኢ ጨምሮ በስፋትና በብዛት ከመሬት በታች ሃለዋ ወያኔ ተሰሩ። በዚሁ ጊዜ አማራዎች፣ ሽማግሌ፣ ወጣት፣ ህፃን፣ ሴት፣ ወንድ ሳይለዩ ወደነዚህ ሃለዋ ወያኔ እየታፈሱ ታጋዙ። እዛው እንደገበም በተለያዩ የጭካኔ ግፍ ተገደሉ። በጢስ እየታፈኑ የሞቱት አማራዎች ብዙ ናቸው። በጅላ ጉድጓድ በጥይት እየተደበደበ ያለቀው አማራ ብዙ ነው። ወህኒ ቤት በገባው ተላላፊ በሽታ፣ ኮሌራን ሌላ በሽታዎች በመተላለፍ ሕዝብ አለቀ። በቶርቸር በመርዝ በእሳት የጋለ በረት ወደ ሆዱ በመክተት አሰቃይተው ንጹህ ኢትዮጵያዊ ዜጋ አጠፉት ።

የህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች በአማራው ያልፈጸሙት ግፍ የለም ። እነዚ አረሜኔ ግፈኞች በአንድ ህዝብ ላይ አማራ ጠላታች ብለው የዘር ማጥፋት ዘመቻ አካሂደዋል የሞተም በሂወት ያሉትና የሞቱትም እንደነ መለስ ዜናዊ በከባድ ወንጀል 1 ዘር በማጥፋት 2 ሃገር ለባእዳን መሸጥ (ለሱዳን ) 3 የመሬት ወረራ መፈጸም (ሰሜን ጎንደር ሰሜን ወሎ ) የታላቅዋን ዲሞክራቲክ ሪፓብሊክ የትግራይ መንግሥት ማስፋት የሌላው ክፍለ ሃገር ለምና ሰፊ መሬት በመንጠቅ የህዝቡ ማንነት ባህሉ ወጉ ፀረ ዲሞክራሲ ፀረ ህልውና በመሆኑ ከባድ የወንጀል ተግባር ነው ። አሁንም ህ.ወ.ሓ.ት በዚሁ እየቀጠለበት ሲሆን እንዲያውም በከፋ መልኩ በግማሹ ወደ ትግራይ በማካለል ግማሹ ለሱዳን መንግሥት በመሸጥ በአማራው ላይ የሚፈጸመው ግፍ ወያኔው አባብሶታል ። በአማራው እየተፈጸመ ያለው ግፍ አማራን ብቻ የሚመለከት አይደለም የሁሉ ኢትዮጵያዊ ጥቃት ነው ፤ አማራው ዘሩ ሲጠፋ አማራው ብቻ አይደለም ዘሩ የሚጠፋው ያለ ሁሉ ኢትዮጵያው ነው ዘሩ የሚጠፋ ያለው ፤የጎንደር ለምና ሰፊ መሬት ለሱዳን እየተሸጠ ያለው የጎንደር ብቻ አይደለም የሁሉ ኢትዮጵያዊ ነው የኢትዮጵያ ባለታሪክ ቦታዎች ቴድሮስ በመቅደላ ዮሃንስ በመተማ እምቢ ለጠላት ብለው የተሰዉበት መሬት ወያኔ

ለኢትዮጵያ ዝህብ ጠላት ለሆነው የሱዳን መንግሥት አሳልፎ መሸጥ ታሪካችንም አሳልፎ እየሸጠው የገኛል ፤ስለሆነም የጎደር ህዝባዊ ትግል የሁሉ ኢትዮጵያዊ ተልም ነው ፤አብረን ተባብረን የምንታገልበትም ጊዜው አሁን ነው ። ጎንደርና ትግራይ ፤ጎንደርና ሲዳሞ ፤ ጎንደርና ሓረር ፤ ጎንደርና አፋር ፤ ዶንደርና አኦጋዴን ፤ ጎንደርና ጋምቤላ ፤ ወ.ዘ.ተ ምንም ልዩነት የለንም ፤ሁላችን የኢትዮጵያልጆች ነን ፤ ኢትዮጵያ የሁላችን ሃገር መመክያ ናት ፤ሁላችን ሃገራችን ከወያኔው ፋሽሽት ስርአት ከሃዲ ባንዳ ተባብረን ኢትዮጵያን እናድን ። የወልቃይት ፤ ጠገዴ ፤ጠለምት ፤ሌላውም አማራ በህ.ወ.ሓ.ት. ፤የወረደበት ከባድ የጥቃት ዘመቻ በዝምታ ወይም እየተገደለ አልቀረም ፤ተወልዶ ያደገበት የትውልድ ቦታው ስለሆነ መግቢያው መውጫው ስለሚያውቀው ፤መሳሪያ ያለው ታጥቆ ፤የሌለው በቤቱ ያገኘው ጎራዴ ፤ፋስ ፤ ገጀራ ፤ወ.ዘ.ተ. እናቶች ወጣት ሴቶች ወንድም ሳይቀር በርበሬ በመያዝ ወያኔን በሚገባ በሁሉ አቅማቸው ገድለዉታል አጥቅተዋል ፤በአንዳንድ ቦታዎችም ሙሉ በሙሉ ለማለት የሚቻለው የወያኔ ሠራዊት ደምሠዉታል ፤የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ በታሪክ የተመሰከረለት አርበኛ ተዋጊ ፤ሙሉ ወኔ ያለው ህዝብ ከመሆኑ የተነሳ ከ 1972 ዓ.ም. ጀምሮ ወያኔ ህ.ወ.ሓ.ት.እንደፈለገው ኢትዮጵያን እንዲያፈርስ ህዝብ ሊበታትን በደም ሊያቃባ እድል አልሰጠዉም ፤የወልቃይት፤ ጠገዴ ፤ጠለምት ህዝብ ቆለኛም ደገኛም ህዝብ ነው ፤የመሬቱ ነፋስ የተስማማ ከመሆኑ የተነሳ ወያኔ ይህ ህዝብ በቀላሉ ሊያጠቃው ጠራርጎ ሊያባርረው አልቻለም ።ሌላው አማራ ቶሎ ብሎ በመቻኮል ወደ በቀል አርምጃ አይሽጋገርም ፤ከተነሳ ግን ወደ ኋላ አይታጠፍም ፤በአማራ ጥርስ የገባ ጠላት የመጨረሻ እጣ ፈንታው ውድቀት ምርኮ ናት ።

አማራ ለኢትዮጵያ አንድነት ለኢትዮጵያ ሏላዊነት ዋልታና ማገር ፤ ፤የሃገሩ ድንበር በመጠበቅ ፤ የእስልምና ፤የክርስትና ሃይማናት ባለቤት በመሆኑም እነዚህ ሁሉ ተዳምረው በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ ህዝብ ፤ በባንዴራው አረንጓዴ ፤ብጫ፤ቀይ የሚኮራ ህዝብ ነው ፤ይህ አማራ የሚባለው ህዝብ ዘሩን ካልጣፋ ኢትዮጵያ የምትባል ሃገር በአፄ ምኒሊክ የተፈጠረች ከተፈጠረችም ከ 100 ዓመት ያነሰ ዕድሜ ታሪክ አልባ ሃገር ከዓለም ካርታ ለመፋቅ አይቻልም ፤ብሎ የተነሳው የባእዳን ቅጥረኛ ባንዳ ወያኔ ፤የአማራው ወኔ ጥንካሬ ጀግንነት አይቶታል አሁን እያየው ነው ።

ህ.ወ.ሓ.ት አማራውን ሲያጠቃ አብሮም የተጠቃው የኢትዮጵያ ተዋህዶ ክርስትናም ነው ፤ ቀደም ሲል ብ 1971 ዓ ም በአኩሱም አውራጃ እንዳባ ጴንጦሌን (ብዙ አክሱማዊም እንዳባ ፍሬሚናጦስ ) እያለ የሚጠራው ከአክሱም ከተማ የ 5 ኪሎሜትር ርቀት ያለው አካባቢው የሚጠራበት ስም ደግሞ እንዳየሱስ በተባለው ቦታ ጥንታዊው ገዳም እንዳ አባ ጴንጦለን ብዙ ጥንታዊ ቅርሶች ብዙ ጥንታዊ የታሪክ መጻህፍት ጥንታዊ የብራና ጽሁፎች የሚገኝበት ገዳም ለመዝረፍ ህ.ወ.ሓ.ት በሰነዘረው ጥቃት ሳይሳካለት ቀረ ፤ቀጥሎም በአድዋ ውስጥ የሚገኘው እንዳሥላሴ ገዳም ቢሞክርም አልተሳካለትም ይህ ኦፐረሽን የተመራው በአረጋዊ በርሄ ነበር ፤ቀጥሎ ወያኔ የዘመተው ወደ ዋልድባ ገዳም ፤ በዚሁ ገዳም ተልእኮው ሙሉ ለሙሉ ተሳካለት በህ.ወ..ሓ.ቱ ሊቀ መንበር ስብሃት ነጋና በህ.ወ.ሓ.ቱ ም/ሊቀመንበር ግደይ ዘራጽዮን መሪነት ዋልድባ ገዳም ሙሉ በሙሉ ተዘርፈዋል በዙ ብጿአን ባህታውያን፤ ቀሳውስት፤ አባዎች ተገድለዋል ታሪካዊ ቅርሶች መጻህፍት ብራናዎች ሃብቱ ንብረቱ ወ.ዘ.ተ. ተዘርፈዋል አሁንም ዋልድባ ገዳም እየተጠቃ ይገኛል ባለታሪክ ጥንታዊ ገዳም እየወደመ ለህልፈቱም ገደል አፋፍ ነው ያለው ፤ ይህ ገዳም አማራን ብቻ አይመለከትም የሁሉ ኢትዮጵያዊ ነው ፤ ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይና ዋልድባ ገዳም በሚል ርእስ ለሁሉ ኢትዮጵያዊ ስለ አሰራጨሁት የዚሁ ቅዱስ ዋልድባ ገዳም በህ.ወ.ሓ.ት. የደረሰበትና እየደረሰበት ያለው ጥቃት በዝርዝር ስለፃፍኩት ጽሁፉ በየዌብ ሳይቱ ስለሚገኝ እዛው ፈልገን እንመልከት ።

በአማራው የተፈጸመው አሰቃቂ ጥቃት ደግሞ ከሁሉ የከፋ በአርከበ እቁባይ፣ ዘርአይ አስገዶም፣ ሳሞራ የኑስ፣ ታደሰ ወረደ፣ ሃየሎም አርአያ ወዘተ የሚመሩ የገዳይ ቡድን ሕዝቡን እየሰበሰቡ በሳር ቤት ውስጥ በማስገብት ቤቱን በእሳት በማቃጠል ያለቅው ሰው ቁጥር ብዙ ነው። እኔ ራሴ ያየሁት አርከብ እቁባይ 12 ቤተሰቦችን ሰብስቦ በገዛ ቤታቸው፣ አባት፣ እናት፣ ልጆች፣ የተዳሩ ሴቶች ልጆቻቸውን ጨምሮ ከነህፃናቱ ሰብስቦ ሳር ቤት አዳራሽ አስገብቶና ቤቱን ዘግቶ እሳት ለቀቀባቸው። ሁሉም ቤተሰብ በእሳቱ አለቁ። በዚሁ በሰሜን ጎንደር የተካሄደው የዘር ማጥፋት ወንጀል በተጨማሪ ሁሉም ንብረታቸው ሃብታቸው፣ በሬ፣ ላም፣ ፍየል፣ በግ፣ አጋሰስ ጠቅላላ የቤት እንሣት ሁሉ በህወሓት ተዘርፈው ተወርሰው ተወሰደዋል ።

ከ 1972 ዓ.ም. ታህሳስ ወር ይህ ሁሉ ጥቃት የተጀመረው አጠቃላይ የጠገዴ፣ ጠለምት፣ ወልቃይት አማራ ዘሩ ሲጠፋ ቀሪው ደግሞ ወደ ሱዳን ተሰደደ፤ ጫካ ውስጥ ገብቶ ፀረ ወያኔ በሽምቅ ውጊያም የተሰማራ ጥቂ ልነበረም፤ ህዝብም ባገኘው መንገድ ሁሉ ወያኔን ከማጥቃት አላቆመም ፤ የወልቃይት ፤ጠገዴ ፤ ጠለምት ፤ ሴቶች በርበሬ በትንሽ ከረጢት

ቋጥረው ከወገባቸው አትለይም በቤታቸው ውስጥም የተዘጋጀ አለ የወያኔ ታጋይ በመንገድ ሲገኙት አቁመው ለማነጋገር በመሰለ መልኩ ከያዝዋት በርበሬ ዘግነው በማውጣት አይኑ ላይ በመርጨት እዛው ሲደናበር መሣሪያ ማርከው ብዙ የወያኔ ታጋይ ገድለዋል፤ወደ ቤታቸው የሚመጣ ታጋይ ምበርበሬ በውሃ በጥብጠው የሚበላ የሚጠጣ አቅርበው ደህና ነው ብሎ ሆዱን ሲሞላ ፤የበጠበጡት በርበሬ አይኑ ላይ በመድፋት የታጠቀው መሳሪያ ማርከው ታጋዩም በድምፅ አልባ መሳሪያ ይገድሉታ በዚሁም ተገድሎ የጠፋ የወያኔ ታጋይ ብዙ ነው ።

በ 1973 ዓ.ም . በተለያየ መንገድ የተገደሉ ከማስታውሳቸው ውስጥ ፤ በህዝብ ግኙኝነት የነበሩት ፤ አለማየሁ ፤ ብርሃነ ፤ ፍስሃ ፤ገብረተንሳይ ፤ ነጋሽ ፤ አማረ ፤ ደስታ ; ብዙ ተገድለዋል የጠቀስኩት ከማውቃቸው ነው ።በወያኔ ታጋይ ሰራዊትም በተለያዩ መንገዶች በህዝቡ የተገደሉም ብዙ ናቸው ከማስታውሳቸው ለመጥቀስ ገብረ ሥላሰ ፤በላይ ፤ ፍጹም ፤ካህሳይ ፤ ነጋሽ ፤ ገረግዚሄር ፤ አባይ ፤ አበበ ፤ ጸጋይ ፤ የሚባሉ ህዝቡን ለመግደል በቡድን በቡድን ተከፋፍለው ሲንቀሳቀሱ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብም በየጫካው ተደብቆ በማድፈጥ የገደላቸው እነዚህን አስታውሳለሁ። የወልቃይት ፤ጠገዴ ፤ጠለምት ህዝብ የሚቻለው ሁሉ አቅሙ በፈቀደለት መጠን ህ.ወ.ሓ.ት. ወያኔን ከማጥቃት ባለው መሣሪያ እየተጠቀመ ወደ ኋላ ሳይል ጀግንነቱን ያስመሰከረ ፤ያሳየ ህዝብ ነው ። እኔ ባለኝ እምነት ይህ ኩሩ ጀግና ህዝብ ከወያኔ ፋሽሽት ቅኝ ገዢ አረሜኔ ስርአት እየታገለ የመጣው ያለኝ እምነት እውነትም የኢትዮጵያ መድህን ጠባቂም ነው ። ተስፋ ሳቆርጥ ከ 1972 ዓ ም . አንስቶ እስከ ዛሬዋ ዕለት የማንነት ጥያቄው አድማሱን በማስፋት ወያኔ በማጥቃት ተሰማርቶ ይገኛል። በመሬቴ ላይ እሞታለሁ እንጂ ትወልድ ቦታየ አለቀም ያለው በ 1969 ግንቦት ወር የተጀመረው ጥቃት እስከ ዛሬ ድረስ ቀጥሏል።

ይህ የሰሜን ጎንደር ህዝብ በወያኔ እየሞተ እየተገደለ ማንነቴን አሳልፌ አልሰጥም ብሎ 42 ዓመት ሙሉ ከተሓህት-ህወሓት ዘራችንም ብታጠፉ አንድ ሰወ እስኪ ቀር ማንነታችን አሳልፈን አንሰጥም እኛ አማራ ጎንደሬች እንጂ ትግሬዎች አይደለንም ብሎ እስከ አሁን ድረስ በማንነቱ የማይደራደር ማንነቱን አሳልፎ የማይሰጥ ኩሩ ኢትዮጵያዊ አማራ ነው ። በምሬት እየታገለ የሚገኝ የጎንደሩ ህዝብ ከቀን ወደ ቀን ጥንካሬው በግልጽ እይታየ ነው ። የአማራው ህዝብ በየትም ቦታ የተገኘ አማራ እንዲ ገደል ያወጀው ህ.ወ.ሓ.ት. በ 1969 ሲሆን፣ በትግራይ ውስጥ የሚኖሩ አማራዎችም ከየቦታው እየተለቀሙ እንዲገደሉ አምስቱ የተሓህት አመራሮች፣ አረጋዊ በርሄ፣ ሊቀመንበር፣ ግደይ ዘርአጽዮን፣ የድርጅቱ ም/ሊቀመንበር፣ አባይ ፀሃየ፣ ስዩም መስፈን፣ ስብሃት ነጋ፣ ትግራይ የትግራዮች እንጂ የሌላው መጤ ቦታ አይደለችም፣ ስለሆነም ማንም የትግራይ ተወላጅ ያልሆነ ከትግራይ ይውጣ ተብሎ ታወጀ። በአዋጁ መሰረትም አማራው በነቂስ እየተፈለገ ተገደለ፣ እነዚህ ይህ ውሳኔ የተላለፈባቸው ከትግራይ ተጋብተው ልጆች ወልደው ያሳደጉም ናቸው ፤ ያመለጠውም ሂወቱና ቤተ ስቦቹን ይዞ የሸሸም ብዙ ነው ።ይህ የተመለከተና ያየ የትግራይ ህዝብም ፤ወያኔን አወገዘ ፤መሬታቸው ነው አይወጡም ይህ የኢትዮጵያ ቦታ ነው ፤ማነው ወጪ ማነውስ አስወጪ ፤ከፈለጋቹህ ወያኔዎች ውጡ እያለ ከአማራው ወንድሙ ቆመ ። በየቦትው ፀረ ወያኔ እንቅስቃሴ ተነሳ ፤ወያኔም በየ ቦታው ፤ ይህ እንቅስቃሴ የታዩባቸው በህዝብ ግኙኝነቱ በፀረ ወያኔ ፖሊሲ ተንቀሳቅሰዋል ያላቸው የትግራይ ሰዎች አንድ በአንድ እየለቀመ ሓለዋ ወያነ በማስገባት ደብዛቸው አጠፉቸው ፤ጠፍተዉም ቀሩ ።

ተሓህት-ህወሓት ይህን ሁሉ በሰሜን ጎንደር አማራው ህብርተሰብ ላይ ይህን ሁሉ ግፍ ሲፈጽም እጃቸውን ለወያኔ የሰጡ የኢህአፓ አባላት የነበሩ፤ ታምራት ላይኔ፣ አዲሱ ለገሰ፣ ተፈራ ዋልዋ፣ በረከት ስምኦን፣ ዮሴፍ ረታ፣ መለስ ጥላሁን፣ ህላዊ ዮሴፍ፣ ታደሰ ካሳ፣ ሙሉአለም አበበ፣ ወዘተ ይገኙበታል። ከወያኔ ህወሓት በመተባባር የሰሜን ጎንደር፣ ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምት ወዘተ።የቀድሞዎቹ ኢ.ህ.ዴ.ን በህ.ወ.ሓ.ት አምሳልና ቡራኬ ተጠፍጥፈው የተሰሩ ተላላኪዎች የዛሬዎቹ ብአዴን አካባቢው ለብዙ ጊዜ የቆዩበትና የሚመሩበት ስለነበሩ ሕዝቡን በነቂስ ስለሚያውቁት አካባቢ እየመሩ ለወያኔ ጥቃትና የዘር ማጥፋት ወንጀልም ተባባሪ ሆነዋል። ወያኔን እየመሩ የሰሜን ጎንደሬውን አማራ አጥቅተውታል። ስለሆነም በማራው ላይ የደረሰው የዘር ማጥፋት ወንጀል በተለያዩ የጥቃት ዘዴዎች በህወሓት የተፈጸመው እነዚህ የብአዴን አመራር ከህወሓት አመራር ጋር አብረው ተጠያቂ ናቸው።

ሕዝብ ላይ ለሚደርሰው ጥቃት ፤ሃብት ንብረት ዘረፋ ፤ለሚደርሰው ማንገላታትስላማዊ ዜጋው ተይዞ ለእስር የሚዳረገው በሕዝብ ግንኙነት በኩል ጥናትና ሪፖርት ነው ። መኮንን ዘለለው ለመጀመሪያ ጊዜ በህ.ወ.ሓ.ት በኩል ወደ ወልቃይት ጠገዴ የተሰማራው እሱ ነበር የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ግን አልተቀበለውም ሪፖርቱ ሲያስተላልፍም ሁሉም ፀረ ተ.ሓ.ህ.ት. ህ.ወ.ሓ.ት ናቸው በማለት ከነስም ዝርዝራቸው ለወያኔ ፖሊት ቢሮ ከ 100 በላይ ሰዎች ሴቶችም አሉበት

ቀስ በቀስ አንድ በአንድ ብስራት አማረ በሚመራው አፋኝ ቡድን ተለቅመው በቡምበትና ሱር ሓለዋ ወያነ ገብተው ጠፍተዋል ፤ንብረታቸውም ሙሉ በሙሉ በወያኔ ተዝርፎ ባዶ ቤት ቀረ ። የዚህ ሁሉ ተጠያቂው ስንመለከት፣ መኮንን ዘለለው ነው፣በዚህም ላይ የሚጠየቁ መረሳ ረዳ፣ አጽብሃ ሃይለማሪያም፣ ፀጋይ በርሄ(ሃለቃ)፣ መኮንን የአዲረመጽ ሕዝብ ግንኙነት፣ አርአያ ወ/ቅነህ፣ ቅዱሳን ነጋ፣ ቀሺ ታደሰ፣ መሃሪ ግብርገርግስ ሃለቃ ታደለ አለምሰገድ ፤ሙብራት በየነ ፤ ወዘት። እነዚህም አንኳር ተጠያቂ ናቸው።

የህ.ወ.ሓ.ት.ፕሮግራም ተሓህት-ህወሓት ገና ደደቢት በርሃ ከመውረዱ በፊት ማ.ገ.ብ.ት. ማሕበር ገስገስቲ ብሄረ ትግራይ እየተባለ በሚጠራበት ጊዜ አዲስ አበባ ውስጥ ሆኖ ይጥቅሙኛል በሚላቸው ተግባራት ቢንቀሳቀስም ብዋናነት ሥራው ግን የትግሉ ፕሮግራም ወይም የትግል አቋሙን ፖሊሲ ማዘጋጀት ነበር ። ከማ.ገ.ብ.ት. መስራቶቹ ውስጥ በቂ እውቀትና ችሎታ በትምህርቱም ከፍተኛ ደረጃ በሳል እውቀትና ችሎታም ያለው አረጋዊ በርሄ ብቻ ነው። ስድስቱን ሰዎች ሰባተኛው ራሱ አሰባስቦ ማ.ገ.ብ.ት. የፈጠረም እሱ ነው ። በዚሁ የተሰባሰቡ ጓደኞቹ በእውቀትም በችሎታም አንፃራዊ ናቸው ፤ ሁሉም የማ.ገ.ብ.ት. ሥራን ሃላፊነትም እንዲመራ የመረጡት አረጋዊ በርሄን ነው ፤በዚሁ መሰረት 1 የፐሮግራሙ ንድፈ ሃሳብ ማዘጋጀት 2 የውጭ ሃገር መንግስታት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ኢምባሲም ይሁን ቆንስላ እየተገናኘ ድጋፍ ማሰባሰ እውቅናና ተቀባይነት ማግኘት የመሳሰሉ ስራዎች በሱ ብቻ ነበር የሚሰሩ ፤። የፐሮግራሙ ዝግጅት የተጀመረውን ገና ማህበር ገስገስቲ ብሄረ ትግራይ (ማገብት) ተብሎ መስከረም ወር 1967 እንደተመሰረተ።

መስራቶቹም ፣ አረጋዊ በርሄ፣ ሊቀመንበር፣ ግደይ ዘርአጽዮን፣ ም/ሊቀመንበር፣ አባይ ፀሃየ፣ ፣ ስዩም መስፍን፣ ፣ ዘርኡ ገሰሰ፣ አስፍሃ ሃጎስ፣ ሃይሉ መንገሻ. ተሰብስበው ማ.ገ.ብ.ት እንደመሰረቱ የሥራ ክፍፍልም አደረጉ ሲያደርጉ በዋና ሃላፊነት አረጋዊ በርሀ ፕሮግራሙን በማርቀቅና በማዘጋጀት ሥራውን ቀጠለ። በዚሁም ተጨማሪ በኢትዮጵያ የሚገኙ የጥንት ጠላቶች ኤምባሲም ሆነ ቆንስላ እየተንቀሳቀሰ የትግራይ ሕዝብ በቅኝ አገዛዝ በአማራው መንግሥት በአሰቃቂ ኑሮ ላይ ሰለሚገኝ ታግለን ትግራይን ከአማራው ቅኝ ( ኢትዮጵያ ) አገዛዝ በትግል ነፃነታችንን ካልተጎናጸፍን የትግራይ ሕዝብ የወደፊት እጣ ተበታትኖ መቅረት ስለሆነ የናንተን እርዳታ እንፈልጋለን ብሎ መማጸኑን ሥራየ ብሎ ተያያዘው። ይህ ሰው ከደረሰባቸው ኤምባሲዎች፣ ቆንስላ ውስጥ፣ ከሱዳን፣ ግብጽ፣ ጣልያን፣ ሊቢያ፣ ኢራቅ፣ ሶሪያ፤ሶማሊ ( መቃድሾ ) ጎልተው ከሚጠቀሱ እየተዘዋወረ የተስፋ ይሁንታ በማግኘት ትንሽ ገንዘብ ሲለቅም በዋናነት ፕሮግራማችሁን አሳዩን፣ በረሃ ወርዳችሁም ትግል ስትጀምሩ እንከታተላለን፤ በዚያን ጊዜም በትጥቅና በገንዘብም ጭምር እንረዳለን እያሉ የቃላት ተስፋ ሲገቡላቸው እንደነበር ይታወቃል በትግሉ ጊዜም የህ.ወ.ሓ.ት. ተስፋ በነዚህ የዓረብ ሃገራት ነበር ትልቁ ተስፋው ከ 1967 ዓ.ም የገቡበት ቃልም አላጠፉም በድብቅ በግልፅም እየረዱ የመጡ ናቸው ።

ይህ በዚህ እንዳለ ደደቢት በረሃ እንደገቡም የተዘጋጀው ፕሮግራም አጠናክረው በማዘጋጀት በመፃፍ፤ የካቲት ወር 1968 ተሓህት በዲማ በጠራው ዲማ ኮንፈረንስ እየተባለ የሚጠራው ፕሮግራሙ ለተሰብሳቢው ቀርቦ ፤ የነበረው ታጋይ ፕሮግራሙን አውገዘው ይህ ፕሮግራም ፀረ ኢትዮጵያ ሏላዊነት ፀረ ህዝብ አንድነት ነው ፤ትግራይ ከ/ሃገር በአክሱም ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ መናገሻ ዋና ከትማ ፤የኢትዮጵያ የታሪክ ማእከል ናት ከየት የመጣ በምን መልኩ ነው የኢትዮጵያ ቅኝ ተገዥ የሆነችው ፤ ስለ ኤርትራ የምትናገሩት ኤርትራ ም የኢትዮጵያ ግዛት ናት ፤ ወልቃይት ጠገዴ የጎንደር አልወሃ ምላሽ የወሎ ነው በማለት ይህ ፕሮግራም አንቀበለውም ሲል ታጋዩ ።

ነገር ግን በትእቢትና በአምባገነናዊ ትምክህት በሊቀመንበሩ አረጋዊ በርሄና ጥቂት ተባባሪዎቹ ፀድቋዋል አልፈዋል በማለት ለሕዝብ በተነው። ዘሬ ይህ በአረጋዊ በርሄ የተዘጋጀው ፕሮግራም የኢትዮጵያ ሕገ፣መንግሥት በመሆን ኢትዮጵያ አንደነትዋ እየፈረሰ የገኛል። ሕዝብም ኢትዮጵያዊነቱን ተነጥቆ በዘርና ብቋንቋ ተከፍሎ ክልል በሚል ሃረግ ተወስኖ እንዲቀር ቀሰ በቀስ ኢትዮጵያዊነቱን፣ አመለካከቱን፣ አስተሳሰቡን ከማላላቱም በላይ፣ አንድነቱን ያዳከማል፣ በማለት ወያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተብሎ ለብዙ ዘመናት ሲጠራበት የቆየውን 'ሕዝቦች" በሚል የተለያየ ሕዝብ እንደሆነ ገና በማገብት ጊዚያቸው የተጀመረና በፕሮግራሙ ውስጥ የተካተተ መሆኑ በገጽ X (10) ይገኛል።

ክልል የሚለውም በግልጽ ቃሉን ባያስቀምጠውም ብሄር ብሄረሰቦች ተገንጥለው ራሳቸውን በራሳቸው በመወሰን ተገንጥለው የራሳቸውን መንግሥት መመስረት አለባቸው በሚለው ጽንሰ ሃሳብ የተካተተ መሆኑ ለመገንዘብ ፕሮግራሙን እንመልከት። በአሁኑ ጊዜ የሚሰሙ ውሸቶች አሉ ፤በጣም የሚገርመው ግን የአረጋዊ ብርሄ ንግግር ነው ፤ የህ.ወ.ሓ.ት. ፕሮግራም አላዘጋጀሁም በደፈና ራሳቸው ነው ያዘጋጁት ይላል ራሱ በዋናነት ያዘጋጀው የራሱ የእጅ ሁፉ ያለበት

ፕሮግራም እንዴት በግልፅ ለሚታየው ነገር ይካዳል ፤ ሌላው ትግሉን ከጀመርን በስድስት ወራችን እንዲታረም ተብሎ፤ በፅሁፍ ግን ያየነው ለውጥ የለም ይላል ፤የድርግቱ ሊቀመንበር እሱ ራሱ ነው ፤ ፕሮግራሙ ያዘጋጀው ያረቀቀው ራሱ፤ ያፀደቀውም እሱ ራሱ በሚመራው ስብሰባ ፤ፀድቀዋል ብሎ ያሳለፈው እሱ ራሱ ነው ፤ይታረም ከተባለም የድርጅቱ ሊቀ መንበር ሃላፊነት ወስዶ የፖሊት ቢሮ አባሎቹ ሰብስቦ እያወያየ ፕሮግራሙ ይታረማል ታርሞም እንዳዲስ ለጉባኤ ይቀርባል ፤የነበረው ስህተት ተገልፆ ጉባኤተኛውም አስተያየት ሰጦ ሃገርና ህዝብ የሚከላከል ሆኖ ከተገኘ ያፋል ፤ካልሆነም ውድቅ ይደረጋል መሆን ያለበትም ይህ ነው ፤ይህ ሁሉ የአረጋዊ በርሄ ሃላፊነት እንጂ የሌላ አይደለም ምክንያቱ የድርጅቱ መሪ ሊቀ መንበር እሱ ብቻ ነው ።

ይህ የድርጅቱ ፕሮግራም ተራ ሰነድ አይደለም በአንድ ተራ ታጋይ ወይም ማእከላይ ኮሚቴ ወይም በተራ አባል ፖሊት ቢሮ የሚሰራ አይደለም ፤ የድርጅቱ መመሪያ ነው ።አረጋዊ በርሄ የሚናገረው የኢትዮጵያ ህዝብ ንቀት መናቅ ማሳነስ ገና ከልቡ አልተፋቀም ፤የት ይደርሳሉ ወያኒያዊ ትእቢቱ አላስወገደም ።ይህ ሁሉ ተግባርና ሥራ የራሱ ነው የሚያስተካክለው ሌላ የለም ። ትግሉ ከተመሰረተ ጀምሮ እስከ 1977 ዓ.ም ፈላጭ ቆራጭ የነበረው አረጋዊ በርሄ ነው ፤ በህ.ወ.ሓ.ት ድርጅት ውስጥ ካለ አረጋዊ በርሄ ፍቃድ የሚሰራ ነገር የለም ፤ ደፍሮ የሚሰራም የለም ። በማ.ለ.ሊ.ት ምስረታ የመፈንቀለ መንግሥት ባልታሰበው ሁኔታ የደረሰዉም የራሱ ታማኝ ሎሌዎቹ እነ ስብሃት ነጋ መለስ ዜናዊ ስየ አብርሃ አካሄዱበት እሱና አሽከሩ ግደይ ተባረሩ ። ሲባረሩም ምንም የፖሊሲ ልዩነት አልንበራቸውም ስብሃት ነጋም በጉባኤው በማያሻማ መንገድ በጉባኤው በመካከላቸው ልዩነት ሳይፈጠር አብረው መዝለቃቸው በንግግሩ ሲያረጋግጥ ፤ይህ ንግግርም አረጋዊ እና ግደይ ተቀብለዉታል የሰጡት የተቃውሞ ምላሽ የለም ።።፤ሁሉ የህ.ወ.ሓ.ት. መሪዎች ፀረ ኢይዮጵያ ፀረ አንድነት ፀረ ህዝብ ናቸው ። አረጋዊም ሆነ ሌሎቹ ህዝብን እያታለሉ ገበናቸው ወንጀላቸው ሊደብቁ ፈፅሞ አይችሉም ፤። የንፁሃን ደም እየጮኸ ነው ። የኢትዮጵያ ህዝብ እነዚህ ፀረ ሃገርና ፀረ ህዝብ ከሂዲዎች የጠላት መሳሪያ የወያኔ መሪዎች ይዞ ለፍርድ ማቅረብ ግዴታውም ሃላፊነትም የህዝቡ ነው ፤።

የህወሓት ፕሮግራም በኢትዮጵያ ላይ የፈጠረው ችግር//

ፕሮግራሙ ሙሉ በሙሉ ተዘጋጅቶ ይፋ የተደረገው በየካቲት ወር 1968 ነው። ለሕዝብም ተበተነ፣ በትግራይ ሕዝብ ተቀባይነት አላገኘም። የትግራይ ሕዝብ ሙሉ በሙሉ ተቃውሞታል፣ በግልጽም ተናግሯል። ትግራይን ከቅኝ ገዢው አማራ (ኢትዮጵያ) እጅ አስወጥተን ነፃ የትግራይ መንግሥት እንመሰርታለን፣ ትግራይ የኢትዮጵያ አካል አይደለችም፣አፄ ዮሃንስ ከሞቱ ነፃነትዋ ተገፎ በአማራው (ኢትዮጵያ) ቅኝ አገዛዝ ስር የወደቀች ሃገር ናት ብሎ የተነሳው ተሓህት-ህወሓት። ከኢትዮጵያ ሕዝብም መሰረትም ግኑኝነት የለውም። ከዚህ ተነስተው በእነ አረጋዊ በርሄ የሚመራው ድርጅት ዋናው የምስረታ ዓላማው ጸረ-ኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነትፀረ ኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የሆነውን ፕሮግራማቸውን ዘረጉት።የዚሁ ፕሮግራም ምሶሶ ፖሊሲ ትግራይን ገንጥለው የትግራይ መንግሥት ማቋቋም ነው ።ወያኔና የኢትዮጵያ ህዝብ አይገናኙም ።

ወያኔ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛቴ ስር አስገባታለሁ የሚል ህልምም ሆነ ሃሳብ እስከ 1981 አልነበረውም። አጋጣሚ ሆኖ ግን በነበረው የደርግ መንግሥት ዳካማ ስርዓት ኢትዮጵያና ሕዝቧ በወያኔ ቅኝ አገዛዝ እጅ ወደቀች። በዚዜ ይከተሉት የነበረው ፕሮግራም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕገ መንግሥት ስርዓት ሆነ። ለዚህም በምሳሌነት የወያኔን እንኳር የሕገ መንግስት ልጥቀስ፤

1. የመገንጠል መብት ያረጋገጠው በፕሮግራሙ ብሄራዊ ተጽእኖ ገጽ 7 እንመልከት፣ 2. ትግራይ ነፃ ሃገር ነበረች የሚለው በመቅድም 5 እንመልከት፤ የአረጋዊ በርሄ የእጅ ጽሑፍ ። ይህ ፕሮግራም በፀረ አማራ ከመነሻው እስከ መጨረሻው ፀረ አማራ ፕሮግራም ነው፣ 3. የኢትዮጵያን ጥንታዊ የባህር በር ያሳጣት ተሓህት-ህወሓት በፕሮግራሙ የኤርትራ ጥያቄ ለሚለው አርእስቱ ግዛቷን እና የበህር በርም የሰጣት በፕሮግራሙ በገጽ 32 እንመልከት፣አሰብን ሳይቀር ወደ ኤርትራ አጠቃለሉት ።አሰብ አውራጃ የኤርትራ ሳይሆን የወሎ ጠ/ግዛት ክፍልና አውራጃ ነው ፤ በኤትራም ሥር ገብቶ አያውቅም ፤ ይህን ያደረጉበት ዋናው ምክንያት ሆን ብለው ኢትዮጵያን ለሞጉዳትና የባህር በር አልባ እንድትሆን ከኢትዮጵያ ጠላት ባእዳን ሃገራት ተነጋግረው የፈፀሙት ፤ፀረ ኢትዮጵያ ተግባር ነው ። 4. ሕዝቦችና ክልል የሚሉትም የዚህ ፕሮግራም ጽንሰ ሃሳብ ናቸው።

ስለሆነም የተሓህት-ህወሓት ፕሮግራም የኢትዮጵያን አንድነትና ሉአላዊነት፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍቅርና ሰላም የሚንድ ጸረ-ኢትዮጵያ ነው። ለዚህም ተጠያቂዎቹ፣ አርጋዊ በርሄ፣ መለስ ዜናዊ፣ ግደይ ዘርአጽዮን፣ ስብሃት ነጋ፣ ስዩም መስፍን፣ አባይ ፀሃየ፣ ስየ አብርሃና አውአሎም ወልዱ ናቸው። ህወሓት ሰሜን ጎንደርን ብ 1972 በወረረበት ጊዜ፣ በጠቅላላ ለማለት ይቻላል፣ በሬ፣ ላም፣ ፍየል፣ በግ፣ በቅሎ፣ ፈረስ፣ አህያ ከወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምት ወዘተ በመዝረፍና በመውረስ፣ ከ 1973 ጀምሮ ህወሓት የእንስሳ ነጋዴ ሆኖ ነበር። ገበሬዎች እየመለመለ ነጋዴ በመሆን የተሰረቁትን የተዘረፉት እንስሳዎች በትግራይ አውራጃዎች በመሸጥ ገንዘቡ ይህ ነው ተብሎ ባይደነቅበትም ጊዜዊው ችግሩ ይሸፍንለት ነበር ። ሌላው የዚሁ የሰሜን ጎንደር ከሰደትና ከሞት የቀረው የሰበሰበውን እህል በመቀማት ህዝቡ ባዶ ቤት ይዞ የቀረበበት ነው ።

ህወሓት በአማራና በትግራይ ሕዝብ ላይ የፈጸመው ወንጀል በሕግ የሚጠየቅበት ነው። ተገድለዋል፣ ጠፍተዋል፣ ተሰደዋል፣ ንብረታቸው ውርስ ለህ.ወ.ሓ.ት. ተብሎ ተነጥቋል። ዛሬ በሕዝብ ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈጸመ፣እየፈጸመ ያለው የ ህ.ወ.ሓ.ት ፋሽሽት መንግሥት ሕዝብ በአሰቃቂ መንገድ እያንገላታ፣ እየገደለ፣ አፍኖ እያጠፋ፣ የሃገርን ሉአላዊነት እያፈረሰ፣ ከ 1600 ኪ.ሜ. ርዝመትና 100 ኪ.ሜ. ጥልቀት በላይ ያለውን የኢትዮጵያን መሬት በ 1975 ዓ/ም ለሱዳን የሸጠው ጊዝያዊ ጥቅምና እውቅና በሱዳኖች አገኝበታለሁ ብሎ የኢትዮጵያ ሏላዊነት በመፃረር ለምና ታሪካዊ የኢትዮጵያ መሸጥ በከፍተኛ ወንጀል የሚያስጠይቅ ነው ። ምንም በህዝብ አሜኔታ ያልተሰጠው በህዝብ የማይታወቅ የህ.ወ.ሓ.ት የማፍያና የባንዳዎች ስብስብ ፤ የራሱን ፕሮግራም በ 1968 የፃፈው ያዘጋጀው ፤ የትግራይ መንግሥት ለመመስረት ነው ፤ ዛሬ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ሆኖ ይገኛል አድርጎታልም ። ህወሓት ገና ከትግሉ መጀመሪያ ጀምሮ በሕዝብ ላይ ያወረደው ግፍና መከራ ፤ሽብር አሁንም የሚወርደውን ግፈኛው አገዛዝ በባሰ መልኩ ቀጥሎበት ፤መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እያሰቃየ የሚገዛ ያለው በዚሁ ፕሮግራሙ ነው ፤ ስለሆነም ይህ ድርጅት ከአፈጣጠሩ ጀምሮ ሽብርተኛ በሽብርተኛነቱ ተደራጅቶ በግልፅም በስዉር ህዝብ አጥቅተዋል ።

ለዚሁ ምስክርነት የሚጠቅሙ አብነቶች ማንሳት እንችላለ ፤ 1 ኛ ከ 1969 ዓ.ም ግንቦት ወር ጀምሮ ፈዳያን ይህ የአረብኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙም አጥፍቶ ጠፊ ማለት ነው ፤ወደ እንግሊዝኛ ሲተርጎም ደግሞ TERIORRIST ማለት ነው ፤የዚሁ የአጥፍቶ ጠፊ ቡዱኝ መሪ ብስራት አማረ የተባለው ወኝጀለኛ ነው ፤የዚሁ ማስረጃም ፍኖተ ግድል › ብሎ ፀረ ኢትዮጵያ በጻፈው መፅሃፍ ፈዳያን በሱ የሚመራው አጥፍቶ ጠፊ በሰላማዊ ሰዎች የፈጸመው ጥቃት በገፅ 172፤ 173 ፤ በጽሁፍ ማስረጃ በማያሻማ ሁኔታ ገልፆታል ፤መፅሃፉን ፈልገን እንመልከት ።ይህ ደግሞ አንድ ድርጅት ሽብርተኛ የመሆኑ ቀዳሚ ማስረጃ በመሆኑ ተ.ሓ.ህ.ት. ህ.ወ.ሓ.ት. ሽብርተኛ፡ድርጅት ነው ።

2 ኛ ዘር ማጥፋት በአፈና ፤በግድያ ፤በጢስ አፍኖ መግደል ፤በጋለ ብረት ወደ ሆድ እቃው አስገብቶ መግደል ፤በመርዝ በሚጠጣው ውሃ ፤በሚበላው ምግብ ጨምሮ ሰላማዊ ዜጎች መግደል ፤እርቃኑን ወንድ ሴት ከግንድ አጣብቀህ ቀን በጽሃይ ለሊት በብርድ ለ 48 ሳአት አስረህ የሰው ፍጡር ነብስ ማጥፋት ፤በብልቱ 10 ኪሎ ግራም አሸዋ አስረህ ማንጠልጠል ለረጅም ሳአታት በሴትም በጡቶችዋ ማንጠልጠል ፤ወ.ዘ.ተ. እነዚህ ሁሉ የአንድ ሽብርተኛ ተግባራት ናቸው ፤በዚሁ መሰረት ህ.ወ.ሓ.ት. ከአፈጣጠሩም ሽብርተኛ ነው ።እነዚህ የተገለጹ የሽብር ተግባራት በተ.ሓ.ህ.ት. ህ.ወ.ሓ.ት. የተጀመሩት ብ 1969 ዓ.ም. ቡምበት (ሽላሎ )በነበረው ሓለዋ ወያነ በም/ሊቀ መንበሩ በግደይ ዘራጽዮን መሪነት ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆኑ ም/ሊቀ መንበሩ ባለው ሃላፊነትና ሥልጣን መሰረት ጠቅላላ የተ.ሓ.ህ.ት.--ህ.ወ.ሓ ት. ሁሉ ሓለዋ ወያነ (06 ) የምርመራ ስራቸው በዚሁ እንዲሆንም ትእዛዙ በማስተላለፍ የህ.ወ.ሓ.ት. የምርመራ ቶርቸር በዚሁ ቀጠለበት ። 3 ኛ ይህ በብዙ አማራዎች የተፈጸ ነው ፤በተገኘበት ኢጋጣሚ ስል በሆነ ገጀራ አንገቱን ቆርጠህ መጣል ፤ወይ በሳንጃ ሆድ እቃውን በጣጥሰ ገድለህ መጣል የጅብ እራት እንዲሆን ማድረግ ፤ይህ በብዛት የታየበት ቦታ ፍየል ውሃ ውስጥ የሚገኘው ሓለዋ ወያኔ አካባቢ ዓዲበቅሎ በሚገኘው ሓለዋ ወያኔ አካባቢ ሲሆን የዚሁ ዋና ሃላፊው አባይ ጸሃይ ሲሆን መክትሉ ክንፈ ገብረመድህን ነው ።

4 ኛ ፋሽሽት ሽብርተኛው ህ.ወ.ሓ.ት. ግንቦት ወር 1983 ዓ.ም .ኢትዮጵያ ወሮ በቅኝ ግዛቱ ካስገባ ከበረሃ ይዞት በመጣው የአማራው ዘር ማጥፋት በስፋት በመቀጠል በተለያዩ የኢትዮጵያ ግዛት ይኖሩ የነበሩ አማሮች ተወልደው ባደጉበት መሬት ሰፊ የዘር ማጥፋት ወንጀል ሲፈጽም በገደል በመወርወር ፤ቤት ውስጥ ሰብስቦ ቤቱን በእሳት በማቀጣጠል ህዝብ የፈጀ ሴቶች ህፃናት እርግዞች እመጫት ሽማግሌዎች ሁሉ በአሰቃቂ መንገድ ገደላቸው ፤ይህ ድርጊትም የሽብርተኛው ተግባሩ፤ በዓለም ደረጃ ያጋለጠው የህ.ወ.ሓ.ት. ሽብርተኛነት ነው ። 5 ኛ ህ.ወ.ሓ.ት. የአማራው

ዘር ለማጥፋት ያልተጠቀመበት ዘዴ የለም ፤ወጣት ወንድ ሴት ሕክምና እያለ ሲፈልግ የአይን ትራኮማ ሲፈልግ የጀሮ የተለያዩ ምክንያቶች በመስጠት፤ልጅ እንዳይወልዱ የሚከለክል ማምከኛ መድሃኒት በመስጠት በርካታ መሃን ሁነው እንዲቀሩ አድርጎዋል ፤ይህ ከባድ የወንጀል ተግባርም የሽብርተኛ ሥራ ነው ፤በዓለም ደረጃ የተወገዘ ተግባር የሚፈጽም ሽብርተኛ ብቻ ነው ፤ይህም የወያኔ ሽብርተኛነቱን ያጋልጣል ። 6ኛ ወያኔ ህ.ወ.ሓ.ት. ኢትዮጵያን በተቆጣጠረ እንኳን በአዲስ አበባና በጎንደር በወልይታ በተለያዩ ቦታዎች ንጹሃን ኢትዮጵያውያን በለሊት ከየቦታ በማፈን ግድሎ ወንዝ ውስጥ ገድሎ ድልድይ ውስጥ መጣል የተለመደ ሆኖ የመጣበት ጊዜ ነው ዛሬ ለምሳሌ ብንጠቅስ አዲስ አበባ ውስጥ እሪ በከንቱ ድልድይ ከስድስት ዓመት በፊት ስድስት ወጣቶች ተገድለው ደልድዩ ስር ተጥለው መገኘታቸው በዜና ሰምተናል ሽብር ማለትም ይህ ነው ፤እነዚህ ተገድለው በየቦታው ተጥለው የሚገኙ በደህንኖቶቹ የተገደሉ ናቸው ።

ስለዚህ ኢትዮጵያ የምትገዛው ያለች በሽብርተኛው ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ ነው ፤ይህ ድርጀትም ጊዜ ከመጠበቁ አንጻር ካልሆነ ፤ኢትዮጵያን በታትኖ ህዝቡም ሃገር አልባ ከማድረግ እንደማይመለስ ካሁኑ ማወቅና መገንዘብ ለምናካሂድው መከላከል ይጠቅመናል ። ይህም በየትኛውም ዓለም የማይደረግ ድርጊት ። የኢትዮጵያ ህዝብ ግን የዚሁ የህ.ወ.ሓ.ት. ፋሽሽት ስርአት ሰለባ ሆኖ እየተሰቃየ ይገኛል ። በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያነሳው ትልቅ ጥያቄ አለ፣ እሱም፤ በኢትዮጵያ ወስጥ ለተፈጠረው ችግር ተጠያቂው ማነው? እንዴትስ መጡብን ? የሚለው ነው። በ1960ዎቹ የተፈጠረው እንቅስቃሴ ለችግሩ ጥንስስ መሆኑን እንዳለ ለታሪክ ሊቀውንቶች ልተወው።-- ህወሓት የተፈጠረው በዚሁ የተማሪዎች ንቅናቄ ወቅት ነበር። በመጀመሪያ የነበረው ስም በተፈጠረበት በ1964 National Tigray Organization (NTO) ብሄረ ትግራይ ድርጅት ሲሆን፣ ይህንን ድረጅት የመሰረተው አረጋዊ በርሄ ብቻው ነበር። ፣ ተሳታፊ አባላት አልነበሩትም። በዚህ ጊዜም ሌላ ድርጅት በጀብሃ ታጋድሎ ሃርነት ኤርትራ የተፈጠረም ነበር። እሱም Tigray Liberation Front (TLF) የሚባል

ወይም ግንባር ገድሊ ሃርነት ትግራይ (ግገሃት) ነው። ይህ ድርጅት ጸረ-ኢትዮጵያ ሉአላዊነትና ጸረዲሞክራሲ ነበር። ተእዛዞችን በሙሉ የሚቀበለው ከጀብሃ ነበር። የትጥቅ ትግሉን የጀመረው በ1964 ዓ.ም. ነው። ይህ ድረጅት ትግራይ በአማራ መንግሥት (በኢትዮጵያ) ቅኝ ግዛት የወደቀችው ከአፄ ዮሃንስ 4ኛ ሞት በኋላ ነው ብሎ ያምናል። ትግራይ የኢትዮጵያ አካል አይደለችም ብሎ የሚያም ፅንፈኛ ድርጅትና ከሃድ ነው ፤ ህ.ወ.ሓ.ትም እምነቱ ይህ ነው ፤ ስለሆነም፣ለትግራይ ሃገራዊ ነፃነት እንዋጋለን ብሎ ነው የተነሳው። ጀብሃም ትግራይ የአማራው መንግሥት ቅኝ ግዛት ናት ብሎ አምኖ ተቀብሎታል። የአረጋዊ በርሄ ድረጅትም ከግ .ገ.ሓ.ት. መሪዎች ግኑኝነት ነበረው ፤በብዛትም ጓደኞቹ የነበሩ ናቸው ።የሁለቱ ድርጅቶች ማለት ግ.ገ.ሓ.ት. እና ብሄረ ትግራይ ድርጅት ቀጥሎ ማ.ገ.ብ.ት. ፕሮግራማቸው ምንም ልዩነት የለውም። ሁለቱም ትግራይ በአማራው በምኒሊክ ዘመነ መንግሥት ነፃነትዋ ተነጥቃ በቅኝ አገዛዝ በአማራው እጅ የወደቀች ሃገር ናት ፤ የአማራው መንግሥት ለትግራይ ህዝብ በሸዋዊ ዘዴዎቹ ከፍጡር ሁሉ ውጭ በማድረግ ለረሃብ በሽታ ድንሩርና ለስደት ለሽርሙጥና ዳርጎት ይገኛል ። ስለሆነም በትጥቅ ትግል የሃገራችን ነፃነት እናስመልሳለን ፤ በለው የሚያምኑ ሁለት ፅንፈኛ ድርጅቶች የተፈጠሩት በዚሁ የተማሪው ንቅናቄ ጊዜ ነው ። የፕሮግራማቸው ይዘታን አቀማመርም ልዩነት የለም ።ሁለት ድርጅቶች ፀረ ኢትዮጵያ ሏላዊነት ፀረ ኢትዮጵያ ህዝብ ናቸው ።ኢትዮጵታን ለማዳከም አዳከመው ለመበታተን የተፈጠሩ ናቸው ።

ሁለቱም ድርጅቶች ግንባር ገሊ ሓርነት ትግራይና የትግራይ ብሔር ድርጅት (NTO ) መቆም የቻሉት በሱዳንና በግብፅ ውስጣዊ ድጋፍን መበረታታ ነው ፤ብዙም ሳይሆን ትንሽ የገንዘብ ድጋፍም ያገኙ ነበር ፤ ከዚሁ የተነሳ ሱዳኖች ከአረጋዊ በርሄ የቆየ ግንኙነታቸው ተጠቅመው ሱዳኖች በ1974 ዓ ም . ያነሱት ኢትዮጵያ መሬታችን ነጥቃናለች ይመለስልን ያቀረቡት አቤቱታ የድርጅቱ ቁልፍ መሪ አረጋዊ በርሄም በመሆኑ ጥያቄው ተቀብሎ ያስተናገደው እሱ ስለነበረ የሱዳን መንግሥት ለጠየቀው አወንታዊ መልስ በ1975 ዓ .ም .መስከረም ወር ሱዳን መሬትዋ እንደምታገኝ በነበሩት አምስቱ ፖሊት ቢሮ እና ስድስተኛው መለስ ዜናዊ ፈርመው ያረጋገጡላቸው ። ጊዜው እየተራዘመ ሲሄድ የአረጋዊ በርሄ ድርጅት N.T.O. ( የትግራይ ብሄራዊ ድርጅት ) ጥቂት ሰዎች አሰባስቦ በመጀመሪያ መሰከረም ወር 1967 ዓ.ም. ፣ አረጋዊ በርሄ የመሰረተው ድርጅት ተጨማሪ አባላትን በማሰባሰብ አዲስ አበባ ውስጥ ማገብት ተመሰረተ። ማህበር ገስገስቲ ብሄረ ትግራይ ፤ ( የትግራይ ብሄራዊ ድርጅት) ( N.T.O. ) የሚለው ስም በማ.ገ.ብ.ት. ተለወጠ ። ;።ይህ ድርጅት የመሰረቱት ሰባት ሰዎች ናቸው: እነሱም፣ አረጋዊ በርሄ፣ ዋና ሰብሳቢና ሊቀመንበር፣ ግደይ ዘርአጽዮን ም/ሊቀመንበር፣ አባይ ፀሃየ፣ የቅስቀሳና የፕሮፓጋንዳ ሃላፊ፣ ስዩም መስፍን፣ ዘርኡ ገሰሰ፣ አስፍሃ ሃጎስና አለምሰገድ መንገሻ (ሃይሌ ነጠቦ) ናቸው። ማገብት እንደተመሰረተ ስብሃት ነጋ፣ መለሰ ዜናዊ፣ ቴዎድሮስ ሃጎስ፣ ስየ አብርሃ፣ አውአሎም ወልዱ፣ አጽብሃ ዳኘውና

ገሰሰው አየለ በፍጥነት ተቀላቅለው አባል ሆኑ።

ፕሮግራሙን በተመለከተ፣ በዲማ ኮንፈረንስ በየካቲት ወር 1968 ይፋ እንደተደረገ የተ.ሓ.ህ.ት. የተግል ፖሊሲ የአቋም ፕሮግራም ሆኖም ፀደቀ ።ፕሮግራሙም የድርጅቱ አቋም ሆኖ ቀጠለ ። ይህ ፕሮግራም ከደደቢት በረሃ ለትጥቅ ትግል ተ.ሓ ህ.ት. ከተነሳበት ጊዜ ጀምሮ በትጥቅ ትግሉ ጊዜ ምንም አይነት ለውጥ ያልተደረገበት ታስቦም ተሞኩሮም የማይታወቅ ትግሉ ከተጀመረ ከ 6 ወር ቆይታችን በኋል የነበሩት ጉድለቶች አርመነዋል የሚል የሚናገሩት ፍፁም ውሸት ሲሆን የታረመው የትኛው ክፍል ነው ተብለው ቢጠየቁ መልስ የላቸውም ማስረጃም ሊያቀርቡም አይችሉም ።የበሰበሰ አምባገነናዊ በታኝ ፀረ ህዝብና ፀረ ሃገር ፕሮግራም ። ሀወሓት ወያኔ ኢትዮጵያ ወሮ የቅኝ አገዛዝ ስርአቱ ስልጣኑን ካረጋገጠበት ግንቦት 20 1983 ዓ.ም. ሳይለወጥ እንዳለ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ሆኖ ሃገር እያፈረሰ ሃገር እየሸጠ ህዝብ እየበተነ ያልው የፋሸሽቱ ወያኔ ፕሮግራም ነው ። ።

ይህ ፕሮግራም ከመነሻው ገጽ ጀምሮ ጸረ-ኢትዮጵያ ሉአላዊነትና ጸረ-ኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ይህ ፕሮግራም በእነ አረጋዊ በርሄ የተዘጋጀና የተሳናዳ ሰነድ ከመነሻው ጀምሮ በትግራይ በሺዎች የሚቆጠሩ ሕዝብ በአማራው ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምት ወዘተ የአማራውን ዘር ያጠፋ ወንጀለኛ ሰነድ ነው። ይህ ብቻ አይደለም፣ ተሓህት-ህወሓት የአማራውን ግዛት፣ ጎንደሬዎች የሚኖሩበትን፣ ከትወልድ ትውልድ እየተላለፈ የመጣውን የአማራውን መሬት የትግራይ ቦታ ወይም ግዛት ነው በማለት መሬታቸውን ተነጥቀዋል። የአማራውን ሕዝብ ከትውልድ ቦታቸው ለማጥፋት፣ ዘራቸው የጠፋው ከዚህ የመሬት ነጠቃ ጋር የተያያዘ የግፍ ግፍ ተፈጸመባቸው። ይህ በዓለም አቀፍ ሕግ  የዘር ማጥፋት ወንጀል ነው። በዚሁ ጊዜ ተዋናይ በመሆን ይህንን ግፍ ሲፈጽሙና ሲያስፈጽሙ የነበሩትን በግልጽ ለማስቀመጥ፤ አረጋዊ በርሄ፤ ግደይ ዘርአጽዮን፣ ስብሃት ነጋ፣ አባይ ፀሃየ፣ ስዩም መስፍን እና መለስ ዜናዊ ናቸው። የመጀመሪያዎቹ አምስቱ የፖሊት ቢሮ አባል ሲሆኑ፣ መጨረሻ ላይ የተጠቀሰው በማንኛውም ውሳኔ ከነሱ የማይለይ ማእከላይ ኮሚቴ የነበረ በ 1975 ዓ.ም ደግሞ ፖሊት ቢሮ የሆነ ነው ። በዘር ማጥፋቱ ወንጀልና በትግራይ በተፈጸመው ሕዝብ የመግደል፣ የማፈን እና ማጥፋት እንዲሁም ንብረትና ሃብት መንጠቅ ተለይቶ አያውቅም። ይህንን ሁሉ ግፍ የፈጸሙት አብረው ነው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የህወሓት ከፍተኛ የአመራር አባላት የሚመሩት ድርጅት የፈጸመው ወንጀል የሚዘገንን ነው። ወንጀል የሚፈጽሙበትን አሠራር አስቀድመው አዘግጅተዋል። ዋና ዋናዎቹ፣ ሃለዋ ወያነ (06) ወህኒ ቤቶችን ከተሟላ አባላቱ ጋር በየቦታው መስርተዋል፤ ፈዳያን ( አጥፍቶ ጠፊ ) terrorist-አፍኖ የሚያጠፋና የሚገድል ቡድን፣ ክብሪት ተብሎ የሚታወቀው በአንድ ጉጅሌ ከ 10---እስከ 12 ታጋና ወያኒ ( ምልሻ ) ያካተተ ሁሉ የታጠቁ አደገኛ ነብስ አጥፊ በቀን በለሊት ሰውን እያፈነ የሚገድል በማሰማራት ፣ ግለሰቦችን ባገኙበት ቦታ የሚገድል ቡድን፣ የስለላ መርበብም አጠናከሩት ፣ የሕዝብ ግንኙነት ታጋዮች፣ሁሉ በስለላው ውስጥ የተካተቱ ናቸው ፤ እነዚህ ህብረተሰቡን በማያውቀው የፖለቲካ ውጥንቅጥ በማስገባት ህዝብ ራሱ በራሱ እንዲጠራጠር እንዳይተማመን አንዱ ለአንዱ ተከታታይ ሰላይ አደረጉት እንደ ድሮው አብሮ መብላት መጫወት ቀረ ፤ ባል ከሚስቱ ፤ሚስት ከባልዋ መተማመን ቀረ ፤የህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች የትግራይ ህዝብ ከፋፈሉት ፤ለሚጠሉት ለሚጠረትጥሩት ሁሉ ፤ ጸረ-ህወሓት፣ ኢዲዩ፣ ኢህአፓ፣ ደርግ ወዘተ የሚል ስም እየለጠፉ ሕዝብ አስጨረሱት ፤ የአካባቢ ኗሪ ሰዎች ወንድ፣ ሴት እየመለመሉ ታማኝነታቸውን ለማስመስከር በውሸት ብዙ ሰዎች አጥፍተዋል። ለውለታቸውም ሰፊ መሬት ይሰጣቸዋል። እነዚህ ከየቦታው እየተመለመሉ ተባብረው የሚሰሩት ከሕዝብ ግንኙነት አባላት ጋር ነው። ከነዚህ መካከል ለስጋቸው ያደሩ ቄሶችና ካህናት ይገኙበታል። ቀሱም ካህኑም እግዚአብሄር የከዱበት ዘመን ህ.ወ.ሓ.ት ፈጠረ ።በአስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ግን ይህ አልታየም ፤በእምነታቸው እንደፀኑ ቀጠሉ ፤ፀረ እምነታቸው ሁነህ ፤ከመጣህም ይቃወሙሃል አይፈሩም አይንበረከኩም ።

መለስ ዜናዊና ስብሃት ነጋ ለስልጣን የበቁበት ምስጢር ስንመለከተው ምስጢሩ የሚያስገርም ነው። ገና የተሓህት 1 ኛው ጉባኤ በእቅድ የተያዘው በ 1969 መጨረሻው አካባቢ ነበር። ስብሃታ ነጋ በወቅቱ ፖሊት ቢሮ ሲሆን መለስ ዜናዊም እስከ 1 ኛው ጉባኤ ድረስ ተለዋጭ ማእከላዊ ኮሚቴ አባል ነበር። የፕሮፖጋንዳው ክፍል ሁለተኛ ተጠሪ ከአባይ ፀሃየ በታች በመሆን በሥራም የሚታወቀው ግን መለስ አዛዥ አባይ ታዛዥ ሆነው ሲሰሩ ድብቅ ምስጢር አልነበረም። ምክንያቱም መለስ ዜናዊ የአረጋዊ በርሄ ታማኝ ነው።

አረጋዊ በርሄም በመለስና በስብሃት የሚመጣ ነገር አያስችለውም።ፀር-መለስና ስብሃት ሆነው የተነሱ ታጋዮች አረጋዊ በርሄ ካለምንም ማቅማማት ያጠፋቸዋል፣ ይገድላቸዋል።የተገደሉም አሉ ስብሃትና መለስ አትመን ፀረ ሃገርና ፀረ ህዝብ ናቸው የባንዳ ልጆች ከመሆናቸው የተነሳ በትግራይ ህዝብ ቂም በቀል በሆዳቸው የቋጠሩ ችግር ይፈጥራሉ ፤ ሌላም

እነዚህ የባንዳ ልጆች የትግራይን ህዝብ መምራት ማለት ለትግራይ ህዝብ ስድብና ውርዴትም ጭምር ነው ፤ብለው ብዙ ምክር ቢለጉስለት የራሱ የቅርብ ጓደቹ አረጋዊ ይህን አልሰማ ብሎ ይህ ቀና ምክር መጥፎ ትርጉም ሰጥቶ ገልብጦ የሥልጣን ሥሰኞች በማለት ተረሸነው ተገድለዋ በጥቂቱም ለማንሳት 1 እቁባዝጊ በየነ 2 አሰፋ ገብረዋህድ 3 ዘወንጀል በየነ 4 ህንፃ ሽፈራው 5 ዓለም ወልደገሪማ ሌሎችም ብዙ ታጋዮች ተረሸነዋል ፤አመራሩ ሕንፍሽፍሽ ብሎ የሚጠራው በድርጅቱ ታጋይ አምነት የዲሞክራሲ ጥያቄ ነው፤ ዋና ግንባር ቀደም ጥያቄ ስብሃት ነጋ እና መለስ ዜናዊ ፀረ ህዝብ የባንዳ ልጆች ይወግዱልን መለስ ፈሪ ከብዙ ጦርነት የሸሸ ይገደል በማለት ቀዳሚ ጥያቄ ሆኖ በተነሳ ለነ አረጋዊ ሊዋጥላቸው ስላልቻለ በስንት ሺህ የሚቀጠሩ ታጋዮች ተረሸነው ተገድለዋል ።

ሌላው አስገራሚ ነገር በ 1969 ዓ.ም. መጀመሪያው አካባቢ በአረጋዊ በርሄ የሚመራ ቡድን ስብሃት ነጋ ግደይ ዘራፅዮን ስዩም መስፍን ሆኖው ወደ ሻዕብያ ፤ሳሕል ድረስ ተጉዘው ነበር ፤ የጉዞው ዋና አንኳር ምክንያቱም ትግራይ ነፃ ሃገር ራስዋን ችላ ቀደም ሲል የአኩሱም መንግሥት መስርታ ለ 900 መቶ ዓመታት በነፃነትዋ የቀየች ሃገር ፤ በኋላም በአፄ ዮሃንስ መንግሥትነት እየተመራች የቆየች ነፃነትዋ አስከብራ የቆች ነፃ ሀገር ከአፄ ዮሃንስ ሞት በኋል በንጉሥ ምኒልክ ተወራ በአማራው የሸዋ መንግሥት በቅኝ ግዛት ሥር ወደቀች ።

ትግራይ ነፃነትዋ ተገፋ የአማራ መንግሥት ቅኝ ግዛት ሆነች ። በአማራው ዘዴ ህዝብዋ ለመከራ ለችግር ለስደት ዜግነቱ ነፃነቱ ተነጥቆ ሁለተኛ ዜጋ ሆኖ ፤ ነፃ ሃገር ትግራይ ፤ በአማራው ቅኝ አገዛዝ ስርአት መሆንዋን የሻዕብያ ድርጅት የአማራው ቅኝ ተገዥ መሆናችን እውቅና ሰጥቶ በእውቅና ይቀበለን የሚል ጥያቄን ልመና ይዘው ሳሕል ድረስ ሂደው አቀረቡ ።ይህን የእውቅና ልመና ይዘው የሄዱት የተ.ሓ.ህ.ት. መሪዎች 1ኛ አረጋዊ በርሄ 2ኛ ግደይ ዘራጽዮን 3ኛ ስብሃት ነጋ 4ኛ አባይ ጸሃይ ናቸው ። የአቶ ኢሳያስ አፈወርቅ መልስ ፤ ይህን ጥያቄ ማቅረባችሁ በጣም አዝናለሁ ፤ትግራይና ኤርትራ የኢትዮጵያ የታሪክ እምብርት ናቸው ፤የኢትዮጵያም አካልና ግዛት ናቸው ፤በታሪክም በባልም በቋንቋም በሃይማኖትም አንድ ህዝብ ሆኖ የመጣ ህዝብ ነው ።

እኛም በኤርትራ ውስጥ ትግል የጀመርነው ለኤርትራ በተባበሩት መንግሥታት የተሰጠን የኤርትራ ፌደረሽን በንጉሡ ተነጥቀን የነበረው መዋቅር አፍርሰው የተሰጠን መብት ተነጥቀን ነው ፤ በተባበሩ መንግሥታት የተሰጠን የፌደራሉ አገዛዝ ቢመለስልን ውጊያ አያስፈልገንም ነበር፤ የፌደራሉ ስርአቱን ይዘ ኢትዮጵያዊነታችን ይበጀን ነበር፤ ግን አልሆነም ።

የአሁኑ የናንተ ጥያቄ የአማራ ቅኝ ተገዢ ነን ማለታችሁ ጤንነት የሌለው በመሆኑ አዝናለሁ ፤እኛ ለዚሁ አሳፋሪ ነገር ፀረ ኢትዮጵያ እውቅን አንሰጥም ። በእትዮጵያዊነታቹህ ልትኮሩ በተገባቹህ ነበር፤ መልሳችንም ይህ ነው ። ብለው አሰናበትዋቸው። እነዚህ የተ.ሓ.ህ.ት. መሪዎች የኤርትራው የሻዕብያው መሪ ኢሳያስ አፈወቂ የትግራይ የቅኝ ግዛት ጥያቂ አልቀበልም ፤ትግራይ የኢትዮጵያ አካል ናት ስላለን ግኑኝነታችን ተበላሽትዋል ብለው ለተ.ሓ.ህ.ት.ታጋይ በአዋጅ በስብሰባ ተናገሩ ፤ሁሉ ታጋይ ሻዕብያን እንዲያወግዝ ቢያደርጉም ሰሚ አልተገኘም ።የህ.ወ.ሓቅ.ት. መሪዎች ጠባሳ ታሪክ አደራ አስቀምጠው ተመለሱ ፤ሻዕብያ ይህን በድምፅ ቀርፆ በሰነድ ፅሁፍ አዘጋጅቶ ነው የሚያስቀምጠው ።

የድረጅቱ ፋላጭ ቆራጭ፣ እስከ መባረሩ ጊዜ ድረስ ሆኖ የቆየው ፣ አረጋዊ በርሄ መሆኑና መኖሩ ሁሉ የህ.ወ.ሓ.ት ታጋይ በግልጽ የሚያውቀው ጉዳይ ነው ።እሱ ያልፈቀደው አንዷት ነገር አትሰራም ፤ይሁን ያለው ይሆናል አይሆንም ካለም አይሆንም ፤ የስብሃት ነጋ የመለስ ዚናዊ ከአረጋዊ በርሄ የነበራቸው ፍቅር የጠበቀ ግኑኝነት ልዩ ነበር ከዚሁ በመነሳትም መለስ ዜናዊ በጦርነት ፈሪ በመሆኑ ጥይት ስትቶኮስ መሬት ተከፍታ ብትውጠው ይመኛል ከብዙ ጦርነቶች የሸሸ ፈሪ ታጋይ ከህ.ወ.ሓ.ት. ውስጥ መለስ ነበር አንዱ ከብዙ የውግያ ቦታ የሸሸ ነው ሌላ በጦርነት ያፈገፈገ በቀጥታ ይገደላል መለስ ግን ከዓድዋ አፖረሽን ከዓዲዳእሮ ፤ ከማይቅነጣል ወ.ዘ.ተ ፈርቶ ሸሽቶ ሲጠፋ የተወሰደበት እርምጃ የለም እድሜ ለአረጋዊ የሚጠይቀውም የለም ። መለስ ከስልጣን ወደ ስልጣን እየተራመደ የመጣውም በአረጋዊ በርሄ ትክሻ ነው ፤ ስብሃት ነጋን ጨምሮ ። ሶስቱ የነበራቸው ግኙኙነትና ጓደኝነት በጣም የጠበቀ የሚተማመኑ አመራር እነዚህ ሶስቱ ነበረ ሁሉም ታጋይ በአይነ ቁራኛ ይመለከታቸው ነበር።

አረጋዊ በርሄም የድረጅቱ ስልጣን በዋናነት በሶስቱ እጅ እንዲወድቅ በነበረው ምኞት መሰረት ገና 1ኛው ጉባኤ ከመድረሱ በፊት ሶስቱ ባልታወቀ ቦታ ተገናኝተው የሚከተለውን እቅድ አወጡ፣የሃሳቡ ባለቤት አረጋዊ ሲሆን ፤በሚከተለው ሃሳብ ተስማሙ ፤ 1ኛ. የድርጅቱ ሊቀመንበር ለስብሃት ነጋ፣ 2ኛ. የድረጅቱ ወታደራዊ አዛዥ ለአረጋዊ በርሄ፣ 3ኛ. በህወሓት ውስጥ ለሚመሰረተው ማርክስ ሌኒናዊ አስኳል በመለስ ዜናዊ እንዲመራ ኮምሽነር ሆኖም ሁሉ

የካድሬ ሥልጠና በመለስ እንዲመራ ተስማሙ። ይህ በዚህ እንዳለ፣ ይህ የሶስቱ ሚስጢር ያገኘው ተክሉ ሃዋዝ የድርጅቱ የደህንነት ሃላፊ ነው ሚስጢሩም ያጫወተኝ ያገኘሁትም ከተክሉ ሃዋዝ ነው ። አረጋዊ በርሄ ከተለያዩ ታጋዮች ስብሃት ነጋ እና መለስ ዜናዊ ለድርጅቱም ሆነ ለትግራይ ሕዝብ አደገኞች መሆናቸው የተለያየ ሃሳብ ይሰጡት ነበር። ቢሆንም አረጋዊ በርሄ እነዚህ ታጋዮች የሚሰጡት ሃሳብና ምክር ሳይቀበል ቀርቶ ይህ ምክር የለገሱት ታጋዮች በጠላትነት እየፈረጀ የሥልጣን ሱሰኞች እያለ ከገደላቸው የተማሩና አብረውት ያደጉ ታጋዮች ለአብነት መጥቀስ አስፈላጊ ሆኖ ስለአገኘሁት ልጥቀስ፤ እቁባዝጊ በየነ፣ አሰፋ ገብረዋህድ፣ አባዲ ተምቤን፣ ዘወንጀል በየነ፣ ገብረዝጊ አለማየሁ፣ ይብራህ ገብረጊዮርጊስ፣ ዘሚካኤል ደስታ፣ ዓለም ወ/ገሪማ፣ አበራ ማንካ፣ ሃይለሥላሴ ገ/ሚካኤል፣ ሃዲሽ ዮሃንስ፣ ሃጎስ ሃይለሥላሴ፣ ዘርኡ በዛብህ፣ ባሻይ ሃንጣል፣ ዘርኡ ገሰሰ፣ ገሰሰ አየለ፣ አዘናው ገ/ጻዲቅ፣ ተስፋይ ዓድዋ፣ ህንጻ ሽፈራው ወዘተ መለስ ዜናዊና ስብሃት ነጋ ወደ አመራር መምጣት ከሚሰጠው ጥቅም ለትግራይ ሕዝብ አደገኛ መሆናቸው በመጠቆም ሌላው ድርጅቱ በባንዳ ልጆች መሙላቱ አድጋውን አስቀድመው በመተንበይ ሲናገሩ በአረጋዊ በርሄ ደግሞ የሥልጣን ሲሰኞች ተብለው እነዚ ሁሉ ተገደሉ።

በተሓህት-ህወሓት ውስጥ በዚሁ ወቅት የተለያዩ የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ታጋዩ ይስነሳበት ጊዜም ነው። እኛ የተሓህት-ህወሓት መብታችን ይከበር ድርጅቱ አምባገነን እና ፀረ-ኢትዮጵያ ሉአላዊነት፣ ፀረ-ሕዝብ አንድነት፣ ፀረ-ሰላም ፀረ ዲሞክራሲ ነው ። መለስ ዜናዊ ከተለያዩ የጦርነት ቦታዎች በፍርሃት ሲያፈገፍግ የተወሰደበት እርምጃ የለም። እኛ ታጋዮች ግን በዚሁ ምክንያት በመቶዎች ታጋይ ሃለዋ ወያኔ (06) እያስገባችሁ ተረሽነን ተገድለናል ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎች ተነስተዋል። የተሓህት-ህወሓት አመራር፤ አረጋዊ በርሄ፣ ስብሃት ነጋ፣ ግደይ ዘርአጽዮን፣ ስዩም መስፈን፣ አባይ ፀሃየ፣ መለስ ዜናዊ ተሰባስባችሁ በድርጅታችን ሕንፍሽፍሽ ተነሳ በማለት የዴሞክራሲውን ጥያቄ ወደ ሕንፍሽፍሽ ለውጣችሁ ታጋዩን ፈጃችሁ፣ በጅምላ ጉድጓድ ቀበራችሁ። ሌላውም ሕንፍሽፍሽ ወደ ሰላማዊ ዜጋ ተዛመተ ተብሎ የገጠርና የከተማውን ሰው እያጠፋችሁ ነው። የገደላችሁትንም ንብረቱን በህወሓት ውርስ ተደርጓል።

የንጹህ የትግራይ ሕዝብ ሙብት ይከበር በምንልበት ጊዜ፣ ሕጋዊና ዴሞክራሲያዊ ጥያቄ ብናነሳ መልኩን ለውጣችሁ ሕንፍሽፍሽ በማለት ተፈጀን፣ አለቅን። ለዚህ ሁሉ ግድያ በታጋዩ እና በሰላማዊ ዜጋ ላይ የተፈጸመው፣ እየተፈጸመም ያለው እልቂት ተጠያቂ የምትሆኑት 6 (ስደስት) የአመራር አባል ናችሁ። ከዚሁ በመነሳት ታጋዩ ባገኘበት መንገድ ወደ ደርግ የያዘው መሳሪያም ሆነ ሌላ የድርጅቱ ንብረት እየተሸከመ በብዛት ጎረፈ ለደርግ እጁን ሰጠ።

ከላይ የተጠቀሱትና የተገደሉት ታጋዮችና ያልጠቀስኳቸው ሌሎችም የአረጋዊ በርሄ አብሮ አደግና የቅርብ ጓደኞቹ ናቸው። ግን ለመለስ ዜናዊና ስብሃት ነጋ ተቆርቋሪ በመሆኑ መሆን የለበትም ፤የድርጅቱ ሕግ በሁሉ ታጋይ እኩል መስራት አለበት ሌላው ሲገደል ሌላው አይጠየቅም ፍርድ እየተዛባ ነው በማለታቸው ገደላቸው። ይህም ተጠያቂ የሚያደርገው አረጋዊ በርሄን ነው ፤ የፈጸማቸው ወንጀሎች ብዙ ናቸው። ከኢዲዩ ጦርነት ህወሓት በሚካሄድበት ጊዜ የኢዲዩ አብላት ተሸንፈው እጃቸውን ሰጡ። በመስከርም አካባቢ 1969 ብዙ ምርኮኞች ናቸው አረጋዊ በርሄ ጨአ፣ መስከበት አካባቢ የጅምላ ጉድጓድ አስቆፍሮ ረሽናቸው። ከሱ ጋር የነበረው አልአሚን፣( የኗላሸት ገብረመድህን)፣ ተው አትግደላቸው አሁን ጠያቂ ባታገኝም ለኋላ ኋላ ግን ያስጠይቅሃል ብሎ ቢማጸነውም አልተቀበለውም። አልአሚን ያየውን ፋሽስታዊ ግፍ ለብዙ ሰዎች ተናግሯል።

አረጋዊ በርሄ ተውልዶ ያደገው ዓድዋ ከተማ እንዳ መድሃኒ ዓለም ሰበካ ውስጥ ነው ። በአባቱም በእናቱ የአርበኞች የጀግኖች ልጅ ነው ። በአጭሩ እንመልከት ። የአረጋዊ ወላጅ አባት ቀኛ/በርሄ ገብረማርያም ይባላሉ ፤አባታቸው ፊታውራሪ ገብረማርያም ናቸው ትውልድ ዓድዋ ፤ቀኛ/በርሄ የቤተ ክህነት ትምህርታቸው ሙሉ በሙሉ በልጅነታቸው ያጠናቀቁ ሊቅ ናቸው ። ወራሪው ፋሽሽት ጣልያን በ 1928 ዓ.ም. ኢትዮጵያን አንደወረረ ፊታውራሪ ገብረማሪያም የ 20 ዓመት ልጃቸው በርሄ ገብረማሪያም አስከትለው ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋር ተቀላቀሉ ፤በማይጨው ዘመቱ ፤ምድብ ቦታቸው አላጀ ግንባርም ነበር ፤የኢትዮጵያ አርበኞች በማስተባበርም ግንባር ቀደም መሪ በመሆን ወራሪው ጣልያን ያሸመደመዱ ጀግና መሆናቸው በህዝብ አድናቆት ያገኙ ናቸው፤በኢትዮጵያ ታሪክም የገድሉ ታሪካቸው በባህረ መዝገብ የተጻፈ ኢትዮጵያዊ ጅግና ናቸው ፤ ፤በመጨረሻ አላጄ ግንባር ለናት ሃገራቸው ኢትዮጵያ መስዋእትነት ከፍለው በፋሽሽት ጣልያን በተቶኮሰው የአይሮፕላን ቦምብ ተመተው ተሰውተዋል ።አይበገሬው ወጣቱ ልጃቸው በርሄ ገብረማሪያም እስከ መጨረሻው ከአርበኞቹ ሳይለይ ወራሪው ጣልያን እየተዋጋ ቆይቶ ፤ ጣልያን ተሸንፎ በድል አርበኝነት ኢትዮጵያ ሙሉ ነፃነትዋ ከተቀዳጀች ወጣቱ በርሄ ገብረማሪም አረንጓዴ ብጫ ቀይ የሚወዳት ሃገሩ ኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማው ተሸክሞ ዓድዋ ገባ ። አረጋዊ በርሄ በወላጅ እናቱም የአርበኛ ልጅ ነው ፤ የእናቱ ወላጅ አባት ፊታውራሪ በዛብህ ፍላቴ ይባላሉ የዓድዋ ባላባት ፤ፋሽሽት ጣልያን በ 1928 ዓ.ም .ኢትዮጵያን እንደወረረ ከአርበኞች ተቀላቀሉ የዘመቻ ምድባቸው ማይጨው ስለነበር ፤ማይጨው ዘምተው ከራስ ካሳ ኋይሉ የጦር ቀጠና መሪ ሆነው 5 ዓመት በአርበኝነት እናት ሃገራቸው ኢትዮጵያ ያገለገሉ የ 5 ( የአምስት ) አርበኛ ናቸው ።ኢትዮጵያ ነፃነትዋ እንደተቀዳጀችም ፤በቀዳማዊ ኋይለ ሥላሴ ንጉሰ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ መልካም ፍቃድ አዲስ አበባ ድረስ ተጠርተው ሚያዝያ 27 ቀን 1945 ዓ.ም በክብረ በዓሉ ፤ በቦታው በመገኘት የልጅ መዓርግ ከነሙሉ የመዓርግ ልብስ ተሸልመዋ የአምስት ዓመት የአርበኞች የተለያዩ መዳሊያዎች የተሸለሙ አርበኛ ። በልጅ በዛብህ ፍላቴ ፍላጎት መሰረት የመንግሥት ሥራ ይቅርብኝ ልረፍ ስላሉ ፤ለሃገርህ ኢትዮጵያና ለንጉሠ ነገሥትህ ታማኝ ሆነህ አምስት ዓመት ሙሉ ከጠላት ተፋልመህ ለሃገርህ ነፃነት ጉልህ ሚና ያበረከት የአንድ አውራጃ ገዥ ደሞዝ በየወሩ የሚከፈልህ የጡሮታ ክፍያ እድሜህ ልክ ከዛሬ ጀምሮ ተፈቅዶልሃል ተብለው በክብር የተሰናበቱ ጀግና ናቸው ። አረጋዊ በርሄ በጥሩ ቤተ ሰብ ያደገ ፤ ተማሪ በነበረበት ሰው አክባሪ ትሁት ታዛዥ መኖሩን የዓድዋ ነዋሪ ህዝብ ያውቃል ። በትምህርቱ ጎበዝ ፤ወላጆቹ ተልቅ ተስፋ ያሳደሩበት ነበር ፤አያቱ ልጅ

በዛብህ ፍላቴ ሲጠሩት ያይኔ ብርሃን ብለው ነው የሚጠሩት ፤በጠቅላላ ቤተ ሰቡ ሁሉ የሚኮራበት ነበር ።በመጨረሻው በረሃ ወጥቶ በፀረ ኢትዮጵያዊነት ተሰልፎ ንፁሃን ኢትዮጵያውያን የትግራይ ዜጎች በመግደል መሰማራቱን በየቀኑ በሚደርሳቸው ዜና ረግመዉት ፤ውጉዝ ከመ ስይጣን ብለዉት ከዚህ ዓለም አልፈዋል ። ከዚህም የከፋ ነገር የለም ። አረጋዊ በርሄ ከእነዚህ አብራክ የተፈጠረ ልጅ ፤360 ዲግሪ ተገልብጦ ለምን ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ ኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት ሆነ ? የሚለው ጥያቄ ገና ከ 1964 ዓ .ም የተነሳ ጥያቄ ነው ።መልስ ያላገኘ ፤ግን መልስ አለው ፤ በዙም ባይባሉም ጥቂት ምሁራኖች ለምን ኢትዮጵያን ጠላህ ? የሚሉትም ነበሩ የሚሉም አሉ፤መልሱ ደግሞ አረጋዊ በርሄ በባዕዳን ፀረ ኢትዮጵያ ኋይሎች በጥቅም የተገዛ በተክለ ሰውነቱ ባንዳ አተላ ዝቃጭም ነው ። የአረጋዊ በርሄ ጥልቅ ባህሪያት ፤ 1ኛ የወጣለት ፀረ አማራ ነው ። አማራን ይጠላል ፤አማራን ያወግዛል ; በዙ ጊዜ እኔ ራሴን የሰማሁት በትግሉ ወቅት አማራ ብሎ እንዳይጠራ ስሙን ስለሚጸየፈው ‹አህዮች ›እያለ ነው የሚጠራው ፤በስብሰባም ይሁን በተገኘው አጋጣሚ ።እነዚህ አማሮች ነፃነትዋ ጠብቃ ለብዙ ሺህ ዓመታት ትግራይ አፄ ዮሓንስ ከሞቱ በኋላ ትግራይ በሸዋ አማራ መንግሥት ቅኝ ግዛት ሥር ወድቃ ዛሬ በአማራ አገዛዝ እየማቀቅን እንገኛለን ፤አረጋዊ ይህ ለህዝብ በሚያስተምርበት እያለቀሰ ነው ፤የሚናገርው ። 2 ኛ ከሃዲ ውሸታም ነው ። ያደረጋት የሰራት በግልጽ የታየው የተሰራው ከተጠያቂነት ለማምለጥ ፤ በአፍጢምየ ድፍት ያርገኝ እኔ አልዋልኩበትም ብሎ ይክዳል ለምሳሌ የህ.ወ.ሓ.ት. ፕሮግራም አልጻፍኩም አላዘጋጀሁም ። ሰውም የገደልኩት የለኝ ንጹህ ነኝ ፤ይላል ። 3 ኛ አምባገነን ፀረ ዲሞክራሲ እኔ ያልኩት ይሁን እኔ የምለው ተቀብሉ እናንተ የምትሉት አያዋጣ እያለ በቀጥታ የሚከራከር ሰው ፡በውስጡ የያዘው ሃሳብ አለው ተቃዋሚ መስሎ በመቅረብ ወያኔ ህ.ወ.ሓ.ት. ሙሉ በሙሉ በህዝብ እንዲወገዝና እንዲጠላ ከሥልጣኑ እንዲወገድ አይፈልግም ፤ምክንያቱም በትግሉ ወቅት በህዝብ ላይ በኢትዮጵያ ሏላዊነት የፈጸሙት ከባድ ወንጀሎች ሃገር ዛሬ ፈርሳለች ኤርትራ ተገንጥላለች ፤ሰፊ ለም ታሪካዊ የኢትዮጵያ መሬት ለሱዳን መንግሥት ሸጠዋል፤ወ.ዘ.ተ. ይህን በከፍተኛ ወንጀል የሚያስጠይቅ ነው ፤ ከ 1972 ዓ.ም. ጀምሮ በአማራው ህዝብ ከባድ የዘር ማጥፋት ወንጀል አካሂደዋል ፤ይህ ራሱ በከባድ ወንጀል የሚያስጠይቅ ነው ። ሊላም ብዙ አለ ከዚሁ ፍርሃትና ጭንቀት የሚከላከልላቸው የህ.ወ.ሓ.ት. ስርአት ሲኖር ብቻ ነው ። ስለዚህ ተቃዋሚ ቢሆኑም በተቃዋሚ ኋይሎች ሰርገው በመግባት ቢያንስ ቢያንስ ወያኔ ዕድሜውን ለማራዘም የሚያስፈልጉት ነገሮች ከማስተካከል ወደ ኋላ አይሉም ። አረጋዊ በርሄ የህ.ወ.ሓ.ት. ዋናው መስራች ነው ፡ይህ ድርጅት የተመሰረተው በ 1964 ዓ.ም. ነው ።በዛን ጊዜ ስሙ ብሄረ ትግራይ ድርጅት ነው ፤ተከታይ ግን አልነበረውም ብቻው አረጋዊ ነበር፤ከብዙ ውጣ ውረድ ከ 3 ዓመት በኋላ መስከረም ወር መጀመሪያ 1967 ዓ.ም. ሰባቱን ሰዎች ተሰባስበው ማ.ገ.ብ.ት. ፈጠሩ ሊቀመንበሩ አረጋዊ በርሄ ሆነ ፤የነበረው ሃላፊነት ። 1 ኛ የድርጅቱ ፕሮግራም ማዘጋጀት ይህ ግንባር ቀደም ሆኖ ወደ ሥራው ተሰማራ ፤ ፕሮግራሙ ከመነሻው እስከ መጭረሻው 1 ፀረ ኢትዮጵያ ሏላዊነት ፤ 2 ፀረ ኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት ፤ 3 ጎጠኛ ከፋፋይ ፤ 4 ኢትዮጵያ በዘር በቋንቋ ተከፋፍላ ተበታትና ከዓለም ካርታ ውጭ እንድትሆን በማድረግ ያዘጋጀው ፤ 5 በኢትዮጵያ ያሉት ብሔር ብሔረሰቦች በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላምና አንድነት ፍቅር እንዳይኖር ህዝቡ በእርስ በርስ ግጭት እንዲተላልቅ ፤የሚፈጥር አርጎ ፕሮግራሙን ያዘጋጀ ። 6 ሙሉ በሙሉ ፀረ አማራ ፤ የአማራ ህዝብ የፈጀ ዘሩን ያጠፋ ።በዚሁ ፕሮግራም በሃላፊነት ተጠያቂው አረጋዊ በርሄ ነው ። 2 ኛ በፕሮግራሙ ውስጥ መስፋፋትና የመሬት ነጠቃ ያካተተ ሆኖም ተዘጋጀ ።በዚሁ መሰረት ሃላፊነት በጎደለው በጉልበት በኃይል ተግባራዊ የሚደረጉ ።

ሀ--- የሰሜን ጎንደር የአማራ ለም መሬቶች ፤ ወልቃይት ፤ጠገዴ ፤ ጠለምት ፤ ቃፍታሁመራ ወደ ትግራይ ያጠቃለለ ፤ይህ መሬት አማሮች በስልጣናቸው በጉልበታቸው ከትግራይ ነጥቃው ወደ ግዛታቸው ያጠቃለሉት ነው ፤ብሎ በወሰነው አረጋዊ በርሄ ፤የትግራይ መሬት ነው ፤ትብሎ በፕሮግራሙ በእስትራቴጂ ደረጃ ወደ ፕሮግራሙ ገባ ። እነዚ ቦታዎች ግን ለስንት ሺህ ዘመናት የአማራ መሬትና ግዛት እንጂ የትግራይ ሆነው አያውቁም ፤በአማራነታቸው የሚታወቁ ዋናው የሁሉ የአማራ ህዝብ መሰረት እዚሁ ነው ። ለ---- ሰሜን ወሎ ፤በሰሜን ወሎ የሚገኙ መሬቶች የወሎ ህዝብ መሰረታዊ የኑሮው የሂወቱ ምንጭ የሆኑት አለውሃ ምላሽ በመባል የሚታወቅ ፤ ራያና ቆቦ ፤ አፍላ ደራ ፤ ወልድያ ፤አላማጣ ወ.ዘ.ተ. ወደ ትግራይ በፕሮግራሙ ገባ ። እነዚህን ሰሜን ጎንደር ሰሜን ወሎ በተመለከተ ያካተተው አረጋዊ በርሄ መቅድም በሚለው አርእስት ገጽ v ወይም ገጽ 5 ማለቱ ነው ፤በራሱ የእጅ ፅሁፉ ይገኛል ፤ፕሮግራሙን ተመልከቱ ። <‹ <የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት >» በዋናነት ያዘጋጀው ፕሮግራም ወይም የአቋም ፖሊሲ አረጋዊ ብርሄ በየካቲት 5 ቀ 1968 ዓ.ም .በዲማ ኮንፈረንስ የፀደቀው ፤ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ሕገ መንግሥት የሆነው ። የአማራ ህዝብ ማንነት

የነጠቀ ፕሮግራም አማራው በገዛ ሃገሩ ሁለተኛ ዜጋ የሆነባት ኢትዮጵያ ፤ያደገበት እትብቱ የተቀበረበ ወልቃይት ጠገዴ ጠለምት፤ ውጣ ይህ የትግራይ መሬት እንጂ ያንተ አይደለም ተብሎ አማራው የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ለስደትና ረሃብ ችግር የተዳረገበት ዘመን ነው ፤ ይህ ሁሉ መከራን ሲኦል የወረደውም በህ.ወ.ሓ.ት. መስራቹና የፕሮግራሙ አዘጋጅና ፈላስፋው በአረጋዊ በርሄ ነው ። አረጋዊ በርሄ የውልቃይት ጠገዴ ጠለምት ቦታዎች ለመያዝና ለመቆጣጠር ቀደም ሲል ከ 1969 ዓ.ም. በትንሹ የተጀመረው ፀረ አማራ ዘመቻ በታህሳስ ወር 1972 ዓ .ም. በከፋ መልኩ ተጠናክሮ አረጋዊ በርሄ በሚመራው ድርጅታዊ መዋቅር የዘር ማጥፋት ዘመቻው ሁሉ የተ.ሓ.ህ.ት. ህ.ወ.ሓ.ት. መሪዎች ፤ 1 ስብሃት ነጋ 2 ግደይ ዘራጽዮን 3 አባይ ጸሃየ 4 ሥዩም መስፍን 5 መለስ ዜናዊ ከስየ አብርሃ ተደራቢ በመሆን የህ.ወ.ሓ.ቱ . ዋናው ወታደራዊ መሪ አረጋዊ በርሄ እነዚህን አመራሮች በወልቃይት በጠለምት በጠገዴ በየአቅጣጫው በማሰማርት ፋታ በማይ ሰጥ ሁኔታ የአማራው ሰሜን ጎንደር ህዝብ በተቻላቸው ሁኔታ የዘር ማጥፋት ወንጀል ፈጽመዋል።ይህ የዘር ማጥፋት ድርጊትም አማራው በተገኘበት እንዲገደል ፖሊት ቢሮው አረጋዊ በርሄ ስብሃት ነጋ ግደይ ዘራጽዮን አባይ ፀሃይ ሥዩም መስፍን መለስ ዜናዊ ባሳለፉት ውሳኔ ገና ሲጀምሩት በ 1968 ዓ .ም መጨረሻ . ማንም የትግራይ ተወላጅ ያልሆ ከትግራይ ይውጣ፤ትግራይ የመኖር መብት የለውም ትግራይ የትግራዊያን ናት ተብሎ ፖሊት ቢሮው ያሳለፈው ውሳኔ ለየርጅኑ ማለት ፤ርጅን 1 ሽሬ አውራጃ ሰመማና ጭላ ከፊል አክሱም ማለት ነው ርጅን 2 ከፊል አክሱም ዓድዋ ተምቤን ርጅን 3 ዓጋሜ፤ ሁሉት አውላእሎ እንደርታ ራያ ( ማይጨው ) በእነዚህ አካባቢ( ሓራ ) ነፃ መሬት በወቅቱ ይህን ያህል ነፃ መሬት ባይኖርም ግን በየቦታው ለሚገኙ ፤የህዝብ ግኙኝነት ትእዛዙ በማስተላለፍ አማራው በቀን በለሊት ከያለበት እየተለቀመ ሓለዋ ወያነ ( 06) እየተወሰደ የተገደለው አምላክ ይቁጠረው፤ በዚሁም ላይ ጠቅላላ ያፈራው ንብረት ሃብቱ ገንዘቡ እየተወረሰ በጡሮታ የወጣ በተለያየ መስክ ተሰማርቶ እየሰራ የሚኖረው አማራ በመሆኑ ብቻ የጥፋት ኖህ ወረደበት ። ይህም ለአመታት ዘለቀ በዚህ የግድያ መቅዘፍት ብዙ የትግራይ ሰው የአማራ ደጋፊ እየተባለ ታስሮ የተገደለው በጣም ብዙ ነው ፤ሃብቱ ንብረቱም እይተወረስ ቤቱ የፈረሰው የትግራይ ሰው አምላክ ይቁጠረው ። ይህ ሁሉ ችግር የፈጠረው አረጋዊ በርሄ በመሪነቱ መሰረት ያወጣው ፕሮግራም የሰሜን ጎንደር መሬት በመስፋፋት የትግራይ ግዛት ለማድረግ ሰሜን ወሎ ጨምሮ ታላቅዋን የትግራይ መንግሥት ለመመስረት ፤ በፕሮግራሙ ወይም ፖሊሲ መሰረት በንፁሃን ኢትዮጵያውያን ላይ በወልቃይት ጠገዴ ጠለምት የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈፀመ ወንጀለኛ መሪከነ ድርጅቱ ። መስፋፋት<<‹ሕገ ወጥ ነው ፤በማንም ህብረተሰብ ተቀባይነት የለውም ፤ መስፋፋት ፀረ ማንነት ፤ፀረ ዜጋም ነው ፤የፋሽሽት መለያም ነው ፤መስፋፋት የሕብረተሰዉን ዘር ለማጥፋት ልዩ መሳሪያም ነው፤ የአማራ ግዛት ዳር ድንበር ተሻግረህ ራሱ የቻለ ታሪካዊ፤ ለስንት ሺህ ዘመናት በኢትዮጵያ ነገሥታት ተከብሮ የኖረው የግዛት ደንበር በጉልበትህ ተማምነህ ባዘጋጀው ፕሮግራም ወልቃይት፤ ጠገዴ፤ጠለምት ቃፍታ ሁመራ ወደ ትግራይ በማስገባት የራሳቸው መሬት ለማስፋፋት ነዋሪው ባለቤት በሆነው ህዝብ ዘሩን አጥፍተው መሬቱ በሃል ተቆጣጥረዉታል ።ይህም በዓለም አቀፍ በከባድ ወንጀል ከማስጠየቁም በላይ ፤ተስፋፊነት የዘር ማጥፋት ወንጀልም ነው ። የወልቃይት ፤ጠገዴ ፡ጠለምት ፤ቃፍታ ሁመራ ፤ በ 1968 ዓ.ም. ባፀደቁ የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ ድርጀት ፖሊሲና የአቋም ፕሮግራም መሰረት፤ ዛሬ ማንነቱ የተገፈፈ ህዝብ ፤ የትውልድ ቀዩ መሬት ተነጥቆ፤ ተበታትኖ በስደትና ችግር ወድቆ የሚገኝ ፤ የአማራ ህዝብ ነው ፤ ከሞትና ከስደት የተረፈው እዛው የሚገኝ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ እንደሁለተኛ ዜጋ ተቆጥሮ ውጣ ከዚህ የትግራይ ቦታ እየተባለ ለመኖር እንኳን መብት የለውም ። ይህ ችግርና መከራም የፈጠረው ያመጣው አረሜኔው የናዚ ውላጅ አረጋዊ በርሄ ነው ። በ 1974 ዓ .ም. የሱዳን መግሥት በፕረዚዳንት ጃእፈር ኒመሪ የሚመራ የሱዳን መግሥት በወቅቱ በነበሩ የገዳሪ ጠ/ገዢ ከህ.ወ.ሓ.ት. መሪዎች ተደራድረው በ 1902 ዓ.ም.. በጊዜው የሱዳን ካርቱም አስተዳዳሪ የነበረው ሻለቃ ጋዊን የተባለ ካለመብቱ የኢትዮጵያን ሏላዊነት በመጋፋት በራሱ ፍላጎት ሱዳንን የለም መሬት ባለቤት ለማድረግ በሕገ ወጥ መንገድ የኢትዮጵያ መሬት ወደ ሱዳን ለማካለል ያዘጋጀው ፤ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ማንም የማያውቀው ውድቅ የተደረገ ካርታ ፤የኒሜሪ መንግሥት ካርታውን ይዞ ከህ.ወ.ሓ.ት. መሪዎች ተደራድረን በእነሱ እናገኘው ብሎ በላከው ደብዳቤ ፤በአረጋዊ በርሄ የሚመራው ፖሊት ቢሮ አመራር ተቀብሎ ፤አረጋዊ በርሄን ስብሃት ነጋ ግደይ ዘራጽዮን ሆነው ፤ለዳግማይ ቀጦሮ ተወስኖ ። በ 1975 ዓ ም .ሱዳን ገዳሪፍ ተግናኝተው ፤የህ.ወ.ሓ.ት .መሪዎች 1 ዋናው የቡዱኑ መሪ አረጋዊ በርሄ 2 ስብሃት ነጋ 3 ግደይ ዘራጽዮን 4 አባይ ፀሃይ 5 የውጭ ሃላፊ በመሆኑ አስተናጋጁ ሥዩም መስፍን 6 መለስ ዜናዊ ተባብረው የኢትዮጵያን መሬት ካለ ምንም ቅድመ ሁኔታ አሳልፈው ሰጡ መስከረም 1975 ዓ ም ። ወያኔም ለዚሁ ውለታ የስዳን መንግሥት ሙሉ እውቅና ሰጠ ሁሉ አስፈላጊ ነው የሚባል ለወያኔ ሙሉ እርዳታ እንደሚያደርግ ፤ሌሎች የአረብ ሃገራትም ለህ.ወ.ሓ.ት. እውቅና እንዲሰጡ አደርጋለሁ ብሎ በገባው ቃል መሰረት ግብፅ፤ሊብያ ;ኢራን ;ኢራቅ ;ወ.ዘ.ተ ከመቅፅበት እውቅና ሰጡ ።እላይ ያለዉን ካርታ ይመልከቱ ። ይህ በህ.ወ.ሓ.ት. ፈላጭ ቆራጩ መሪ

አረጋዊ በርሄ አመራር በኢትዮጵያ ላይ የተፈፀመ የወንጀል ክህደት ነው ። የህ.ወ.ሓ.ት. መሪዎች ለጊዝያዊ ጥቅም የሸጡት የኢትዮጵያ መሬት ዛሬ በህዝቡ ፈጥሮት ያለውን ችግር ፤እነዚህ በፈጠሩት ሰበብ ነው ። ባለፈው እየተፈጸመ የመጣው የዘር ማጥፋት ወንጀል የመሬት መስፋፋት ፤የአማራው ማንነት ባህሉ ተነጥቆ ከትውልድ ቦታው ተፈናቅሎ ተባሮ .ኢትዮጵያዊ ኩሩ ፤የሃገር መከታ ህዝብ ፤ ለሞተላት ኢትዮጵያ ፤ ከጠላት እየተከላከለ ሏላዊነትዋ ጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ እያረካከበ የመጣ የአማራው ህዝብ ፤ዛሬ በህ.ወ.ሓ.ት.ወያኔ በጠላት ተፈርጆ ሁለተኛ ዜጋ ሆኖ ሲገደል ሲታሰር መኖሪያ ያጣ ህዝብ ሆኖ በችግር በሰቆቃ እየተገረፈ ነው ። እነዚህ ሰሜን ጎንደር፤ ሰሜን ወሎ በታሪክም የአማራ መሰረት ናቸው ። ፤ሌላው ኢትዮጵያዊ አኦሮሞው አፋሩ ወላይታው ጋምቤላው ቆቱው ሃረሬው ወ.ዘ.ተ.፣ አብሮ በወያኔው ፋሽሽቱ እየተጠቃ ነው ።ይህ ጥቃት የሁሉ ኢትዮጵያዊ ዘር ጥፋት የሁሉ ኢትዮጵያ ሞት ስደት ችግር ሶቆቃ ፤የሁሉ ኢትዮጵያዊ ማንነት ማጣትን መነጠቅም ነው ። ይህን ሁሉ በኢትዮጵያና በህዝብዋ እየደረስ የመጣው እየደረሰ ያለው ፤ኢትዮጵያና ህዝብዋ በአንድነት እንዳይ ኖሩ በታትነን እርስ በሩሱ አጋጭተን ትምክህተኛው ኢትዮጵያዊ ሃገር አልባ እንደርገዋለ ። ይህ ሁሉ ሤራም የኢትዮጵያ የውጭባእዳን ጠላቶች በእጅ አዙር እነ አረጋዊ በርሄ በመያዝ ኢትዮጵያ በሞት አፋፍ አድርሰዋታል ።አረጋዊ ብርሄ በኢትዮጵያ እየደረሰ ላለው ችግር አሁንም ግንባር ቀደም ተጠያቂ ነው ።እሱ ገና ከትግሉ መጀመር አዘጋጅቶ ያመጣው ፕሮግራም ( ፖሊሲ ) አሁንም ሃገር እየፈረሰች ናት እስከ 1977 ዓ .ም . ህዝብ እያጠፋ የመጣ የዘር ማጥፋት ያስፈጸመው የፈጸመ የድርጅቱ ፈላጭ ቆራጭ የነበረ ሰው በሥልጣንሽኩቻ ቢባረርም ከያዙም በስፋት ቀጠሉበት እስከ 1977 ዓ ም . አረጋዊ በርሄ ሲስራቸው የነበሩ ወንጀሎች ሌሎቹ ተረክበው እየቀጠሉበት ይገኛሉ። 1 ግደይ ዘራጽዮን ግደይ ዘራጽዮን የማ.ገ.ብ.ት. መስራች በሥልጣንም ሁለተኛ ሰው ነው ።ይህ ሰው በትውልዱ ኢርትራ ክ/ሃገር ነው ።ወላጆቹም በ 1952 ዓ.ም. ወደ አክሱም በመምጣት የንግድ ሥራቸው በመቀጠል ክህዝብ ተፋቅረው ተስማምተው የሚኖሩ የቤተ ክርስትያን ሰዎች ጥሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው ።

ግደይ ዘራጽዮን ልክ እንደጓደኛው አረጋዊ በርሄ 360 ዲግሪ ተገልብጦ ፀረ ኢትዮጵያ ሏላዊነት ፀረ ኢትዮጵያ አንድነት ፀረ ህዝብ ፀረ ዲሞክራሲ አረሜኔ ጨካኝ ርህራሄ የሚባል የማያውቅ ወዶ ገባ ባንዳ ሃገር አጥፊ ሰው ነው ። ግደይ ዘራጽዮን በማ.ገ.ብ.ት. ምስረታ ም/ሊቀመንበር በየካቲት 11 ቀን 1967 ዓ . ም. ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ ( ተ.ሓ.ህ.ት. ) እንደተመሰረተም አረጋዊ በርሄ ሊቀ መንበር ሲሆን ግደይ ዘራጽዮን ም/ ሊቀመንበር በመሆን በሃላፊነት የነበረ ቀጥሎም በየካቲት 5 ቀን 1968 ዓ . ም .በተካሄደው የዲማ ኮንፈረንስ (ጉባኤ ) የአመራር ምርጫ ሲደረግም ተመርጦ የም/ሊቀ መንበርነቱ እንዳለ በመቀጠል ሥልጣኑ ጨበጠ ፤ይህ በዚሁ እንዳለ የካቲት 5 ቀን 1971 ዓ . ም. በተካሄደው 1ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ በተደረገው የአመራር ምርጫ ተመርጦ የድርጅቱ ስም ከተሓ.ህ.ት. ወደ ህ.ወ.ሓ.ት. ይህም ማለት ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ ፤በሆነበት የህ.ወ.ሓ.ት. ስብሃት ነጋ ሊቀመንበር ሲሆን ግደይ ዘራጽዮን ም/ሊቀ መንበር ሆኖ ተመርጦ እስከ 1977 ዓ. ም . የድርጅቱ ሃላፊ በመሆን የሰራ ቁንጮ መሪ ነው ።እምብዛም ፖለቲካዊ እውቀትና ችሎታ የሚያጥርበት ድሃ የንግግር ችሎታም የሌለው መሪ ።ጨካኝ አረሜነ ተብሎ የተነገረለት ። በዚሁ ጉባኤ የተሰራው አ ሻጥር ድርጅቱን አጥብቀ በኢ- ዲሞክራሲ ለመቆጣጠር ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ ህዝብ አንድነት የሆኑት መሪዎች ወደ ሃላፊነት የመጡበት ጊዜ ነው ።ይህ ሁሉ የተደረገውም በአረጋዊ በርሄ ነው።በዚሁ መሰረት ። 1 ስብሃት ነጋ የድርጅቱ ሊቀ መንበር ፖሊት ቢሮ 2 አረጋዊ በርሄ ወታደራዊ አዛዥ የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ ፖሊት ቢሮ 3 መለስ ዜናዊ የማርክሲሲት ለኒኒስት አደራጅ ኮምሽን ሃላፊና የካድሬዎች አሰልጣኝ በየቦታው የሚመደቡ ካድሬዎች መዳቢና ተቆጣጣሪ ፤እንዲሁም በፕሮፓጋንዳ ጽ/ቤት ምክትል ሃላፊ ። በማእከላይ ኮሚቴ ደረጃ ። 4 ግደይ ዘራጽዮን ም/ሊቀመንበር ፖሊት ቢሮ 5 አባይ ጸሃየ የፕሮፓጋንዳ ጽ/ቤት ሃላፊ ፖሊት ቢሮ 6 ሥዩም መስፍን የውጭ ጉዳይ ሃላፊ ፖሊት ቢሮ እነዚ ሰው በላ አረሜኔ COLD BLOODED መሪዎች ድርጅቱን የተቆጣጠሩት ።ይህ ሁሉ ቅንብርም የተዘጋጀው በተግባር የዋለው በአረጋዊ በርሄ ፀረ ዲሞክራሲ ሥራ ነው ። ወደ ግደይ ዘራጽዮን እንመለስ ፤ ግደይ ዘራጽዮን ሰው ሆኖ በሰው ልጅ ቀንጣት ርህራሄ የሌለው ጨካኝ አረሜኔ አውሬ ፍጡር ነው ፤ በተለያየ ጊዜ ፤የትግራን ህዝብ ለሰንሰለታዊ የአማር ቅኝ ተገዥ፤ ትግራይም የአማራ ቅኝ ግዛት ሆና ለድህነትና ለከፋ ስቃይ የዳረጋት አማራ ነው እያለ ሃቅነት የሌለው የውሸት ፕሮፓጋንዳው በየስብሰባው እንደ ገደል ማሚቶ እያራገበ ሰላማዊ ኢትዮጵያውያን ዜጎች ወንድማሞች አማራና ትግራይ በደም ለማቃባት ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረውም ፤ይህ ደካማ ፀረ ህዝብ ሃሳቡ ደግሞ ተቀባይነት አላገኘም የሚሰማውም አንድም አልነበረም ።ከዚህ ተነስቶ ግደይ አማራ በመጥፎ ውግዘት ያወግዘዋል ። በመሰረቱ ግደይ ዘራጽዮን አማራውን በሚገባ አያውቀውም ፤ይህን ያህል ውግዘት በሄደበት የሚወረውረው ። ግደይ የህ.ወ.ሓ.ት. መሪና ም/ሊቀመንበር ነው ፤በወቅቱ ተ.ሓ.ህ.ት. በ 1968 ዓ.ም..በግንቦት ወር በቡምበት »ሸላሎ ታች

አድያቦ ውስጥ >» የተቋቋመው 06<‹ሓለዋ ወያነ መሪና አዛዥ ምክትሉም አበበ ተክለሃይማኖትና ብስራት አማረ ጋር በመሆን ፤የፈጸመው ግድያ ለሰሚው ጀሮ ቀፋፊ እናም አስደንጋጭ ነው ። ይህ ቡምበት በዚሁ ጊዜ ትልቁ የተ.ሓ.ህ.ት. 06 ነው፤ በዚሁ ጊዜ ከየትም እየተለቀመ ምንም ጥፋት ወንጀል ያልሰራ ንጹህ ዜጋ ፤ተ.ሓ.ህ.ት. የሚቃወም ፤የኢድዩ አባል ነህ እየተባለ ፤የኢ.ህ.አ.ፓ አባል ነህ እየተባል ፤የደርግ ሰላይ ፀረ ኤርትራ ትግል ነህ እየተባለ የተ.ሓ.ህ.ት. መሪዎችና የህዝብ ግንኙነት ካድሬዎች ስም በመለጠፍ እዚሁ ጭር ያለ በረሃ ታስረው የሚሰቃዩ ቁጥራቸው ብዙ ሲሆኑ ፤በግደይ ዘራጽዮን መሪነት ከባድ የሶቆቃ ቶርቸር ለመጥቀስ 1 1 ያለምግብ ውሃ ብርሃንም እንዳያዩ በጨለማ አፍኖ ለቀናት ማሰቃየት 2፤ወንድ ሴት እርቃናቸው በማውጣት ውጭ ከግንድ አጣብቆ በማሰር ቀን በፀሃይ ለሊት በብርድ ፤ 3 በጣም የፈላ ውሃ በታሳሪው ጭንቅላት ላይ በመድፋት ወይም መልቀቅ ፤ 4 በወንድ ብልት 5 ኪሎ አሸዋ ማንጠልጠል ፤በሴትም በግራና በቀኝ ጡትዋ የአሸዋ ከረጢት ማንጠክጠል ለረጅም ሰዓታት በማሰቃየት፤ 5 ጎማ በለበስ ወፍራም የኤለትሪክ ገመድ ሆድ እግሩና ጀርባው ቆዳው እስኪላላጥ ደብድቦ ማሰቃየት ፤ 6 ሴት እርቃንዋን ወጥታ ማህፀንዋ ላይ መግረፍ 7 በመርዝ መግደል ምግብ ላይ በሚጠጣ ወህ ተጨምሮ 8 በጋለ ብረት በሆድ እቃው ማስገባት፤ሰፊ ጉድጓድ ራሳቸው የሚረሸኑ ቆፍሮው ተመልሰው ጉድጓዱ ውስጥ በማስገባት በጥይት ተደብድበው ተረሽነው በጅምላ መግደል ፤ ወ.ዘ.ተ. ወደ ዚሁ ማሰቃያ ማእከል የገባም አይቆይም እጃቸው ላይ ይሞታል ። የአምላክ ፍጡር ያጠፋ መሪ ግደይ ዘራጽዮን ነው ።በዚሁ ሰቆቃ የተገደሉ አዛውንቶች ሰላማዊ ዜጎች ውስጥ ለአብነት ያህል ፤ አቶ ገብረሊባኖስ መዝገቡ ፤አቶ ተወልደ ገብረሥላሴ ፤አቶ አበበ ገብረማሪያም ፤አቶ ሙሉጌታ ደስታ ፤ወ/ሮ ሥላስ ፤ወ/ሮ መድህን ፤ አቶ ወልደ ንጉሥ ፤አቶ ገብረጻድቅ ፀጋይ ፤የ 10 አለቃ ጥላሁን ፤ ቄስ ፅጌ አቶ በላይ ባህታ ይገኙበታል ፤በዚሁ ጊዜ የተገደሉት ገዳዮቹ በብስራት አማረና በአበበ ት/ሃይማኖት የሚመሩ ገዳይ ታጋዮች በለቀቁት ተባራሪ ውስጥ ለወስጥ እንዲታወቅ ብለው ያሰራጩት ከ 4500 በላይ ህዝበ አዳም በ 10 ቀናት ውስጥ በጅምላ ጉድጓድ ተረሽንው መገደላቸው የተረጋገጠበት ወቅት ነው ። ታጋዩ በሕንፍሽፍሽ ሰላማዊ ዜጋ ፀረ ወያኔ የሚል ስም እየተሰጠ ፤በግደይ ዘራጽዮን መሪነት ቡምበት ውስጥ ተገድለዋል ።ይህ ሰው በሻዕብያ የትማረኩ ምርኮኞች ሻዕብያ ስንቀ ስጥቶ ወደ ትውልድ ቦታቸው አሸጋጉርዋቸው በማለት የላካቸው ግደይ ተቀብሎ 300 መቶ ምርኮኞች ረሽኖ መግደሉን ሕዳር ወ 1971 ዓ.ም. ጊዜ ሁሉ ታጋይ የሚያውቀቅ ሓቅ ፤በዚሁ ድርጊቱም ናዚ አዶልፍ ሂትለር ተብሎ መወገዙም ራሱ ግደይ የሚያውቀው የትናንት ትዝታው ነው ። ግደይ ዘራጽዮን የትግራይ ህዝብ ለማዳከም፤ የአማራ ህዝብ ዘሩን ለማጥፋት እቅዱን ለማሳካት በ 1969 ዓ . ም. ድርጅቱን ከሚመሩ ጓደኞቹ በመተባበር ሁሉ 06 ሓለዋ ወያነ ከመሬት በታች 2 ሜትር ጉድጓድ ተቆፍሮ ከ 150 እስከ 200 እስረኞች የሚይዝ ሆኖ መሰራት አለበት ብሎ ባቀረበው ሃሳብ ፤ሁሉ አመራር ተስማምተው ፤የቡምበት ሓለዋ ወያነም ወደ ሱር ሽመልባ ሽራሮ ተዛውሮ ስለነበር ። 1 ሱር 2 ፃኢ 3 ገሃነብ ቃሌማ 4 ፍየል ውሃ 5 ወርዒ 6 ባኽላ 7 ዓዲ በቅሎ በግደይ ዘራጽዮን ትእዛዝ ከመሬት በታች ተሰሩ በነብስ ወከፍ እስር ቤቶች በጣም ተንሽ ቀዳዳ መስኮት ያላት ሆነው በብዛት ተሰሩ ። እነዚህ እስር ቤቶች ለወልቃይት ጠገዴ አዋሳኝም ናቸው ፤ይህ የሆነበት ምክንያት የሰሜን ጎንደሩ አማራ በእነዚህ ማሰሪያ ቦታዎች እያጎሩ ለመግደል ለማጥፋት ለማሰቃየት አሰቃይቶ ለመግደል አስበው የሰሩት ነው ። ግደይ ዘራጽዮን ወደ እነዚህ ሓለዋ ወያነ ከትግራይ ህብረተሰብ አነስተኛ ቁጥር ቢሆንም በአብዛኛው ግን አማራ ወንድ ሴት በአንድ ክፍል ጉድጓድ ከ 200 መቶ በላይ እየታጨቀ በማሰር ሌላ በውጭ ጥልቀት ያለው ሰፊ ጉድጓድ ተቆፍሮ<‹ ዓየ >›ተብሎ የሚጠራ ዛፍ እየተቆረጠ በተቆፈረው ጉድጓድ አስገብተው በማቀጣጠል ጢሱ በትንሽዋ ቀዳዳ መስኮት እየገባ chamber smoke ሰዉ ሁሉ እየታፈነ አለቀ ፤የዓየ እንጨት እንደ ሌላው እንጨት አይነድም የሚተፋው ጢስ ብቻ ነው እንዳለም ረመጥ ነው የሚሆነው ። የዚሁ ፈላስፋና መሪም ግደይ ዘራጽዮን ነው ። ግደይ የአማራው ህዝብ የጨረሰው በዚሁ በጢስ አፍኖ ድምጽ የሌለው መሳሪያ የጨረሰው ። አባይ ፀሃየ ተውልዱ አኩሱም ነው ፤የቤተ ሰቡ ማንነት ብዙ አይታወቅም ፤አባይ ፀሃየ የማ.ገ.ብ.ት መስራች ነው ፤ በትግሉ መጀመሪያ በየካቲት ወር 1967 ዓ ም .ተ.ሓ.ህ.ት. ከመጀመሪያዎቹ አንዱ መሪ ነው ፤ቀጥሎም በዲማ ጉባኤ የካቲት ወር 1968 ዓ ም .ተመርጦ የፖሊት ቢሮ አባልም ነው ፤ቀጥሎም ተ.ሓ.ህ.ት. በየካቲት 5 ቀን 1971 ዓ. ም. በዓዲዳዕሮ ውስጥ ማይ አባይ ተብሎ በሚታወቀው ቦታ በተካሄደው 1 ኛ ድርጅታዊ ጉባኤሲካሄድ ተመርጦ የህ.ወ.ሓ.ት. ፖሊት ቢሮ ሆኖ እስከ አሁን በማገልገል በከፍተኛ ሥልጣን ይገኛል ። አባይ ጸሃየ ወላዋይ አቋም የሌለው መሪ ነው ፤እሥስት በደቂቃዎች ሃሳቡን የሚለዋውጥ ተንሸራታች ፍጡር፤ በትግራይ ህዝብ ግፍ የፈፀመ ፤ስንቱ ንጹሃን ብስራት አማረ በሚያቀርብለት የውሸት ወንጀል ሪፖርት ብዙ የትግራይ አዛውንት ሴቶች ወጣቶች በመካከለኛ ዕድሜ የሚገኙ ሰዎች በተለያዩ ዘዴዎች ህዝብ የፈጀ ወንጀለኛ ከመሆኑ በላይ ፤በ 1969 እስከ 1970 ዓ.ም አጋማሽ የቆየው የደርግ ቀይ ሽብር ተደናግጠው ወደ ተ.ሓ.ህ.ት. ሂወታቸውን ለማዳን የመጡ ወደ ወታደራዊ ማሰልጠኛ በመውሰድ የደርግ ሰላዮች ናችሁ ተጋለጡ እያለ በመሪነት ስብሰባው እየመራ

አስጨንቆ በመያዝ በማስጨነቅ በከባድ ፍርሃት የተነሳ የተሰብሳቢ ብዛት በማኸል ቁሞ በፍርሃት ያልሆነው ነኝ ሲል እየተያዘ 06 ሓለዋ ወያነ በማስገባት የስንቱን ሂወት ጠፋ ፤በዚሁም ላይ በሕንፍሽፍሽ ተበክለሃል ማን አስገባህ ምንስ ተነጋገራቹ የምታውቃቸው በዚሁ ሕንፍሽፍሽ የተበከሉ እነማን ናቸው ተናገር አውጣ እይተበለ ከደርግ ግድያ ያመለጠ የመሰለው ከድርግ የባሰ ተ.ሓ.ህ.ት. ገጠመው ስንትቱን ተገደለ ተረሸነ ናዚ ወንጀለኛው ወጣቱን የጨረሰው አባይ ጸሃየ ነው። ይህ በዚሁ እንዳለ በዚሁ ወቅት የተ.ሓ.ህ.ት. አመራር የፈጸመው ወንጀል ታሪክ ይቅር የማይለው ከወቅቱ ሊቀ መንበር አረጋዊ በርሄ፤ም/ሊቀመንበሩ ግደይ ዘርአጽዮን ስብሃት ነጋ ፤መለስ ዜናዊ ሥዩም መስፍን በመተባበር በፍርሃት ሸሽተው የመጡ በእድሜ ህፃናት ከ 12 ዓመት እስከ 14 ዕድሜ የነበራቸው ህፃናት የበረሃው ኑሮ ከበዳቸው ርሃቡ ብርዱ በተለይ በወባ በሽታ ክፉኛ ስለተጠቁ የእናት አባት እህት ወንድም ናፍቆት በላዩ ተጨምሮ ለኧእምሮ ጭንቀት ስለዳረጋቸው ጥቂትም ታመው ሲተኙ እዛው ሞተው የቀሩ ፤ቀሪዎቹም በዛት ቁጥር ያላቸው ወደ ቤትየ ሊሂድ ቤተሰቦቼን እናቴ ናፈቁ ፤እያሉ ቀኑን ሙሉ ሲያለቅሱ በዚሁም ችግሩን ለመሸከም የማይ ችሉ ህፃናት ፤ከላይ የተጠቅሱ መሪዎች ለነዚህ አቅመ አዳም ያልደረሱ ደቂ እነይ >›የናቴ ልጆች >»በለው ስም በመስጠት፤ ሁሉ ተረሸነው እንዲገደሉ ውሳኔ በምስጠት በአባይ ጸሃየ እርምጃው እንዲፈጸም ተወስኖ እነዚህን አሰባስቦ ወደ ተለያዩ ሓለዋ ወያነ በብስራት አማረ እንዲከፋፈሉም ተወስኖ ገዳይ አስገዳዩ ብስራት አማረ ከፖሊት ቢሮው የተላለፈው ትእዛዝ በቶሎ ተግባራዊ እንዲሆን ተነገረው ። በዚህ ትእዛዝ መሰረት ብስራት አማረ ፤ 1 ፃኢ ሓለዋ ወያነ በስብሃት ነጋ መሪነት ዋና ገዳዮች ሙሉጌታ አለምሰገድ ፤ወዲ ሻምበል( ዘአማኑኤል ለገሰ ዘራይ ይህደጎ 2 ዓዲ በቅሎ 06 በአባይ ጸሃየ መሪነት አለምሰገድ ኢንቺ ተስፋየ ጡሩራ አበበ ዘሚካኤል 3 ዓዲ ጨጓር 06 በመለስ ዜናዊ መሪነት ብስራት አማረ ድልዋ ( ገድለዉታል በሂወት የለም አሰፋ ጉሬዛ ይህም ገድለዉታል በሂወት የለም 4 ሱር 06 በግደይ ዘራጽዮን መሪነት አበበ ት/ሃይማኖት ጀቤ፤ ዓወተ ተስፋይ 5 ባኽላ 06 በአረጋዊ በርሄ መሪነት ሙሉጌታ ፀጋይ፤ መኮነን ገብረማሪያም ( ወዲ ኾምበል ) 6 በለሳ ማይሓማቶ 06 አዋአሎም ወልዱ ሓሰንሹፋ ተስፋየ አፈርሰው አረፋይኔ ጡሩራ በእነዚህ የግድያ ቦታዎች ሌሎች ካላሸን ኮፍ የታጠቁ ገዳዮች በየቦታው የተመደቡ አሉ ፤ይህም የብስራት አማረ ሃላፊነት ነው ።የሁሉ አሰቃቂ ተግባር የደረሰው በአባይ ፀሃየ ምክንያት ነው ።ህጻናትም በስድስቱ ሓለዋ ወይነ ተረሸነው ተገደሉ ይህ በህፃናቱ ለአቀመ አዳም ያልደርሱ የተፈጸመው ግድያ ከመቅጽበት በድርጅቱ በስፋት ተሰራጨ ፤ታጋዩም አሳዘነው አስቆጣው ከታጋዩም አልፎ በገጠሩም ወሬው ተሰራጨ ፤ቀስበቀስም በትግራይ አውራጃዎች ወረዳዎችም ወሬው ተስራጨ ፤የትግራይ ህዝብ በተ.ሓ.ህ.ት. ህ.ወ.ሓ.ት. ፋሽሽታዊ ተግባር ደም አለቀሰ ፤ በደርግ ስርአት ቁጠጥር በመሆኑ ያለው አማራጭ ቤቱ ዝግቶ ማልቀስ ብቻ ነው ።ህ.ወ.ሓ.ት. ተወገዘ በየከተማው ወረዳ የነበርው ህዋሳት ተበታትነው ወደቁ የከተማው ግንኙነቱም ፈረሰ ፤በከተማው አለኝ የሚለው አባል ሙሉ በሙሉ አጣ ።ደርግ በዙ ደጋፊ አግኝቶ ነበር ፤ግን አያውቅበትም ፤ተመልሶ ያፈርሰዋል ወያኒም ይህች ይፈልጋል ። የእነዚህ ህጻናት ግድያ በድርጅቱ ትልቅ ቀውስ እየፈጠረ ሲመጣ መሪዎቹም ለስጋት ስለጣላቸው ፤የፈጠሩት ዘዴ ስድስቱ አመራሮች 1 አረጋዊ በርሄ 2 ግደይ ዘራጽዮን 3 ስብሃት ነጋ 4 አባይ ጸሃየ 5 መለስ ዜናዊ 6 ሥዩም መስፍን በሱዳን ለሚገኙ አባላት ፤ተበታትነው በታጋይም በህዝብም ፊት እየቀረቡ ፤እርምጃው ወስደናል ነገር ግን ለድርጅቱ ህልውና ስንል ነው ፤እነዚህ ከለቀቅናቸው እንደገና ደርግን እየመሩ ሊያስመቱን ስለሚችሉ ለህ.ወ.ሓ.ት. ህልውና ስንል እንዲ ረሸኑ አድርገናል ፤እያሉ ሲማፀኑ በተለ በህዝብ በኩል ተቀባይነት አልነበርውም ፤የትግራይ ህዝብም ድሮውም እውቅና ሰጥቶ ስላልተቀበላቸው የህዝብ ነቀርሳ ፀረ ኢትዮጵያ መሆናቸው በሚገባ ስለሚያውቃቸው ወግዘቱም ቀጠለበት ። አባይ ጸሃየ ፕሮግራሙ በአረጋዊ በርሄ ሲዘጋጅም የድርሻው አስተዋጸኦ ሲወጣ የምጣ ነው ፤በዲማ ኮንፈረንስ በተደረገው ሰብሰባ የነበረው ታጋይ ሲቃወመው ፤ታጋዩን በማስፈራራት ውደዱ ጥሉ ይህ ፕሮግራም በዙ ወራት የጨረሰብን ፤ብናንተ ጭቅጭቅ ንትርክ አንዲት ፊደልም አትሰረዝም ፤የትግል ፖሊሳችን መመርያችን ነው ። ስለ ወልቃይት ጸገዴ ስለ አለውሃ ምላሽም ያነሱ ጥቂት ታጋዮች አሉ ፤እንደ ወራሪነትም የተመለከቱትም ፤አሉ ተ.ሓ.ህ.ት. ወራሪ አይደለም ፤የሚሰጠን ጥቅም ብዙ ስለሆነ ነው ፤ወደ ሱዳን መውጫ ለም መሬት በመሆኑ ፤ የሚመሰረተ የትግራይ መንግሥት ፤እነዚህ ቦታዎች ካልተጨመሩ ሙሉ መንግሥት አይሆንም ስለዚህ ተነጋግረን አምነንበት የተዘጋጀ ነው ።አማራው መሬትየ ተቀማሁ ብሎ ከመጣ ድርብ ድርብርብ ጥቃቱ ተቀብሎ እንደ ጨው ይሟሟል ፤አማራ ማለት ክፉ ጠላት ነው ፤ነፃነትዋ ጠብቃ ለብዙ ዘመናት የቆየችው ትግራይ በምኒሊክ የሚመራው የአማራ መንግሥት አፄ ዮሓንስ ከሞቱ በኋላ በጉልበት ትግራይን ቅኝ ግዛታቸው በማድረግ ሆን ብለው በአማራው ሸዋዊ ዘዴያቸው የትግራይ ህዝብ ሙሉ ነፃነቱ ተገፎ ፤ለልመና ለስደት ለችግር ለበሽታ ተዳርጎ ቤቱ ፈርሶ እየተንከራተተ ያለ በዚሁ ጨቋኝ አማራ ነው ።በተ.ሓ.ህ.ት.የሚመራው የብረት ትግል አማራውን ዘሩን እንዳልነበር አድርገን ፤በአማራው መቃብር የትግራይ ዲሞክራቲክ መንግሥት በትግራይ ይመሰረታል ።

ይህን በተመለከተ የተዘጋጀ ፅሁፍ ካስደመጠ ፤ከአጭር ቀናትም በወይን መፅሄት ለታጋዩ ተዘረጋ ። ሥዩም መስፍን ይህ ሰው ትውልዱ ኤርትራ ክ/ሃገር ዓዲ ቀይሕ ነው ወላጅ አባቱም የጣልያን ባንዳ እንደነበሩ ይታወቃል ፤ ሆኖም ግን ኢትዮጵያ ነፃነትዋ እንደተቀዳጀች በመንግሥት ስራ ተቀጥረው ዓዲ ግራት ውስጥ ለብዙ ዓመታት ሰርተዋል ። ፤ሥዩም መስፈን ከዚሁ ተነስቶ የዓዲ ግራት ልጅ ነኝ የሚለው ።ግን አይደለም ። ሥዩም መስፍን የህ.ወ.ሓ.ት. መስራችም ነው ፤ማ.ገ.ብ.ት. ሲመሰረት ከሰባቱ መስራቶች አንዱ ነው ፤በዛን ጊዜ ኢርትራ በጥር ወር 1967 ዓ.ም. ኢርትራ ሳሕል ወርደው የአንድ ወር ወታደራዊ ሥልጠና በሻዕብያ የተሰጣቸው አመራሮች 1 አረጋዊ በርሄ 2 ሥዩም መስፍን 3 አባይ ጸሃየ 4 ግደይ ዘራጽዮን 5 ሃይሉ መንገሻ 6 አስፍህ ሓጎስ 7 አጋዚ ገሰሰ ናቸው ። ሌሎች የማ.ገ.ብ.ት. መስራች ያልሆንትም እዛው ሳሕል ተገናኝተው የተቀላቀልዋቸው 1 አስገድ ገብረሥላሴ 2 ካሕሳይ በርሄ ( ዶ/ር ግንፅል ) 3 ታከለ ወልደሚካኤል እነዚህም ተቀላቅለው በየካቲት ወር 1967 ዓ ም . ደደቢት በረሃ ወረዱ ፤መሪያቸው አረጋዊ ነው ። ሥዩም መስፍን በተ.ሓ.ህ.ት. ፕሮግራም ዝግጅት ተሳታፊም ነበር ፤ጣልያንን የተዋጉ የትግራይ አርበኞች በጣም ያወግዛል ፤ይጠላል ። ሥዩም ውሽታም ነው የተናገረው ይክዳል ቂመኛ ነው ለጠላው ታጋይ ሌሊት አያሳድረውም መግደል ነው ፤ ከምን እንደተነሳ ባይታወቅም ክፉ ቀናተኛ ነው ፤ ሥዩም አመንዝራ ሽርሙጣም ነው ገና በትግሉ መጀመሪያ በተደጋጋሚ እጅ ከፍንጅ የባላገር ሴቶች እያስገደደ ሲደፍር እየተያዘ የደረሰበት ነገር የለም ፤ሌላው ተራ ታጋይ ግን በጥይት ተደብድቦ ይገደላል ።

ሥዩም መስፍን ብዙ የሰው ሂወት ያጠፋ የገደለ አረሜነ ጨካኝ ነው ፤በወልቃይት ጠገዴ ህዝብ የፈጸመው የግድያ ወንጀል ዘግናኝ ቢሆንም ፤ይህስ ይቀር ተብሎ ሊታለፍ አይቻልም ፤በ 1972 ዓ ም ሥዩምና አርከበ ዕቁባይ ፤ሥዩምና አረጋዊ በርሄ ፤ሥዩምና ግደይ ዘራጽዮን ፤ሥዩምና ሳሞራ የኑስ በተለያዩ ቀናቶች በተገናኙ ህፃን ሴት ወንድ ሽማግሌ ሳይሉ ቤት ውስጥ በማስገባት ሰዉ ወደ ኋላ ዘግተው እሳት እየለቀቁ ቤቱን በማቃጠል ህዝብ ፈጅተዋል ። ሥዩም ሱዳን ውስጥ መሸጎ ፀረ ተ.ሓ.ህ.ት. ህ.ወ.ሓ.ት. ናቸው የሚላቸው በሱዳን ውስጥ ሸቅለው ሂወታቸውን የሚገፉ ንፁሃን የትግራይ ሰዎች በህ.ወ.ሓ.ት. አባላት በለሊት እያስገደለ የስንቱን ሂወት በማያውቁት ሃገር ያጠፋ ወንጀለኛ ነው ። ሥዩም በሱዳን ውስጥ የሚኖሩ የትግራይ ሴቶች በተለያዩ ስራ ተሰማርተው ያፈሩት ሃብት ለመዝረፍ ከሌሎቹ የህ.ወ.ሓ.ት. መሪዎች በመነጋገር ይሁንታ ካገኘ በኋላ እዛው የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች ስብሰባ በመጥራት ራሱ በሚመራው ስብሰባ ያፈራችሁት ሃብት ንብረት እንዳይጠፋ ወርቃችሁ ገንዘባቹህ ለኛ አስረክቡን በጥንቃቄ በአደራ ስም እናስቀምጥላቹህ ፤በምትፈልጉት ጊዜም ውሰዱ ፤ እያለ አስመሳይ በሆነ የማጭበርበሪያ ዘዴ ተጠቅሞ እህቶች ወንድሞች እውነት ስለመሰላቸው ፤ከባንክ ሳይቀር ያስቀመጡት ሃብታቸው አስወጥተው ለሥዩም መስፍን የህ.ወ.ሓ.ቱ መሪ አስረክበው ፤ሙልጭ አድርጎ ከሰበሰበ ወደ በረሃ በመለክ ፤የሚላከው ሃብት ስብሃት ነጋ እየተቀበለ ፤ስብሃትም በበኩሉ ወርቁ ከገጠር ከተማ እየተመለለሱ የሚነግዱ ነጋዴዎች በሚስጢር እየተገናኘ በመስጠት ወርቁ መቀሌ ሽሬ ወ.ዘ.ተ. እየተቸበቸበ የሱዳን ሴቶች ቀልጠው ቀሩ ። ስብሃት ነጋ እና መለስ ዜናዊ እንዴት ለዚሁ ሥልጣን በቁ // ከትግሉ መነሻ ጀምሮ እስከ 1971 ዓ.ም .ሁለቱ ሰዎች በጊዜው በነበረ ታጋይ የተወገዙና የሚጠሉ እነዚሁ ናቸው ፤የሚሰሩት ስራ ሁሉ ከአራጋዊ በርሄ በስተጀርባ ተጠልለው ነው ፤ታጋዩ አያምኑቱም ፤ስብሃትና መለስ ግን ባገኙት መድረክ ታጋዩን መደፍጠጥ ነው ፤ስለ መለስ ዜናዊ ተደጋግሞ የቀረበ አብዮቱታ በአረጋዊ በርሄ ውድቅ እየተደረገ ፤አቤቱታ ያሰሙም የሥልጣን ሡኞች እይተባሉ ተረሽነዋል ።በስብሃትም እንደዚሁ ፤እነዚህ ሁለቱ ታጋዮች በፀረ ኢትዮጵያ አንድነት በፀረ ህዝብ አቋማቸው ግልጽ የማያጠራጥር ሆኖ እየታየ በወቅቱ በነበሩ አመራር እንደ ብልህ አዋቂዎች ለትግሉ አመራርነት ብቃት እንዳላቸው አድርገው በመስበክ ሁሉም ነገር ከነሱ ተማክረው ሲሰሩ የነበረው ታጋይ አጥብቆ ይከታተለው ስለነበር ፤ተወደደም ተጠላ ለሃላፊነት እንደሚያበቁዋቸው ለሁሉ ታጋይ ግልጽ ነበር ፤መክንያቱም አመራሩ የሚያቀርበው ይሾማል ለሚጠላው ይገድላል ፤እድሜ ለአረጋዊ በርሄ ተ.ሓ.ህ.ት.---ህ.ወ.ሓ.ት. ዘረኝነት ሸብርተኝነት ዘረኝነት ሲባልም የክልሉ ሰዎች በአብሮ አድግነት የትምህርት ቤት ጓደኝነት ስር በሰደደ መልኩ የተፈጠረ ድርጅት ነው ።በዚሁ መሰረት በዲማ ኮንፈረንስ በየካቲት ወር 1968 ዓ ም .ሲካሄድ የነበረው እቅድ ስብሃት ነጋና መለስ ዜናዊ ወደ ማእከላይ ኮሚቴው ለማምጣ ሲሆን በተካሄደው ጉባኤ ስብሃት ነጋ በዙ ዲስኩር ተነግሮለት አብዛኛው ታጋይ በግደይ ዘራጽዮን የተነገረው ውሸት መሆኑ ስለሚያውቅ አልተቀበለውም ነገር ግን ምርጫው ተካሂዶ በማጭበርበር ስብሃት በምርጫ አልፈዋል ብለው አጸደቁለት የስብሰባው መሪ አረጋዊ በርሄ ። በመለስ ዘናዊም በአረጋዊ በርሄ የተነገረው ዲስኩር መለስን ሰውነቱ

ሁሉ በቅቤ ቀብቶ ሊቅ የተዋጣለት ታጋይ አድርጎ ሞናሊዛ አስመስሎ አቀረበው ይህ ሁሉግን እልም ያለ ውሸት ነበር ለምርጫም ቀርቦ ወደቀ ።አረጋዊ በርሄ ግደይ ዘራጽዮን አባይ ጸሃይ ሥዩም መስፍን መለስ ዜናዊ በመውደቁ ተናደው አቦራ አስነሱ ፤ላንቃቸው ተላልጦ ቀረ ያመጡት ለውጥ የለም ።በዚሁ መሰረት የተመረጡ; 1 አረጋዊ በርሄ የድርጅቱ ሊቀ መንበርና ወታደራዊ አዛዥ። 2 ግደይ ዘራጽዮን የድርጅቱ ም/ሊቀመንበርና ዋና አስተዳዳሪ ። 3 ስብሃት ነጋ የአረጋዊ በርሄ ረዳት ። 4 አባይ ጸሃየ የፖለቲካ ሃላፊ ።

5 ሥዩም መስፍን የውጭ ጉዳይ ሃላፊ ። 6 ኢጋአዚ ገሰሰ የህዝብ ግኑኝነት ሃላፊ 7 ሙሴ ተኽለ በወታደራዊ ተብባሪነት ። መለስን አሸንፎ የተመረጠው ኢጋአዚ ገሰሰ ነበር ፤ኢጋአዚ ደግሞ የማ.ገ.ብ.ት መስራች ነው ፤ነገር ግን የውቅሮ ሁለት አውላዕሎ ሰው በመሆኑ ፤ይህ የማ.ገ.ብ.ት. መስራች አግልለው መለስን የመተካት የአረጋዊ በርሄ ፕላን ታጋዩ ውድቅ አደረገለት ።ሙሴ ተኽለም በታጋዩ ሃይልና ብርታት ነው የተመረጠ በእነ ግደይ ዘራጽዮን የተጠላ ሰው ነበር ።የመለስ ዜናዊ አለመመረጥ ለአረጋዊ በርሄ እረፍት አልሰጠዉም ኢጋአዚ ገሰሰ እና ሙሴ ተኽለ በድርጅቱ አመራር በዘዴ አስገደላቸው ፤በ 1968 ዓ ም መጨረሻ አመራሩ 5 ( አምስት ) ብቻ ስለቀሩ ለሥራችንም እንቅፋት ስለሆነብን በሚል የምክንያት ዘዴ ፤ 1 መለስ ዜናዊ 2 ስየ አብርሃ 3 አዋአሎም ወልዱ 4 አጽብሃ ዳኘው ( ሸዊት ) መስከረም ወር መጀመሪያ በተለዋጭ ማ/ኮሚቴ ለከፍተኛ ሃላፊነት በቁ ፤ መለስም የፖለቲካ ክፍል ምክትል ዋና ሃላፊ በቃ ፤አረጋዊ በርሄም የሚፈልገው ሰመረለት ። ስለዚህ ስብሃት ነጋና መለስ ዜናዊ ለዚ የሥልጣን ሃላፊነት ያበቃቸው ያደረሳቸው አረጋዊ በርሄ ነው ። ማንነታቸው የሚታወቁና እየታወቁ የመጡ ስብሃትና መለስ ፀረ ኢትዮጵያ ሏላዊነት ፤ ፀረ ኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት ድብቅ ሳይሆን በግልጽ እየተንቀአቀሱ እሱም ራሱ እየተንቀሳቀሰ ሃገርና ህዝብ እዲያጠፉ ተንከባክቡ በመያዝ እዚህ ደረጃ ያደረሳቸው በዋናነት ተጠያቂው ሃላፊነቱን የሚሸከመው አረጋዊ ብርሄ ነው ። ይህ ብቻ አይደለም 1ኛ ፀረ አማራ የሆኑ ንጥር ያለ አቋም ያላቸው ። 2ኛ ፀረ ኢትዮጵያ ሏላዊነት ፀረ ኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት ፈልፍሎ ብቁ ናቸው የሚላቸው እየመለመለ በሚያስተማምን ደረጃ ኢትዮጵያና ህዝብዋ ያጠፉሉ ብሎ ተስፋ የጣለባቸው እንደ ሓረግ እየመዘዘ ለሥልጣን ያበቃቸውም ። 1ኛ ስየ አብርሃ 2ኛ ገብሩ አስራት 3ኛ አዋዓሎም ወልዱ 4ኛው መለስ ዜናዊን ጨምሮ ወደ ሥራ አስፈጻሚ ሃላፊነት አወጣቸው ፤ ከእነዚሁ ፀረ ህዝብ ባለሥልጣናት ስየ አብርሃ የተናገረው ወልጅ አባቴ ቀኛዝማች አብርሃ በአማሮች ስለተገድሉ እኔም በአማራው በቀሌን አወጣለሁ በሎ የተናገረ ሰው ነው ፤የተናገረውም በአማራ ላይ ከፍተኛ የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈጸመ ነው ፤።በዚሁ ተመርጠው የመጡ ፖሊት ቢሮ ( ሥራ አስፈጻሚ ) ይቀርባል ። ወደ ማ/ኮሚቴ ሥልጣን የሚደርሱ ከላይ የተጠቀሱ ሁለት መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆናቸው አስቀድሞ የተጠና የተረጋገጠ በዚሁም ያሳዩት ተግባር ተንተርሶ ለማእከላይ ኮሚቴ ምርጫ የሚቀርበው ። ከህ.ወ.ሓ.ት. በሥልጣን ሽኩቻ የተባረሩት ፤የመጀመሪያዎቹ 1 አረጋዊ በርሄ 2 ግደይ ዘራጽዮን በሓምሌ ወር 1977 ዓ.ም .መጨረሻ በማ.ለ.ሊ.ት ጉባኤ ነው ፤ በጉባኤው በግልፅ የተነገረው እነዚህ ሁለቱም የሰሙት ያዳመጡት ፤በህ.ወ.ሓ.ት ፖሊሲ በህ.ወ.ሓ.ት. ፕሮግራም ቅንጣት የምታክል ልዩነት የለንም ፤ከሃላፊነት የሚነሱ ያሉበት ዋና ምክንያት በብቃት ማነስ ብቻ ነው ፤ሲባል ግደይና አረጋዊ የሰጡት መልስ ወይም የተከራከሩበት ነገር አልነበረም ፤ባይኖርም ግን በግልጽ የታየው የስልጣን ሽኩቻ መሆኑ ነበር ።አረጋዊ በርሄ ገና ከየካቲት ወር 1967 ዓ.ም. እስከ ተባረረባት ሳአት ሓምሌ ወር 1977 ዓ .ም .ድርጅቱን በዋና ህላፊነት የመራ ፤ካለሱ ፈቃድ ውጭ ምንም የማይተገበር ፈላጭ ቆራጭ በመሆን ህ.ወ.ሓ.ትን የመራ ድርጅቱን የመሰረተ ፕሮግራሙን አርቅቆ ወደ ተግባር የለወጠ አንጋፋው መሪ ነው ። አረጋዊ በርሄ በተደጋጋሚ እንደሚናገረው በድርጅቱ አመራር ውስጥ በዙ ንትርክ መቆሳሰል እንደነበረ ይናገራል ፤ይህ ግን ሃቅነት የሌለው ደረቅ ውሸት ነው ፤ከፕሮግራሙ ጀምሮ ሲናገር ፤ፕሮግራሙ ያረቀቁ ሰዎች ይህ ስህተት ነው አንሱት ብንላቸውም አልተቀበሉንም በማለት ደጋግሞ ሲናገር ፤ ሃፍረት ሊሰማው በተገባ ነበር ፤ግን ሰውየው ማወናበድና ማጭበርበር እንደ ስልት ስለሚጠቀምብት “” ደጋግሞ መዋሸት ወደ ሃቅ ይለወጣል--የሚባለውን ዘዴ እየተጠቀመ ህዝብ ያወናብዳል ፤ሰሜን ጎንደር ወልቃይት፤ ጠገዴ ፤ጠለምት ፤ቃፍታ ሁመራ ሰሜን ወሎ አለውሃ ምላሽ ወደ ትግራይ ያካተተው እኮ አረጋዊ ብርሄ ነው ።

የሰሜን ጎንደር ፤የሰሜን ወሎ የህዝቡ ማንነት አማራነቱን ኢትዮጵያዊነቱን እንዲነጠቅ ያደረገው እኮ አረጋዊ በርሄ ነው ።ዛሬ ህዝቡ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ተቆጥሮ በህ.ወ.ሓ.ት እየተሰቃየ ያለው ለዚሁ ሁሉ ችግር ህዝቡ የተዳረገበት እኮ በአረጋዊ በርሄ ነው ። ፀረ አማራ አማራ ይትግራይ ህዝብ ደመኛ ጠላት ነው ፤ብሎ ፀረ አማራ ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳው ያስፋፋው

እኮ አረጋዊ በርሄና፤ ስብሃት ነጋ፤ ግደይ ዘራጽዮን መለስ ዜናዊ ፤አባይ ጸሃይ፤ሥዩም መስፍን እነዚህ ናቸው እኮ አማራውን ያጠፉት ፤ማንነቱን ነጥቀው ፤አማራው ከትውልድ ወደ ትውልድ እይተሸጋገር የመጣ የአማራ መሬት ነጥቀው የትግራይ መሪርት ነው ብለው ወደ ትግራይ ያካለሉት ። ስለዚህ በህ.ወ.ሓ.ት. በአመራሩ ውስጥ በፖሊሲ፤ በአቋም፤ ልዩነት ተፈጥሮ አያውቅም ሁሉ አማራር በዚሁ ተስማምቶ ተደጋግፎ ነው የመጣው ልዩነት የላቸውም ፤ እንደውርስ ሆኖ በመምጣቱም አሁንም እየቀጠሉበት ነው ።በህ.ወ.ሓ.ት ውስጥ እኔ በልጥ እኔ በልጥ እኔ አውቃለሁ ሽርሙጥና ለብቻው ተደብቆ መብላት ተደብቆ መጠጥ መጠጣት ይታያል ፤በአጋጣሚ በዚሁ ሲነጫነጩ ትሰማለህ ፤በዚሁም ደግሞ የድርጅቱ ታጋይ በመሆንህ ታፍራለህ ፤አመራሩ ሁሉ ሂስና ገለሂስ ፈፅሞ አያደርግም የድርጅቱ ፖሊት ቢሮ አመራር ወሰን የሌለው መብት አለው ፤ስድና ልቅ ነው ። ከዚሁ ተነስተውም ብዙ ወንጀል ይፈጽማሉ የሚፈጽሙት ወንጀልም በጠራራ ፀሃይ ነው ። በየትኛውም ጉባኤ ትልልቅ ስብሰባዎች ወይም በካድሬ ስብሰባዎች ሁሉ ፖሊት ቢሮ ስለሚገኙ በእንደዚሁ ስብሰባ የሚያሳልፉት ውሳኔ ሁሉም ተደጋግፈው ተስማምተው ያሳሉፉታ ቅንጣት የሉዩነት ፍንጭ የለም አይታይም ።ይህ እየሆነ እየታየ ንትርኩ መቆሳሰሉ በየት ይመጣል ፤ከዚሁ ተነስተን የአረጋዊ በርሄ እና ሌሎቹ ራሳቸው አግዝፈው ለማሳየት ወንጀላቸው ለመደበቅ የሚፈጥሩት የወደቀ ተረት ነው ። ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ኢትዮጵያን ወሮ በቅኝ ግዛቱ መዳፍ እጅ ከወደቀች ከግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ. ም.እንኳን የሚመራው በህ.ወ.ሓ.ት. ፕሮግራም ነው ፤አረጋዊ በርሄ ያዘጋጀው ፤ሌላው በረሃ በነበረበት የሚወጣ ፖሊሲ እቅድ በአረጋዊ የሚዘጋጁ ነው የነብረው አሁንም በድሮው ስታሊናው ፋሽዚም የሚጠቀሙት የአረጋዊ ብርሄ እቅዶች

ናቸው።/

ሕብረት ምን ማለት ነው ? ጥቅሙስ ? ሕብረት ማለት ሰፊ አመለካከት ያለው ሃገራዊ አድማስ ነው ። ሕብረት በጥቂት ሰዎች ስብስብ የሚጀምር ሆኖ ግን ደግሞ በፍጥነት እያደገ የሚሄድ ነው ፤ሕብረት ወንዝና ተራራ፤ ቋንቋና ሃይማኖት አይደርተውም ፤ሕብረት ጠባብ ብሔርተኝነት ወገናዊነት አይቀበልም፤ ግቡ ኢትዮጵያዊነት ነው ።ሕብረት ከጥቂት ስብስብ ወደ ብዙሃን ስብስብ ፤ከብዙሃን ስብስብ ወደ አንድነት ከአንድነት ወደ ኢትዮጵያዊነት የሚያሸጋግር ሰፊ ጠንካራ ድልድይ ነው ።በምሳሌነት ለመጥቀስም 1ኛ ልሳነ ግፉአን 2ኛ ጎንደር ሕብረት 3ኛ ጎጃም ሕብረት እንደ ምሳሌነት ብንወስድ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ኢትዮጵያዊነት ማእከል ያደረገ የግባቸው እስትራተጂ ኢትዮጵያዊነት ነው ፡ የሚመሩት ህዝባዊ እንቅስቃሴ ለጎንደር ወይም ለጎጃም ህዝብ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን አድማሱ በማስፋት ሞላው ኢትዮጵያ የሚሸፍን ነው ።ይህ እንቅስቃሴ በትኩረት ስንመለከተው ከዘር ከቋንቋ ከሃይማኖት የፀዳ ነው ፤ ዋናው እስትራተጅው ፀረ ክልል ሲሆን ይደመስሰዋ መሰረቱ ያጠፈዋል ፤ በእነዚህ ሕብረቶች ቦታ የለውም ፤ያወግዙታል አይቀበሉትም ፤ሌለው ትልቁ ራኢያቸው በሁለገብ ትግል ያምናሉ ይቀበላሉ ፤ይተባበራሉ ፤ይህ ደግሞ ኢትዮጵያዊ አመለካከታቸው በመስፋቱ በሃገር ውስጥም በውጭም የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የማሰባሰብ ብቃታቸው ከዳር እስከ ዳር ሊያሰባስበው ይችላል ።ጠባብ ብሔርተኝነት በጎሳ መሰባሰብ ለጎሳህ መቆርቆር እነዚህ አደገኛ ፀረ ህዝብ ዝንባሌዎች በጣጥሶ የሚጥላቸው ይህ የአንድነት ሕብረት ነው ። ኢትዮጵያና ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ // ኢትዮጵያ እና የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት( ህ.ወ.ሓ.ት.) የሚገናኙበት መንገድም ሆነ ዓላማ የላቸውም፤አይገናኙም ። ኢትዮጵያና ህ.ወ.ሓ.ት.ያላቸው ልዩነትም የመሬትና ሰማይ ርቀት ነው ፤ የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት በፕሮግራሙ በአቋም ፖሊሲው ትግራይን ከኢትዮጵያ አስገንጥሎ የትግራይ ዲሞክያቲክ መንግሥት ለመመስረት ነው፤ወደ በረሃው ትግል የተሰማራው ።<<ፕሮግራሙ ይመልከቱ ።>>» ህ.ወ.ሓ.ት. በፀረ ኢትዮጵያ ሉአላዊነት በፀረ ኢትዮጵያ አንድነት የተሰለፈ ድርጅት ፤እንደመሆኑ ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ በእጅጉ ተቃራኒ ናቸው ፤የትግራይ ህዝብም ለህ.ወ.ሓ.ት. በእውቅና አልትቀበለውም ፤ በሃይሉ በጉልበቱ ብቻ ነው እንደ መዥገር በትግራይ ህዝብ ተለጥፎ የመጣው ፤ህ.ወ.ሓ.ትና የትግራይ ህዝብም በአንድ ዓይን የማይታዩ የተለያዩ ናቸው ፤ህ.ወ.ሓ.ት በጥቂት ማፍያዎች የተመሰረተ የተፈጠረ ፀረ ህዝብና ፀረ ሃገር ድርጅት ነው፤ጎጠኛ፡ዘረኛ በአንድ ክልል ስም የተነሳ የአፓርታይድ አካል ነው ። በኢትዮጵያ ሉአሏዊ ግዛት የማያምን ፤የኢትዮጵያ ታሪክና ታሪካዊ አመጣጥ የካደ ፤የህዝብ ታሪክ የከዳ ፀረ ኢትዮጵያ ነው ፤ይህ ድርጅት በኢትዮጵያ ጠላቶች በነ ሱዳን ፤ግብጽ ፤ድጋፍና ሃይል የተመሰረተ ነው ፤በእነዚህና ሌሎች ድጋፍ ነው እዚህ ደረጃ የደረሰው ።ይህ ድርጅት ኢትዮጵያን ለማጥፋትና ለማዳከም ቆርጦ የተነሳ ከመሆኑ ባሻገር ፤በህዝብም ብዙ ችግር እያደረሰ የመጣ አሁንም እያደረሰ የሚገኝ ፀረ ኢትዮጵያ ነው ። ጠባብ ብሔርተኛ ከመሆኑም የተነሳ በፕሮግራሙ ያስቀመጠው ኢላማ አድርጎ ያነጣጠረው በፀረ ኢትዮጵያ ህዝብ ፤ በፀረ ኢትዮጵያ ሉአላዊ ግዛትና አንድነት ፤ ታሪካዊ ሃገራዊ እሴቶች ነው ።ከዚሁ በመነሳት ህ.ወ.ሓ.ት. ፀረ ኢትዮጵያ ወራሪ ሃይል ነው ።ይህ ድርጅት በግንቦት ወር 1983 ዓ.ም. ፤ኢትዮጵያን

በመውረር በፀረ ኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎት ሃይሉን ተገን በማድረግ ኢትዮጵያና ህዝብዋ በቅኝ አገዛዝ ስርአቱ ተቆጣጠረ ።ይህ ቅኝ ገዢ ሃይል በኢትዮጵያ ውስጥ የዘረጋው ሕግ በበረሃ ውንብድና ጊዜ ሲጠቀመው የነበረው የህ.ወ.ሓ.ት. ፕሮግራም ኢትዮጵያን ለመበታተን ይጠቅመኛል ብሎ ስላመነ አንኳር የሕገ መንግሥቱ ምሶሶ በማድረግ አስቀምጦታል ። የህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ መሪዎች ነበርና አሁንም በሥልጣን ያሉት ሁሉ ተደምረው ህ.ወ.ሓ.ት. ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲን ለማስጨበጥ አምባገነኑ የደርግ ስርአት ለማስወገድ ፤ብሎ ከአምባገነኑ የደርግ ሠራዊት ትንቅንቅ የጀመረው ገና ከትግሉ መነሻ ጀምሮ ስንት መስዋእትነት እየከፈለ የመጣ ድርጅት ነው ፤ሲሉ ትንሽ ሃፍረት የማይሰማቸው ባንዳና የማፍያ ስብስቦች ፤በህዝብ የፈጸሙት አሁንም እየፈጸሙት የሚገኙት ወንጀል ለማድበስበስ የታሰበ የሌባ አይነ ደረቅ የገዳዮች ማደናገሪያ ነው ። ህ.ወ.ሓ.ት. ለኢትዮጵያ ህዝብና ሉአላዊነት ብለው የከፈሉት መስዋእትነት ፈፅሞ የለም መሪዎቹም አያስቡትም ኢትዮጵያና ህዝብዋ በጠላት ከመፈረጅ በስተቀር የወያኔ መሪዎች ኢትዮጵያ ብለው መጥራት ስለሚቀፋቸው ለኢትዮጵያ ዓዲ ሓበሻ ( የአበሻ ሃገር ) ለህዝቡ ደግሞ (ሓበሻ ) በለው መጥራት የመርጣሉ ፤፤ወያኔ የኢትዮጵያ ግዛት እንኳን በቅጡ አያውቃቸውም ስልጣን እስከ ጨበጠ ድረስ ። ለመሆኑ ዲሞክራሲና ወያኔ፤ ኢትዮጵያና ወያኔ ፤የኢትዮጵያ ህዝብና ወያኔ ፤ ይገናኛሉ ? አይገናኙም ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔ የሚባለው ድርጅት አያውቀውም ፤ ።ወያኔ ፀረ ዲሞክራሲ ነው ፤ወያኔ ፀረ ኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ነው ፤ወያኔ ፀረ ኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት ነው ፤ወያኔ በዘር የተደራጀ ጎሳና ጎጥ ማእከል ያደረገ የአፓርታይድ ድርጅት ነው ፤የትግሉ አላማም ደደቢት በረሃ የገባበትም ትግራይ ነፃ ሃገር የነበረች በአማራው ( ኢትዮጵያ ) ነፃነትዋ ተገፋ ዛሬ የአማራው ቅኝ ግዛት ስለሆነች ፤ትግራይን ነፃ ለማውጣት ብሎም የትግራይ መንግሥት ለማቋቋም ነው ፤ስለዚህ ወያኔና ኢትዮጵያ አይገናኙም ።በዚሁ መሰረት ዛሬ ኢትዮጵያ ሃገራችን የወደቀችው ፤በክፉ ጠላቶችዋ ወያኔዎች ፤ቅኝ አገዛዝ ስርአት ወድቃለች ። ከጣልያን ቀጥሎ የመጣ ወራሪ ቅኝ ገዢ ህ.ወ.ሓ.ት. ነው።የደርግ አገዛዝ በኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ተፍረክርኮ ሲወድቅ ለወያኔም ምቹ አጋጣሚ ስለፈጠረለት በለሱን ቀንቶት ዘው ብሎ አዲስ አበባ ገባ ፤ኢትዮጵያና ህዝብዋ ተቆጣጠረ ፤ ይህ መንገዱም ለወያኔ ያመቻቹሁለቱ ሃያላን መንግሥታት አሜሪካና እንግሊዝ ናቸው ። የወያኔ መሪዎች ነበርና አሁን ሥልጣን ላይ የሚገኙት ሁሉ ማለት ነው ፤የሚናገሩት ነገር ከተግባራቸው ጋር ይጋጫል ፤የሰው ልጅ ዘር ለማጥፋት የተሰማሩት ገና ከ 1969 ዓ.ም. ጀምሮ ሲሆን የሰሜን ጎንደር ህዝብ መሬቱን ለመውረርና የትግራይ ግዛታቸው ለማስፋፋት በከፋ መልኩ ደግሞ ከ 1972 ዓ ም በህ.ወ.ሓ.ት. መሪዎች በአረጋዊ በርሄና በቀሩት ፖሊት ቢሮ ሠራዊታቸው እየመሩ በህዝቡ ላይ የዘር ማጥፋት ከባድ ወንጀል እየፈፀሙ የመጡ እስከ አሁን ካለማቋረጥ በአማራው እየተፈጸመ ያለ የወንጀል ድርጊታቸው ፤በአኝዋክ ሕብረተሰብ የፈጸሙት የዘር ማጥፋት ወንጀል ፤በኦሮሞው ህዝብ የፈጸሙት እየፈጸሙት ያሉት ገድያ ጭፍጨፋ በእስር ቤት ምንም ባላጠፋ ኢትዮጵያዊ ዘጋ በቶርቸር በተለያዩ አፍኖ የማጥፋት ዘዴዎች ኦሮሞው አልቀዋል እያለቀም ነው ፤ከባድ የግፍ ወንጀል እየተፈጸመበት ነው ፤ኦሮሞው ዛሬ ከመሬቱ እየተፈናቀለ በገዛ ሃገሩ ኢትዮጵያ ልክ በአማራው የደረሰው ሃገር አልባ መሬት አልባ እጣ ደርሶት ከርታታ ዜጋ አድርገዉታ ወያኔዎች ፤ በዚሁ መልክ የሰሜን ወሎ ህዝብ መሬት በግፍ የተነጠቀው የማንነቱ መግለጫ የሆነው አለ ውሃ ምላሽ ወ.ዘ.ተ.ተነጥቆ ወደ ትግራይ ተጨምሮ መሬቱ ብቻ ሳይሆን ማንነቱም የተነጠቀ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ዛሬ መሬት አልባ አድርገዉታል ፤ ጋምቤላውም ይህ ችግር ደርሶት መሬቱ ተነጥቆ ለትግሬው ባለሃብት ታድሎ ዛሬ የጋምቤላ ህዝብ የወያኔ ባለሥልጣናት ህዝቡ እንደ አገዳ እያጨዱ በዘር ማጥፋት ተሰማርተው የጋምቤላ ህዝብ በሚፈጸምበት ግድያ አፍኖ ማጥፋት ፤ለመጥፎ ስደት ተዳርጎ በኬንያ ደቡብ ሱዳን እየተሰቃየ ይገኛል ፤ በአፋሩም ይህ የስቀቃ ድርጊት እየተፈጸመበት ነው ፤መሬቱ ተነጥቆ የትግራይ ክልል ነው ተብሎ ከኖረበት ትውልድ ቀዩ ተፈናቅሎ የመሬቱ ባላባት የነበረው ዛሬ እየተንከራተተ ይግኛል ፤እነዚህን ጭብጥ ከያዝን ፤ወያኔ ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ፍትህ ብለን ስንቱን መስዋእትነት ከፍለናል የሚለው ፤ውሃ የማይቋጥር ቀዳዳ አሮጌ ጣሳ ንግግራቸው ምን ያህል አጭበርባሪዎች አስመሳይ ውሸታሞች መሆናቸው በዚሁ ማረጋገጡ በቂ ነው ። ስለሆነም ወያኔ ኢትዮጵያና ህዝብዋ ለማጥፋት የመጣ የባእዳን ቅጥረኛ ወራሪ እንጂ ለኢትዮጵያ በሎ የምጣ አይደለም ።በሥልጣን ያለው የህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ቁንጮ የማፍያ ስርአት በጉልበቱ የመጣ ወራሪ ቀኝ ገዢ ከመሆኑም ባሻገር በሃገሪቱ ያስቀመጠው ሕገ መንግሥት በሎ ወያኔ የሚጠራው፤ ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት በ 1928 ዓ. ም. ከጣልያን ሃገር ይዞት የመጣ ከወያኔ ተመሳሳይ ፖሊሲ ከፋፋይና በታኝ ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ አልቀበልም ብሎ ጣልያንን እንዳሳፈረው ፤የወያኔ ሕግ መንግሥትም ለኢትዮጵያ ህዝብ ሕገ መንግሥት ሊሆን አይችልም ፤ህዝብም አልተቀበለዉም ። ለማጠቃለል .... ህ.ወ.ሓ.ት. ለኢትዮጵያ ብሎ የታገለለት ወቅትና ጊዜ ፈፅሞ የለም ፤በረሃ ወርዶ ለ 17 ዓመታት የታገለው ትግራይን ለመገንጠል ብቻ ነው ። ህ.ወ.ሓ.ት. የሚከተለው ፕሮግራሙ ፤ፖሊሲው ራሱ ባዘጋጀው በሰፋት የሚገልጸው በፀረ ኢትዮጵያ በፀረ ህዝብ አንድነት ከፋፋይ ጎጠኝነት ማእከል ያደረገ ፀረ ህዝብና ፀረ ኢትዮጵያ አንድነትና

ሉአላዊነት ነው ። ህ.ወ.ሓ.ት. ለራሱ የዲሞክራሲ ሕግጋት የማያውቅ ፀረ ዲሞክራሲ ድርጅታዊ ስርአት ፤ለሌላው ህብረተሰብ ዲሞክራሲ ያመጣል ብሎ ማመን የማይታሰብ ከመሆኑም በላይ ወያኔም ከተፈጥሮው ጀምሮ ፀረ ዲሞክራሲ ሆኖ ነው የተፈጠረው ። ህ.ወ.ሓ.ት. ለኢትዮጵያ ብሎ የከፈለው መስዋእትነት በፍጹም የለም በአፈጣጠሩ ታሪክም ይህንኑ የማያሟላ ዘረኛ ነው ። ህ.ወ.ሓ.ት. በዘር ማጥፋት ወንጀል የተሰማራ ፤የለም ሰፊ መሬት ወራሪ ተስፋፊ ፤ለሚመሰርተው የትግራይ ግዛት የሰሜን ጎንደር ፤የሰሜን ወሎ ፤የአፋር ፤እጅግ ሰፋፊና ለም መሬቶች በጉልበቱ የነጠቀ ወደ ትግራይ ያካለለ ፀረ ኢትዮጵያ ነው ። ህ.ወ.ሓ.ት. ኢትዮጵያዊ ሊሆን የማይችልበት በዙ መስፈርቶች ማንሳት ይቻላል ፤ነገር ግን ባጭሩ ህ.ወ.ሓ.ት. ለኢትዮጵያ ሲል ታገልኩ የሚለው አስመሳይ የወሸት ማጭበርበሪያ ጋጋታው ኢትዮጵያን የሚመለከት እንኳን ያወጣው ፕሮግራም የለውም ፤ በምን መልኩ ነው ለኢትዮጵያ ታገልኩ የሚለው ፤ ይህ በትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት ህ.ወ.ሓ.ት. ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ ኢትዮጵያ ህዝብ ፖሊሲው በፕሮግራሙ በማያሻማ መልኩ ገልፆታል፤ አስቀምጦታልም ራሱ በራሱ ፀረ ኢትዮጵያ ድርጅት ሆኖ መፈጠሩ በራሱ ፕሮግራም ( ፖሊሲ ) ፅሁፍ ይጋለጣል። ስለዚህ ወያኔ ለኢትዮጵያ ብሎ የከፈለው መስዋእትነት የለም ።፤ለኢትዮጵያ ብሎም የታገለለ ጊዜም የለም ። ፤የኢትዮጵያ ሃብት ንብረት ፤የህዝብ ሃብት ነብረት መዝረፍ ፤ታሪካዊ ቅርሶች ፤ታሪካዊ መዛግብት በመሸጥ በማቃጥጠል የተሰማራው ህ.ወ.ሓ.ት. ከ 1969 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ዛሬ ፤በምን መልኩ ብሎ ለኢትዮጵያ መስዋእትነት ይከፍላል ፤ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት ሲሰራው የነበረ በከፋ መልኩ ወያኔ ህ.ወ.ሓ.ት.እየሰራው እይፈጸመው ይገኛል ፤ዘር ማጠፋት፤ ግድያ ፤ ዜጎች አፍኖ ማጥፋት ፤የህዝብ መብት መንጠቅ ፤ማገድ የህዝብ ማንነት መንጠቅ ፤የኢትዮጵያ ግዛቶች ለባዕዳን መሸጥ በዘረኛውና ሽብርተኛው ፖሊሲው ህዝብ ማሰቃየት።ስለዚህ ወያኔ ፀረ ሃገርን ፀረህዝብ ፤ቀኝ ገዢ ስርአት ነው ። ኢትዮጵያ ዛሬ ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ህወሓትን እና እኩይ ሥራውን የማያውቅ ኢትዮጵያዊ አለ በሎ ለማመን ያስቸግራል። ህወሓት ሲፈጠር ኢትዮጵያን ለመበታተን፣ ሕዝቧን በዘርና በቋንቋ ለመበታተን የተፈጠረ የኢትዮጵያና የሕዝቧ ደመኛ ጠላት ነው። ዓላማው ኢትዮጵያን በታትኖ መሬቷን በመውረር ታላቋን የትግራይ ሪፓብሊክ መንግሥት ማቋቋም ነው። የድርጅቱ መሪዎች በኢትዮጵያ በህዝብዋ መራር ጥላቻ ያላቸው ናቸው። ሊፍቁት ሊያስወግዱት የማይፈልጉት በፖሊሲና በአቋም መሰረት ያደረገ ። ለዚህ ትልቁ ማስረጃ በፕሮግራማቸው ላይ የተቀመጠው የፖሊሲ አቋማቸው ነው። ኢትዮጵያን የሚመሩበት ሕገ መንግሥትም ሌላው ማስረጃ ነው። ህወሓት ገና በረሃ ሳይወርድ በፀረ-ኢትዮጵያ የውጭ ሃይሎች፣ ማለትም፣ ጣልያን፣ ሊቢያ፣ ሱዳን፣ ግብፅ፣ ሲማሊያ፣ ኢራን፣ ኢራቅ፣ ሶሪያ ወዘተ በመጠኑም ቢሆን ድጋፍ እያገኘ የተፈጠረ ድርጀት ነው። አሁንም የእነሱ ድጋፍና ማበረታታት አልተለየውም። በአንጻሩ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃገራችን አትፈርስም፣ አትበታተንም፣ ለወራሪ ባእድ አትሸጥም፣ አትለወጥም ብሎ በኢትዮጵያ አራቱም ማእዘን በተነሳው አመጽ የወያኔ እቅድ ግቡን ሊመታ አልቻለም።ሱዳኖች ግን ወያኔ በሸጠላቸው ሰፊና ለም መሬት የኛ ነው ብለው በጎንደር ክ/ሃገር ህዝብ ላይ ከወያኔ ተባብረው በህዝብ ላይ ከፍተኛ ጥቃትና ማፈናቀል እያደረሱበት ይገኛሉ ። መላው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሃገሩ ዳር ድንበር በሱዳኖች ተደፍሮ ሲወረር ኢትዮጵያ በጠላት ተወረረች ነው ። የኢትዮጵያ ህዝብም ስሜቱ የሚነካ ሃገሩ ኢትዮጵያ በወያኔዎች ትብብር እየፈረሰች የግዛት ድንበርዋን ተደፍሮ ፤ህዝብዋም ለሶቆቃ ሲኦል የተዳረገበት ጊዜ ነው ።በሕብረት የምንነሳበት ጊዜና ሳአት አሁን ነው ። እኔ ትግሉን የጀመርኩት ከማገብት ጀምሮ ሲሆን፣ በረሃ በወጣሁበትም ጊዜ የህወሓት አመረር በሙሉ የቅርብ ጓደኞቼ ናቸው ። ሆኖም ግን አንድም ቀን ስለ ኢትዮጵያ አንድነትም ሆነ ስለታሪኳ ጥሩ ሲናገሩ ስምቼ አላውቅም። ሕዝብ ስብሰበው የሚሰጡት ትምህርትና ቅስቀሳ ስለኢትዮጵያ ወራሪነት፣ ስለታሪኳ መጥፎነት፣ ስለአማራው ጠላትነት ብቻ ነው። ስለትግራይ ሲያወሩ፣ በአማራው መንግሥት ነፃነቷን ያጣች በማለት መርዛማ በሆነው በሬ ወለደ ተረታቸው ሊያሳምኑት ጥረዋል። ፍላጎታቸውን ለትግራይ ሕዝብ ቢለፍፉም የትግራይ ህዝብ አልተቀበላቸውም ለዚሁም ከባድ መስዋእትነቱ የከፈለው የትግራይ ህዝብ ነው ፤በወያኔዎቹ ተገደለ ሃብት ንብረቱ ተወረሰ ቤቱ ፈረሰ ልጆቹ በሃይል እየተገደዱ ታገሉ ተብለው በየ በረሃው ወድቀው ቀርተዋል ። ዛሬ ከድረጅቱ በሥልጣን ሽኩቻ የተገለሉት ህወሓቶች የሚነዙት በሬ ወለደ የትግራይ የቅኝ አገዛዝ በአማራው መንግሥት እጅ መውደቅ የሚለው፤ ከፕሮግራሙ መነሳት አለበት ብለን ወስነን ፤ያንሱት አያንሱት በፅሁፍ አላየሁም ፤ብሎ የሚናገረው አረጋዊ በርሄ ፤ ማን ነው የድርጅቱ የበላይ መሪ እሱ ራሱ ፤አንሺውስ ማን ነው ? እሱ ራሱ ፤ የድርጅቱ ሊቀ መንበር ራሱ፤ የድርጅቱ ወታደራዊ አዛዥ ፤ሙሉ በሙሉ ትእዛዝ ሰጪ ራሱ ፤ ድርጅቱን ከላይ እስከ ታች የሚቆጣጠረው ራሱ አረጋዊ በርሄ ፤ማረም ማንሳት የነበርው ራሱ አረጋዊ በርሄ ፤ መቆጣጠር ማረም ብቻ ሳይሆን ፕሮግራሙ በሙሉ ፀረ ኢትዮጵያ ፤ፕሮግራሙ በሙሉ ፀረ ኢትዮጵያ ህዝብ ፀረ አንድነት በመሆኑ ተቃጥሎ፤ ሌላ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ለህዝብ ይፋ መደረግ መሆን ነበረበት ፤ይህ አልተደረገም ፤ ታርሞ ከሆነም ለህዝብም ሆነ ለታጋዩ በመጀመሪያ ራሱ የፈጠረው ድርጅት ከነሃገር አፍራሽ ፕሮግራሙ

ራሱም ቆሞ ሂስና ግለሂ አድርጎ ራሱ ያዘጋጀው ፕሮግራም በፅሁፉ የያዘው ስህተት መሆኑ አምኖ ተቀብሎ የፕሮግራሙ ፀረ ኢትዮጵያ መሆኑ ተቀብሎ መዘጋት ፕሮግራሙም መቃጠል ሲገባው ፤በግሉም ሂሱን አውርዶ ነጻ በወጣ ነበር ይህ ሁሉ ሳያደርግ መዋሸትና መመጻደቅ ። አሁንም በሃላፊነት መጠየቁ አይቀርለትም ፤ለዚሁ ሁሉ በኢትዮጵያ እየደረሰ ያለው አረጋዊ በርሄ የፈጠረ መዘዝ ነው ። ። በማሌሊት ምስረታ ጉባኤ ወቅት መለስ ዜናዊ ስለትግራይ በጉባኤው የተናገረውን፣ ማለትም፣ ኢትዮጵያዊነት አንቀበልም ብንል መብታችን ነው ፤ስለ ኢትዮጵያ በዚሁ ጉባኤ የሚነሳበት ምክንያት የለም ፤ጉባኤው የሚያቶኩረው ስለመጪው ትግራይ ዕድገት ብቻ ነው ። ያለውን ማስታወሱ በቂ ነው ። በጉባኤው የነበሩ አባላት የሚያስታውሱት ሃቅ ነው ። ዛሬ ኢትዮጵያ በካባድ አደጋ ላይ የወደቀችው በወያኔ ምክንያት ነው። ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ድርጅቱ የተፈጠረው ኢትዮጵያን ለመበታተን ነው። ፀረ-ኢትዮጵያ ሆኖ መንቀሳቀስ ከጀመረ 44 ዓመት በላይ አስቆጥሯል። ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ስር ካደረጉ ዳግሞ 26 ዓመት ሆኗል። በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ይህ ነው የማይባል መከራና ስቃይ ባማድረሳቸው ተጠያቂዎቹና ለፍርድ መቅረብ ያለባቸው የህወሓት አባላት እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል። እነዚህ እነዚህ ከየካቲት ወር 1967 ዓ.ም. እስከ የካቲት ወር 1968 ዓ.ም. ተ.ሓ.ህ.ት. እየመሩ የመጡ 1 አረጋዊ በርሄ የተ.ሓ.ህ.ት . ሊቀ መንበርና ወታደራዊ አዛዥ ፖሊት ቢሮ 2 ግደይ ዘራጽዮን የተ.ሓ፤ህ፣ት፣ ም / ሊቀ መንበር ፖሊት ቢሮ 3 ስብሃት ነጋ የአረጋዊ በርሄ ረዳት የሓለዋ ወያኔ ( 06 ) ሃላፊ ፖሊት ቢሮ 4 ሥዩም መስፍን የውጭ ጉዳይ ሃላፊ ፖሊት ቢሮ 5 አባይ ጸሃየ የፖለቲካ ክፍል ሃላፊ ፖሊት ቢሮ 6 መለስ ዜናዊ ይህ ሰው በፖሊት ቢሮ ው ደረጃ ባይካተትም በማ / ኮሚቴ ተለዋጭ ሆኖ በማንኛው ውሳኔና ስብሰባ ከላይ ከተጠቀ አምስቱ ተለይቶ አያውቀም ። እድሜ ለነብስ አባቱ አረጋዊ በርሄ ።

ከየካቲት ወር 1968 ዓ.ም በዲማ ኮንፈረንስ ጉባኤ .ስብሃት ነጋ ተጨምሮ አምስት ፖሊት ቢሮ ሆኑ ፤ ሊቀመንበሩ አረጋዊ በርሄ ሲሆን ም/ሊቀ መንበር ደግሞ ግደይ ዘራጽዮን ነበሩ ። ሁለት ማእከላይ ኮሚቴዎች ከላይ በዝርዝር የሚታዩ አመራር 1 አጋአዚ ገሰሰ በሙሴ ተክለ በእጅ አዙር ዘዴ አስገደልዋቸው ፤መክንያቱም ከላይ ከተጠቀሱ አመራር በሚሰሩት በሚፈጽሙት ፀረ ሃገርና ፀረ ህዝብ ተግባራቸው ስለማይስማሙ ። በተ.ሓ.ህ.ት 1 ኛው ጉባኤ የተካሄደው የካቲት 5 ቀን 1971 ዓ፣ም ፣ ሲሆን ለውጦች ተደረጉ ፤የድርጅቱ ስም ከተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ ( ተ.ሓ.ህ.ት. ) ወደ ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህ.ወ.ሓ.ት. )ተለወጠ ጉባኤው የተመራው በአረጋዊ በርሄም ነበር ። በዚህ ጉባኤ የተመረጡ ፖሊት ቢሮ ፤ 1 ኛ አረጋዊ በርሄ ፖሊት ቢሮ ወታደራዊ አዛዥና የድርጅቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ፤ 2 ኛ ስብሃት ሀጋ ፖሊት ቢሮ የድርጅቱ ሊቀ መንበር ፤ 3 ኛ ግደይ ዘራጽዮን ፖሊት ቢሮ የድርጅቱ ም/ሊቀ መንበር ፤ 4 ኛ አባይ ፀሃየ ፖሊት ቢሮ የፖለቲካ ክፍል ሃላፊ ፤ 5 ኛው ሥዩም መስፍን ፖሊት ቢሮ የውጭ ጉዳይ ሃላፊ ፤እነዚህ አምስቱ ድርጅቱ በሃላፊነት እንዲመሩ ተመረጡ ።በሊቀ መንበርነት የተመረጠው አረጋዊ በርሄ ነበር ፤ቀደም ብለው ከላይ የተጠቀሰው በአረጋዊ በርሄ ስብሃት መለስ በድብቅ በተስማሙበት ውዲት መሰረት ፤አረጋዊ ሊቀ መንበርነቱ ለስብሃት ነጋ ስጡት ብሎ አንገቴ ለካራ በማለቱ ፤ስብሃት ሊቀ መንበርነቱን ተረከበ። ሆነም በዚሁ የነበሩ ማ/ኮሚቴ ስብሃት ብቃትና ችሎት የለውም ድርጅቱ ለመምራት አይችልም በማለት ተከራከረው ነበር ፤የአረጋዊ ፍላጎት ለመሻር ግን ስለማይችሉ አረጋዊ ባለው ፀደቀ ። ቀጥሎ የመጣው 2 ኛ ጉባኤ ነው ፤ይህም ተከዜ ውስጥ ፀሊሞይ ተብላ በምትታወቀው ቦታ ተካሄደ ፤ይህም ግንቦት ወር 1975 ዓ .ም .ነበር ።በዚህ ጉባኤ የተመረጡ ፖሊት ቢሮ ። በተጨማሪም በዚሁ ጉባኤ አራት ፖሊት ቢሮ የጨመረ ጉባኤ ነው ።የጉባኤው ሊቀ መንበር አረጋዊ በርሄ ።ምርጫው በሚከተለው ተፈጸመ ፤ 1 ኛ አረጋዊ በርሄ ፖሊት ቢሮ ወታደራዊ አዛዥን የድርጅቱ ዋና የበላይ ሃላፊ ፤ 2 ኛ ስብሃት ነጋ ፖሊት ቢሮ የድርጅቱ ሊቀ መንበር ፤ 3 ኛ ግደይ ዘራጽዮን ፖሊት ቢሮ የድርጅቱ ም/ሊቀ መንበር ፤ 4 ኛ አባይ ፀሃየ ፖሊት ቢሮ የፖለቲካ (ፕሮፓጋንዳ ) ክፍል ሃላፊ ፤ 5 ኛ ሥዩም መስፍን ፖሊት ቢሮ የውጭ ጉዳይ ሃላፊ ፤ 6 ኛ መለስ ዜናዊ ፖሊት ቢሮ የማርክሲሲት ለኒነስት ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን ዋና ሃላፊና የፕሮፓጋንዳ ምክትል ሃላፊ ። 7 ኛ ገብሩ አስራት ፖሊት ቢሮ ፤ 8 ኛ አውዓሎም ወልዱ ፖሊት ቢሮ ፤ 9 ኛ ስየ አብርሃ ፖሊት ቢሮ በወታደራዊ ክፍል ፤ እነዚህ ተመርጠው ተደላደሉ ። ከዚሁ ቀጥሎ የመጣው ምርጫ የማ.ሌ.ሊ.ት ጉባኤ ነው ፤ይህም ከሓምሌ 1 ቀን እስከ ሓምሌ 30 ቀን 1977 ዓ.ም. የረጅም ቀናት ጉባኤ፤ ይህ አንድ ወር የፈጀ ጉባኤ ለህ.ወ.ሓ.ት. መሪዎች መንደላቀቅያና ፈንጠዝያ ነበር የተዘጋጀው ፤በሌላ ደግሞ ትግራይ በከፉ ድርቅ ተመታ የትግራይ ህዝብ የሚላስ የሚቀመስ አጥቶ በዚሁ ከፉ ድርቅ በየበረሃው በየመንደዱ እየ ሞተ ቀባሪ ያጣበት ከፉ ጊዜ ነው የነበረው ፤የሚረዳው ያጣበት ከፉ የምፀት ዓመት የወረደበት ወቅት ;በትግራይ ህዝብ ስም ተለምኖ የመጣ እርዳት በመለስ ዜናዊ በስብሃት ነጋ ከግብረ አበሮቻቸው ጋር ተባብረው በችግር

ከወደቀው ህዝብ አፍ ተነጥቆ ፤ህዝብ እንደቅጠል እየረፈ ሲሞት የሚጠጣው ውሃ ወንዞች ጅረቶች ደርቀው ያፈራቸው የቤት እንስሣት አልቀው ፤መሬት ለትግራይ ህዝብ ጨለማ የሲኦል ነበልባል በሆነችበት ወቅት የህ.ወ.ሓ.ት. መሪዎች ፤ ይህ ጉባኤ ከ 35 000 000 ብር ሚልዮን በላይ ( ከሰላሳ አምስት ሚልዮን በር ) በላይ ወጪ በማድረግ ፤የተንደላቀቀ በምግቡ በመጠጡ እፁብ ድንቅ ተብሎ የተነገረለት የፈንጠዝያ ጉባኤ አካሂደዋል ።ሙሉ በሙሉ ለትግራይ ህዝብ ተብሎ በዓለም ሕብረተሰብ የተለገሰው መጠነ ሰፊ እርዳታ ነጥቀው ፤ዘርፈው ፤ይህ ጉባኤ አካሄዱ ። የትግራይ ህዝብ በወያኔ እጅ መውደቁ ከእግዚአብሄርር የመጣ ቁጣ ነው ።ገና ትግሉ እንደጀመሩ በዚህ ህዝብ ግፍ የፈጸሙት ታሪክ ይቅር አይለዉም ፤ሓለዋ ወያኔው እያስገቡ ገድለዉታል አርደዉልም ፤በዚ ከፉ ድርቅ ጊዜም ቂማቸው ይዘው አጠፉት ፤ለህዝብ ተብሎ የመጣው እርዳታ እየሸጡ ወታደራዊ መሳሪያ በየአይነቱ ከሱዳን ግብፅ ፤ሊብያ ፤ኢራን ኢራቅ ወ.ዘ.ተ.ገዙበት ፤በመሰረቱም ይህ ድርጅት ሲፈጠርም ፀረ ኢትዮጵያ ፀረ ኢትዮጵያ ህዝብ ፀረ ትግራይም ሽብርተኛ ድርጅት ሆኖ ነው የተፈጠረው ።

በዚሁየማ.ለ.ሊት ጉባኤ የተመረጡ መርዎች በሥራ አስፈፃሚነት የተመረጡት የሚከተሉት ናቸው ; በዚሁ ጉባኤ የተወገዱት ባልታሰበ ሁኔታ በድንገት ዱብ እዳ የወረደባቸው አረጋዊ በርሄና ግደይ ዘርአጽዮን ስብሃት ነጋ ተነስቶ ከአረጋዊና ግደይ የአቋም የፖሊሲ ልዩነት የለንም ፤ገንዘብ እንስጣቸው አለን ቢፈልጉ በተራ ታጋይነት በድርጅቱ ታቅፈው ሊታገሉ ይችላሉ ካፈለጉ ደግሞ ወደፈለጉበት ሊሄዱ ይችላሉ ፤በማለት አረጋገጠላቸው ፤በመጨረሻ 1980 ዓ.ም. ለአረጋዊ በሄ $35 000 ሺህ ዶላር ( ሰላሳ አምስት ሺህ ዶላር ) ለግደይ ዘርአጽዮን $ 30000 ሺህ ዶላር ( ሰላሳ ሺህ ዶላር ) አሸክመው መጀመሪያ ግደይ እስከ ገዳሪፍ ሱዳን አጅበው አደረሱት ዘግየት ብሎም አረጋዊ በርሄን እስከ ገዳሪፍ ሱዳን ሸኙት ;የመጡ ሥራ አስፈፃሚዎች። 1ኛ አባይ ፀሃየ ፖሊት ቢሮ የማ.ለ.ሊ.ት ሊቀ መንበር 2ኛ ስብሃት ነጋ ፖሊት ቢሮ የህ.ወ.ሓ.ት ሊቀ መንበር እና የማሕበር ኢኮኖሚ ሊቀ መንበር 3ኛ መለስ ዜናዊ ፖሊት ቢሮ የፕሮፓጋንዳ ጽ/ቤት ዋና ሃላፊ የማለሊት ኮሚሽነር 4ኛ ሥዩም መስፍን ፖሊት ቢሮ የውጭ ጉዳይ ሃላፊ 5ኛ ስየ አብርሃ ፖሊት ቢሮ ሙሉ የህ.ወ.ሓ.ት. ወታደራዊ አዛዥ አረጋዊ በርሄን ተክቶ 6ኛ ተወልደ ው/ማርያም ፖሊት ቢሮ የህዝብ ግኑኝነት/ክፍል / ሃላፊ 7ኛ ገብሩ አስራት ፖሊት ቢሮ የርጅን 1 ሃላፊ እና የማሕበር ኢኮኖሚ ም/ሊቀ መንበር 8ኛ አውዓሎም ወልዱ ፖሊት ቢሮ የርጅን 2 ሃላፊ 9ኛ ጻድቃን ግ/ተንሳይ ፖሊት ቢሮ የርጅን 3 ሃላፊ ቢሆን የሥራዊቱ ኮሚሣር ተወስኖ ቀረ 10ኛ አረጋሽ አዳነ ተለዋጭ ፖሊት ቢሮ ምድብ የለም 11ኛ አርከበ ዕቁባይ ተለዋጭ ፖሊት ቢሮ በወታደራዊ ጽ/ቤት ምድብ ።ከዚሁም በስየ አብርሃ ተባሮ ፤በማሕበር ኢኮኖሚ ለትንሽ ቀናት ቢሰራም ከገብሩ አስራት ስለማይግባቡ ተገሎ ቆየ ።በትንሹ ስለ አርከበ ( የቤቱ ስም ዮሃንስ ነው ) አርከበ የሰከነ አእምሮ የሌለው ግራ የተጋባ ፍጡር እንደ አርከበ የለም በቀን አምስት ከዛ በላይም ፕላን ይቀይሳል ያወጣል ፤አንዷትም ሳይሰራ ይመሽበታ ፤ነገም እንደዚሁ ዛሬ እስራዋለሁ ያለው ማታ ይጥለዋል ፤ቁርሱ ሲበላ እቅድ ያወጣል ፤የተለያዩ ወረቀቶች ከሚጠቀምበት ጠረጴዛ ይከምራል ይህን በጣሙ ይወደዋል ፤ግን አንዷት ስራ ሳያከናውን ይመሸበታ ፤አርከበ እቁባይ ማለት ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ማለት ነው ፤አርከበ ወደ መለስና ስብሃት ወሬ ማመላስ ማቀበል ይወዳል ትንሽ ወሬ ካገኘም እስዋን አግዝፎ መልክ ሰጥቶ የሚዋሽ ውሸታምም ነው ፤ አርከበ ራሰ ወዳድ በምግብ ሳይቀር ስሥታም ምርጥ መርጡ ለኔም ባይ ነው። ለዚሁ ሃላፊነት ያበቃው በችሎታው ሳይሆ በመንደር ልጅነት አረጋዊ በርሄ ነው ፤ግን በማ.ለ.ሊ.ት .ጉባኤ ከመለስና ስብሃት ወግኖ አረጋዊ በርሄን ሰደበው አበሻቀጠው ። 3ኛው ጉባኤ የተካሄደው በ 1981 ዓ.ም. ሲሆን የሥራ አስፈጻሚ ሆነው የተመረጡ እነዚህ ከላይ ተጠቅሰው የሚታዩ ተመረጡ የታየው ለውጥ መለስ ዜናዊ የህ.ወ.ሓ.ት. ማ.ለ.ሊት ሊቀ መንበር ሆነ ፤ስየ አብራሃም የህ.ወ.ሓ.ት. ማ.ለ.ሊ.ት ምክትል ሊቀ መንበር ወታደራዊ አዛዥ ሆነው ተሾሙ ። በአራተኛ ጉባኤም እንዚህ ነው የትመርጡት ።በ 1993 ዓ. ም. በተፈጠረው ህ.ወ.ሓ.ት. በሁለት መሰንጠቁ የተለያዩ ታጋዮች ወደ ፖሊት ቢሮ ደረጃ መጡ እነዚሁም የታወቁ ፀረ ኢትዮጵያ ሉአሏዊነት ፀረ ኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት በዘር ማጥፋት ወንጀል እጃቸው በደም የታጠቡ ህዝብ የፈጁ የሃር ሃብት ንብረት የዘረፉ ሽብርተኞች ናቸው ፤ከተባረሩት ምንም ለውጥ ይላቸውም ፤በመሰረቱ በህ.ወ.ሓ.ት. ለውጥ ይመጣል ብሎ የሚጠብቅ ካለ ሞኝነት የተጠናወተው ብቻ ነው ። ህ.ወ.ሓ.ት. ህ.ወ.ሓ.ት. ነው ።

ይህ ድርጅት ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ጊዜ ወቅት ድርጅቱን እየመሩ የመጡ የህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ

መሪዎች ፤በኢትዮጵያና በህዝብዋ እጅግ ከፍተኛ ወንጀል እየፈፀሙ የመጡ መሆናቸው ሁሉ ኢትዮጵያዊ የሚያውቀው ሃቀና ኡነታም ነው ። 1 የዘር ማጥፋት ወንጀል በአማራው ገና ከ 1969 ዓ ም. በትንሹ የጀመሩት በ 1972 ዓ ም .ታህሳስ ወር በዘግናኝ መልኩ በመቅጠል በሰሜን ጎንደር ወልቃይት ፤ጠገዴ ፤ጠለምት ወዘተ.የሰው ልጅ ዘር አጥፍተዋል ፤ሃብት ንብረቱም በህ.ወ.ሓ፣ት ውርስ እየተደረገ ዘርፈዋል የዚሁ ህዝብ ዘር ማጥፋት አሁንም ወያኔ አላቆመም ቀጥሎበታል ፤በአኝዋክ ህብረተሰብም በዚሁ ተመሳሳይ ዘሩ በማጥፋት ወያኔ ህ.ወ.ሓ.ት. ተሰማርቶ አኝዋኮች ዘራቸው ጠፍተዋል በጋምቤላ ፤በአፋር የዘር ማጥፋት ጥቃት ተፈጽመዋል ። 2 የኢትዮጵያ ሉአላዊነት የግዛት አንድነትዋ በህ.ወ.ሓ.ት. መሪዎች ኢትዮጵያን ለመዳከም ለማጥፋት ይዘዉት በተነሱት አቋም ፕሮግራም መሰርት በማድረግ ፤ ሃገር አፍርሰዋል ኤርትራን አስገንጥለዋ ኢትዮጵያን ካለ ባህር በር በማድረግ ዛሬ ኢትዮጵያ ባህር በር አልባ ዝግ ሃገር ሆናለች ። 3 የህ.ወ.ሓ.ት. መሪዎች በኢትዮጵያና በህዝብዋ ምንም እውቅና ተቀባይነት ሳኖራቸው ባንዳና የማፍያ ስብስብ የኢትዮጵያ ሉአላዊነት በመፃረር በ 1974 ዓ.ም. በሱዳን መንግሥት ተነሺነት ኢትዮጵያ በ 1902 ዓ.ም. በተቀመጠው የመሬት ካርታ አልቀበልም ብላ መሬታች በሃይል ስለ ነጠቀችን የናንተ እርዳታና ተብብር ስለምንፈልግ በማለት ለወያኔ መሪዎች ደብዳቤ በመጻፍ በረሃ ድረስ በመላክ ፤ደብዳቤው ለአረጋዊ በርሄ ደረሰው ፤አረጋዊ በርሄም የነበሩ አመራር ሰብስቦ እነሱም ፤1 ስብሃት ነጋ 2 ግደይ ዘራጽዮን 3 አባይ ጸሃየ 4 መለስ ዜናዊ 5 ሥዩም መስፍን ፤ ተሰብስበው የደብዳቤ ይዘት በመሪው አረጋዊ በርሄ ከተብራራ የወያኔ አመራር በእልልታና በደስታ ተቀብለው በሃገርና በህዝብ የማይታወቅ የባንዳ ስብስብ በ 1975 ዓ. ም. የሱዳን መንግሥት የጠየቀው በተግባር እንደሚፈፅም ከላይ የተጠቀሱ አመራር ስድስቱ በፊርማቸው አረጋገጡ ። እነዚህ የትግራይ ነፃ አውጪ መሪዎች የአማራው ለምና ሰፊ መሬት ዛሬ የሱዳን መንግሥት የሱዳን መሬት ነው እያለ በአማራው ህዝብ እየተፈጸመ ያለው ችግርና መከራ በእነዚህ የወያኔ መሪዎች የተፈጸመ ወንጀል ነው ። ፤ የሱዳን መንግሥትም ለህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ ሙሉ እውቅና በመስጠትና በሙሉ እውቅና ይቀበላል ፤ በተጨማሪም በአረብ ሃገሮች በግብፅ ፤በሊብያ ፤ኢራን ፤ኢራቅ ፤ሶሪያ ፤ሳውዲ አረቢያ ፤ወ.ዘ.ተ ተቀባይነትና እውቅና እንድታገኙ ሙሉ በሙሉ እናስፈጽማለን ፤ከዚሁ በተጨማሪ የሱዳን መንግሥት ሙሉ ድጋፉ ማለት በሱዳን ግዛት የህ.ወ.ሓ፣ት ቢሮ ይከፍታል ወጪው በሱዳን መንግሥት ይሸፈናል ፤ማንም የህ.ወ.ሓ ት. አባል በሱዳን በነፃ ይንቀሳቀሳል ፤ለታጋዮች በነጻ ሙሉ ህክምና ፤አስፈላጊው ወታደራዊ ቁሳቁስ በእኮኖሚ ሙሉ ድጋፍ ያደርጋል ፤የሚል ቃል የሱዳን መንግሥት በመግባት ፤ የወያኔ መሪዎችም ለጊዚያዊ ጥቅም ብለው ሃገር ሸጠዋል ።ይህም በዓለም አቀፍ ሕግ በጣም የተወገዘ ወንጀል ነው ።የኢትዮጵያ ሉአላዊነት በመፃረር ሕጋዊነት የሌላቸው ሕገ ወጥ የትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት የአማራ መሬት ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ የአማራው ግዛትና መሬት ለሱዳን ለጥቅማቸው ሲሉ ሸጠዋል ።በሕግም ይጠየቃሉ ።የሱዳንም እየፈጸመችው ያለች ከሕገ ወጥ የወያኔ ማፍያዎች በመተባበር በአማራው ህዝብ ከትውልድ መሬቱ ማፈናቀ መግደል ማጥቃት በሃይል መሬቱን መንጠቅ ወ.ዘ.ተ ከወያኔ ጋር ተባብራ የአማራው ህዝብ ግፍ እየተፈጸመበት ነው ። 4 የመሬት መስፋፋት ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ የመጀመሪያው ስሙ ፤ ትግራይ ብሔር ድርጅት ፤ቀጥሎ ማሕበር ገስገስቲ ብሔር ትግራይ ( ማ.ገ.ብ.ት. ) ፤ቀጥሎ ትግሉ እንደ ጀመረ (ተ.ሓ.ህ.ት. ) ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ በየካቲት ወር 1967 ዓ. ም. ቀጥሎ በ 1 ኛ ጉባኤው በየካቲት 5 ቀን 1971 ዓ. ም. ስሙን በመለወጥ ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ( ህ.ወ.ሓ.ት. ) ተብሎ ተጠራ ።ይህ ድርጅት ገና ወደ በረሃ ሳይወጣ ትግሉን ከመጀመሩ በፊት በፀረ አማራ ተሰልፎ ፤የአማራ ስም በማጥፋት ትምክህተኛ ፤ፀረ ህዝብ ትግራይ ፤ ተስፋፊ ፤ጨቋኝ ገዢ ፤ትግራይና ኤርትራ ነፃ ሃገራት በቅኝ ግዛቱ በሃይሉ የጠቀለለ ቀኝ ገዢ ወ.ዘ.ተ እያለ ፤ ኢትዮጵያ የምትባል ሃገር የተፈጠረችው በ 19 ኛው ክፍለ ዘመን በምኒሊክ መንግሥትነት ስትሆን ግዛትዋን በመስፋፋት ኢትዮጵያ ተብላ ታወቀች በማለት ታሪክዋን በማጉደፍ ፤የካደ ድርጅት ይህ ነው ።የኢትዮጵያ ስም ያጠፋ ፤ወራሪ ፤ተስፋፊ ፤ሽብርተኛ ፀረ ኢትዮጵያ ፤ፀረ ህዝብ አንድነት ፤ሆኖ ተፈጥሮ የባእዳን ፀረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ቅጥረኛ ሆኖም የመጣ ድርጅት ህ.ወ.ሓ.ት. ነው።

ህ.ወ.ሓ.ት. በረሃ ደደቢት ከመውረዱ በፊት የዘጋጀው የፕሮግራሙ ረቂቅ የዞ ደደቢት እንደገባ ፤ረቂቅ ፕሮግራሙ 1 አረጋዊ በርሄ ዋናው አዘጋጅ 2 ግደይ ዘራጽዮን ተባባሪ 3 አባይ ጸሃየ 4 መለስ ዜናዊ 5 ስብሃት ነጋ 6 ሥዩም መስፍን 7 ስየ አብርሃ 8 አውዓሎም ወልዱ ተባብረውም ፕሮግራሙን አዘጋጅተው ጽፈው በመጽሀፍ መልክ ሰንደው ፤በየካቲት ወር 1968 ዓ . ም. ለህዝብ ተሰራጨ ። የመሬት መስፋፋት የወያኔ መሪዎች ትልቅ ትኩረት የሰጠት የምትመሰረተው የትግራይ መንግሥት ሰፊና ለም መሬት በመውረር ወደ ውጭ መውጫ ከሱዳን የሚያገናኝ ኩታ ገጠም ጎረቤት መሆን ፤የሰፋፊ እርሻ ባለቤት መሆን ፤ወንዝ ፤ጫካ ፤በስፋት ያላት ትግራይ መፍጠር ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ወያኔ

ተ.ሓ.ህ.ት. ሰሜን ጎንደር በሙሉ በፕሮግራሙ በማስገባት ወልቃይት ፤ ጠገዴ ፤ጠለምት ፤ቃፍታ ሑመራ የትግራይ ነው ተብሎ ተካተተ። ሰሜን ወሎ አለ ውሃ ምላሽ ራያና ቆቦ እስከ ታች ሶቆጣ የትግራይ ነው ተብሎ ተካተተ ። ከአፋርም እንደዚሁ በማአድን ሁብታቸው የሚታወቁ ብዙ ወረዳዎች ከዚህ በታች ስም ዝርዝራቸው ቀጥሎ ያለው ከማ.ገ.ብ.ት. እስከ ተ.ሓ.ህ.ት. ቀጥሎም እስከ ህ.ወ.ሓ.ት. በከፍተኛ አመራር ፖሊት ቢሮ ደረጃ ሃላፊነት ድርጅቱን እየመሩ ከየካቲት ወር 1967 ዓ.ም. እስከ ሓምሌ ወር 1977 ዓ .ም. በዋና የድርጅቱ መሪነትና ፈላጭ ቆራጭ ሆኖው የመጡ አረጋዊ በርሄና ግደይ ዘራጽዮን በስልጣን ሽኩቻ ብቻ ሲባረሩ ቀሪዎቹ ደግሞ በዛው የቀጠሉ ናቸው ።በፖሊሲም ሆነ በሚከተሉት የአቋም ፕሮግራም ልዩነት ሳይፈጠርባቸው አንድ አካል አንድ አምሳል ሆነው የመጡ ሁለቱ ዋና መሪዎች እንደተባረሩም የድርጅቱ ሥራና ተግባርም ምንም ሳይዛነፍ በነበረበት ሂደት ቀጠለ ።ቀጥሎም በ 1993 ዓ. ም. በስልጣን ሽኩቻ በመለስ ዜናዊ እና በስብሃት ነጋ የተባረሩትም በፕሮግራሙ አቋምና በፖሊሲ ልዩነት ሳይሆን በተፈጠረው የስልጣን ይገባኛል በዚሁ በመጣው አለመግባባት ስየ አብርሃ ፤ገብሩ አስራት ፤አውዓሎም ወልዱ ፤ተወልደ ወ/ማርያም ፤አረጋሽ አዳነ ከፖሊት ቢሮው ሲባረሩ ፤በሥልጣን በነበሩበት ጊዜ ኢትዮጵያና ህዝብዋ ያጠቁ የገድሉ ዘር በማጥፋት ወንጀል በንጹህን ደም የታጠቡ አረሜኔ ጨካኞች ፤ሃገርና ህዝብ ለባእድ ሃገር የሸጡ ከሃዲ ናቸው ።በለንደኑ ስብሰባ በየካቲት ወር መጀመሪያ 1983 ዓ.ም አሰብ ለኢትዮጵያ ነው የሚገባው ሲሉ አደራዳሪዎች መለስ ዜናዊ ይህን ሲቃወም መለስ ዜናዊ ደግፈው አሰብ የኤርትራ እንጂ የኢትዮጵያ አይደለም ብለው ለአደራዳሪው ሂአርማን ኮሆን የተቃውሞ መልእክት ያሳለፉ እነዚህ ከሃዲዎች ናቸው ፤ዛሬ አዲስ ጭምብል ሰፍተው ኢትዮጵያዊ መስለው የሚታዩት ፤ልክ የነ አረጋዊ በርሄ ዘዴ ተከትለው እኛ ያባረሩን የኢትዮጵያ ግዛት መከበር አለበት ፤የታገልነው በኢትዮጵያ ዲሞክራሲን ለማምጣት ነው ፤አሰብና ባድሜ የኢትዮጵያ ናቸው ብለን በተፈጠረው ክርክር አባረሩን በማለት የፈጠሩት ደርቅ ውሸት ፤ቀላል የማይባል ቁጥር ኢትዮጵያዊም አደናግረዋል፤ ይህ የሚለት የሚናገሩት ለምን በትግሉ በረሃ በነበሩበት አያነሱትም አይከራከሩም ነበር ? ኢትዮጵያዊ ስሜት ያልነበራቸው ቀንድ ያወጡ ፀረ ኢትዮጵያ ፀረ ህዝብ አንድነት ተሰልፈው ኢትዮጵያን ያጠቁ መሪዎች ናቸው ።እነ ስየ አብርሃ አረጋዊ በርሄ ወ.ዘ.ተ. በየስብሰባው በየመድረኩ ኢትዮጵያና ህዝብዋ ሲያወግዙና እንደመስሣቸው አለን እያሉ የጉሮሮ ላንቃቸው እስኪ ሰነጠቅ፤ እያለቀሱ ድርጅቱን ሲመሩ ነው ያየናቸው ፤ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ለማደናገር ብለው የሚዋሹት ከተግባራቸውና ከመጡበት የ 17 ዓመት የአመራር ጉዛቸው የፈጸሙት ግፍ ፤አድበስብሶ አደናግሮ ገበናቸው ለመደበቅ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ለጥቂት ቢያታሉሉም በሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ተቀባይነት የለዉም ።ደደቢት በረሃ የወረዱት ኢትዮጵያና ህዝብዋ ለማጥቃት ለማጥፋት ነው ፤እንዚህ ጠላት እንጂ ወዳጅ አይደሉም አሁንም ጠላት ናቸው፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ላጠቃው ጠላቱ ምህረት መስጠት የለበትም ፤የጊዜ መጠብቅ ካልሆነ ። ፤ኢትዮጵያ አሁን ያለችበት ችግርና ውድቀት እነዚ መሪዎች የፈጠሩት ያመጡት ነው ። ዝም ብሎ ከሰማይ የወረደ አይደለም ።፤ዋናው መሪ አረጋዊ በርሄ ህዝብ የፈጀ ሃገር የሸጠ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ቅርሶችና ታሪካዊ መዛግብት መጻህፍት ከየቤተክርስትያኑ በሃይል ዘርፎ የሸጠ ኢትዮጵያና ህዝብዋ ለዛሬው ሲኦል የዳረገ በየስብሰባው ይጠራል ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ ህዝብ ሰውየ መድረክ ወጥቶም ይናገራል ፤ ፤ይህ ትልቅ ስህተት ነው ፤የፈሰሰው የንጹሃን ደም ጋባዞቹ ረስተዉታል ። ለወደ ፊቱም ይወቀሳሉ ፤ሊወገዙም ናቸው ።የንጹሃኑ ደም እግዚአቢሄር ፊት ቆሞ እየጮኸም ነው /// ቀጥሎ ተፈላጊ ወጀለኞች ዋናዎቹ ስም ዝርዝሩን ከዚህ በታች ያሉትን ሲሆኑ ፤ ለኢትዮጵያውያን የሕግ አዋቂዎች እንስጥ ። እነዚህን ከያሉበት የሕግ ባለሙያ ኢትዮጵያውያን በሚከተሉት የሕግ አሰራርና መንገድ ለፍርድ ማቅረብ የነሱ ሙያ በመሆኑ አካሄዱ ለባለ ሞያዎቹ እንስጥ ፤እኛ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ግዴታችን ይህ ብዙ የገንዘብ ወጪ ስለ ሚጠይቅ በሁሉ ኢትዮጵያዊ እንዲ ሸፈን የኛ ጥረትና ሃላፊነቱን እንወጣ ።

1 አረጋዊ በርሄ 2 ግደይ ዘራጽዮን 3 ስብሃት ነጋ 4 አባይ ጸሃየ 5 ሥዩም መስፍን 6 መለስ ዜናዊ ሲሆኑ ። እነዚህ ስድስቱ አመራር ትግሉ ከመጀመሩ በፊትና ትግሉም እንደ ተጀመረ ተ.ሓ.ህ.ት. ህ.ወ.ሓ.ት. እየመሩ የመጡ ና የመሩ በከፍተኛ ሃላፊነት የነበሩ አሁንም ያሉ ትንሽ ዓመታት ቅየት ብሎም ስየ አብርሃ ፤ገብሩ አስራት ፤አውዓሎም ወልዱ የተቀላቀሉ ፖሊት ቢሮ ፕሮግራሙን በማሰናዳት ፤የስሜን ጎንደር ፤ የሰሜን ወሎ ለምና ሰፊ መሬት ወደ ትግራይ አስገብተው የነጠቁ ተስፋፊዎች የአማራው ህዝብ ዘር ያጠፉ የፈጸሙ ታሪካዊ ቅርሶች የሸጡ ፤ለምና ሰፊ የኢትዮጵያ ግዛት ለሱዳን የሸጡ ወ.ዘ.ተ. ግንባር ቀደም ተጠያቂ ናቸው ቀጥለው ያሉትን ፖሊት ቢሮ እየተከታተሉ የመጡ ሲሆኑ ከእነ አረጋዊ በርሄ የተቀበሉትን አደራ መስመር ተከትለው የኢትዮጵያ አንድነት እያዳከሙ የሃገርና የህዝብ ሃብት ነብረት በመዝረፍ እየዘረፉ ሃገርና ህዝብ ወደ ድህነት አዘቅት ያስገቡ ወራሪ ፀረ ሃገርና ፀረ ህዝብ ፤ብዙ ሚልዮን ህዝብ የፈጁ የህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች ፤የኢትዮጵያ ቀይ ባህርን የሸጡ ሸጠውም ኢትዮጵያ የባህር በር አልባ ዝግ ሃገር ያደረግዋት ከሃዲ ባንዳ ፀረ ኢትዮጵያና

ህዝብዋ እነዚህ ናቸው ፤ 7 ስየ ሃብርሃ 8 አውአሎም ወልዱ 9 ገብሩ አስራት 10 ፃድቃን ግ/ተሳይ 11 ተወልደ ወ/ማርያም 12 አርከበ እቁባይ 13 አረጋሽ አዳነ 14 ክንፈ ገብረመድህን 15 ቴድሮስ ሓጎስ 16 ፀጋይ በርሄ (ሃለቃ ) 17 አዜብ መስፍን 18 ገብረአብ ባርኖባስ 19 ቴድሮስ አድሓኖም 20 ዶ/ር ሰሎሙን እንቋይ 21 አባይ ወልዱ 22 ደብረጽዮን ገ/ሚካኤል 23 ትርፉ ክ/ማርያም 24 ፈትለወርቅ ገ/እግዚአቢሄር 25 ዓለም ገብረዋህድ 26 ጌታቸው አሰፋ 27 አዲስ ዓለም ባሌማ 28 አባዲ ዘሞ 29 በየነ ምክሩ 30 ገብረመስቀል ታረቀ 31 ሙሉጌታ አለምሰገድ 32 ክንፈ ገብረመድህን 33 አበበ ተ/ሃይማኖት የአመራሩ ቀኝ እጅ በመሆን ህዝብ የፈጁም ከሚፈለጉ ማእከላይ ኮሚቴ የነበሩ አሁንም ያሉ በኋላም ወደ ፖሊት ቢሮ የወጡ በሰቆቋ ህዝብ የፈጁ የሚከተሉት ናቸው 1 ዘርአይ አስገዶም 2 ሓሰን ሹፋ 3 ሕቡር ገ/ኪዳን 4 ሳሞራ የኑስ 5 ብርሃነ ገ/ክርስቶስ 6 ሰሎሞን ተስፋይ ጢሞ 7 የማነ ኪዳነ ጃማይካ 8 ቢተው በላይ 9 ታደሰ በርሄ ጋውና 10 ሃለቃ ጸጋይ በርሄ 11 አብርሃ ካሕሳይ 12 ታደሰ ወረደ 13 ወ/ሮ ሮማን ገ/ሥላሴ 14 ኢሳያስ ወ/ጀወርጊስ 15 ብርሃነ ኪ/ማርያም 16 ተክለወይኒ አሰፋ 17 ቅዱሳን ነጋ 18 ኪሮስ ቢተው 19 አስመላሽ ወ/ሥላሴ 20 ጌታቸው አሰፋ 21 ሙሉ ሰንደቅ 22 ሸዊት ገ/ክርስቶስ 23 ሕሽ ለማ 24 አክሊሉ ደንበአርቃይ ፤እነዚህ ብቻ ሳይሆኑ በጠቅላላ ማእከላይ ኮሚቴው የህ.ወ.ሓ.ት ብዙ ከባድ ወንጀል የፈጸሙ ናቸው ከፍርድ አያመልጡም የጠየቃሉ ። ከዚህ በታች ተዘርዝረው የሚታዩ ታጋዮች በንጹሃን ኢትዮጵያዊ ዜጎች ከፖሊት ቢሮው በሚሰጣቸው ትእዛዝ ህዝበ ኢትዮጵያ የፈጁ የሓለዋ ወያኔ ሃላፊዎች ናቸው ። 1 ብስራት አማረ 2 ሓሰን ሹፋ 3 ዘአማኗኤል ለገሰ ( ወዲ ሻምበል ) 4 አበበ ዘሚካኤል 5 መኮንን ገ/ማሪያም ወዲ ኾምበል 6 አረፋይኔ ጡሩራ 7 ተስፋየ አፈርሰው(አጽብሃ 8 ተስፋየ መረሳ (ጡሩራ ) 9 ታደሰ መሰረት 10 ዘርአይ ይሕደጎ 11 ካሕሳይ ቆራጽ 12 መኮነን ገ/ማርያም ( ወዲ ኮምበል ) 13 ዘአማኑኤል ለገሰ ( ወዲ ዛምበል ) 14 ሃይሉ በርሄ (ሃይሉ ሳንቲም ) 15 ሕቡር ገ/ኪዳን 16 ግደይ ወዲፉዳል 17 ተስፋየ ጡሩራ መረሳ 18 ተስፋየ አፈርሰው 19 ልኡል በርሄ 20 ወልደሥላሴ ገ/ሚካኤል 21 ገ/እግዚአቢሄ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽነር የሆነው 22 አስመላሽ ው/ሥላሴ 23 ፍሬ ጎይትኦም ( ሴት )አውስትራሊያ ፐርዝየምትገኝ 24 አራንሺ የአ.አ. ኮሚሽነር 25 ቢተው በላይ እነዚህ በሓለዋ ወያነ በተለያየ የሶቆቃ ዘዴዎች ህዝብ የጨረሱ ያሰቃዩ ዋና ዋናዎቸ ሲሆኑ ብዙዎቹ ግን ለምስታወስ አልቻልኩም በጣም ብዙ ናቸው ፤የእነዚህ ዋና መሪ ደግሞ ብስራት አማረ ነው ።የሞቱም ብዙ